በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር






# ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ

ጥር 2010

# ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ

በተባበሩት መንግስታት የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት

ከስዊዝ የልማት እና ትብብር ኤጀንሲ
በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ

Schweizerische Eidgenossenschaft
Confédération suisse
Confederazione Svizzera
Confederaziun svizra

Swiss Agency for Development
and Cooperation SDC

# የእርሻ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ መልዕክት

ኢትዮጵያ ባስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት በዓለም ደረጃ እውቅና እያገኘች መጥታለች። ከረጅም ዘመናት ጀምሮ እስካ አሁን ድረስ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የግብርና ምርቶችን መሰረት አድርጎ ቆይቷል። እህል የኢትዮጵያ የምግብ ምንጭ ነበር ወደፊትም ምንጭ እንደሆነ ይቀጥላል። የምግብ ፍላጎትን በራስ አቅም ለማሟላት ከፍተኛ ጥረቶች እየተከናወኑ እና ዓመታዊ የግብርና ሰብሎች ምርት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ቢሆንም አገሪቱ በተለይም በአንዳንድ አካባቢዎች በተደጋጋሚ የምግብ እጥረት ያጋጥማታል። ለዚህ የምግብ እጥረት መንስኤ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል ያልተሻሻለ የድህረ-ምርት ሥርዓት አንዱ ነው። የድህረ-ምርት ሥርዓቱ ያልተሻሻለ በመሆኑ ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ከአጨዳ አንስቶ ለተጠቃሚ እስከሚደርስ ድረስ ለብክነት ይዳረጋል። ስለሆነም ለገበያ የሚቀርበው የምግብ እህል መጠን ስለሚቀንስ ለምግብ እጥረት እና ለዋጋ ማሻቀብ አስተዋፅዖ አድርጓል።
በኢትዮጵያ ውስጥ በየዓመቱ ከሚመረተው ምርት ውስጥ እስከ 25% የሚሆነው ምርት በድህረ-ምርት ጊዜ ባክኖ እንደሚቀር ይገመታል። ይህን የብክነት መጠን ማስቀረት ቢቻል ኖሮ በየዓመቱ በጣም ብዙ ሰዎችን ለአንድ ዓመት መመገብ ይቻል ነበር። ይህም በመሆኑ የድህረ-ምርት ብክነት በምግብ ዋስትና፣ በአልሚ ምግብ አቅርቦት እና በኢኮኖሚ መረጋጋት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። ስለሆነም ትርፍ እህል ለማምረት አገሪቱ በምትቀርጻቸው እና ሥራላይ በምታውላቸው ፖሊሲዎች ሁሉ ዋና ጉዳይ ሆኖ ሲታይ ኖሯል። ውጤታማ እና ዘላቂ በሆነ የግብርና ሥርዓት ውስጥ የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ የምግብ እና የአልሚ ምግቦችን ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል ተግባር ነው።

አሁን ላለው የድህረ-ምርት ብክነት ችግር ምላሽ ለመስጠት ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ በሚመለከታቸው ባለድርሻ-አካላት (ከመንግስታዊ ድርጅቶች፣ ከግሉ ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) ንቁ ተሳትፎ እና ከእነሱ በተገኘ ግብዓት ተዘጋጅቷል። የምግብ ብክነትን መቀነስ የተመረተው ምርት በአግባቡ እና በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም ከማስቻሉ በተጨማሪ እያደገ የመጣውን የምግብ ፍላጎት ለመሸፈን ይረዳል። ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ሰነድ ለድህረ-ምርት ብክነት ምክንያት የሆኑ ቁልፍ ማነቆዎችን በመለየት የመፍትሔ ሀሳቦችን እንዲሁም የትግበራ አቅጣጫዎችን በዝርዝር አስቀምጧል። እነዚህ ቁልፍ ጉዳዮች የድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ ሂደት ውስጥ በሚሰሩ ሥራዎች ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል። ቁርጠኝነት፣ ተነሳሽነት፣ ትብብር እና በቂ ሀብት መኖር የድህረ-ምርት ብክነት ችግርን ለመፍታት ወሳኝ ነገሮች ናቸው። ስለሆነም ሰነዱ በፌደራል፣ በክልል እና በወረዳ ደረጃ በሰብል ጥበቃ፣ በግብርና ኤክስቴንሽን እና በምግብ ዋስትና ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለድርሻ-አካላት መመሪያ ሆኖ ያገለግላል። በተጨማሪም ሰነዱ ለፖሊሲ አውጭዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለሌሎች ሙያተኞች እና ለሲቪክ ማህበረሰቡ እንደ ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል።

የቴክኒክ፣ የገንዘብ እና የሎጂስቲክስ ድጋፍ ላደረጉ ተባባሪ ተቋማት እና ሠራተኞቻቸው
በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የእርሻ ልማት ዘርፍ ሥም ማመስገን እወዳለሁ። በተለይም ይህን የስትራቴጂ ሰነድ ዝግጅት ለደገፉ በተባበሩት መንግስታት የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት "በኢትዮጵያ ውስጥ በተሻሻለ የድህረ-ምርት አያያዝ የምግብ ብክነትን መቀነስ" ፕሮጀክትን በመደገፍ፤ እንዲሁም የስዊዘርላንድ መንግስት በስዊዝ የልማት እና የትብብር ኤጀንሲ በኩል ላደረገው የገንዘብ ድጋፍ አመሰግናለሁ። በመጨረሻም ይህን የስትራቴጂ ሰነድ ለማጠናቀቅ በተጠራው የማረጋገጫ ወርክሾፕ ተገኝተው ግብረ-መልስ ለመስጠት እና ሃሳባቸውን ለማካፈል ለመጡ ባለድርሻ-አካላት በሙሉ ምስጋና አቀርባለሁ።

ተስፋየ መንግስቴ
የእርሻ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ

## ማውጫ


የእርሻ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዲኤታ መልዕክት ........ i
የጠቋሚ ዝርዝር ........ iii
የሥዕል ዝርዝር ........ iii
የሠንጠረዥ ዝርዝር ........ iii
አጭር ማጠቃለያ ........ iv

ክፍል ፩ ነባራዊ ሁኔታዎች ........ 1
1. መግቢያ ........ 1

ክፍል ፪ የድህረ-ምርት ብክነት ........ 3
2.1. ዋና ዋና ትርጓሜዎች ........ 3
2.2. የድህረ ምርት ሥርዓት ........ 4
2.3. በመስክ ምልከታው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች ........ 8
2.4. የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ መሠረቶች ........ 9
2.4.1. የኢትዮጵያ ግብርና አጠቃላይ ዳሰሳ ........ 9
2.4.2. የድህረ-ምርት ብክነት እንደ ዋና ተግዳሮት ........ 11
2.5. የመመሪያ መሠረታዊ ደንቦች ........ 11

ክፍል ፫ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ማዕቀፍ ........ 13
3.1. የስትራቴጂው ጥቅም ........ 13
3.2. ራዕይ ........ 13
3.3. ግብ ........ 13
3.4. ዓላማዎች ........ 13
3.5. አጠቃላይ የማዕቀፉ ፅንሰ-ሀሳብ ........ 14

ክፍል ፬ የድህረ-ምርት አያያዝ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 16
4.1. የአካሄዶች እና የትኩረት አቅጣጫዎች አወቃቀር ........ 16

4.2. ምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ ........ 16
4.2.1. ዳሰሳ ........ 16
4.2.2. ዓላማ ........ 17
4.2.3. ተለይተው መሰራት የሚገባቸው ተግባራት ........ 17
4.2.3.1. ውጤታማ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ማስፋፋት ........ 17
4.2.3.2. የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ የማላመድ ምርምርን እና ልማትን ማስፋፋት ........ 18
4.2.3.3. የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ........ 19
4.2.3.3. ክህሎት፣ ስልጠና እና የሰው ልማት ........ 20
4.2.3.4. ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ........ 21

4.3. የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ቅልጥፍና ማሻሻል ........ 23
4.3.1. ዳሰሳ ........ 23

4.3.2. ጥቅል ዓላማ ............ 23
4.3.3. ተለይተው መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች ............ 23
4.3.3.1. የማከማቸት እና የአያያዝ ሥርዓት ............ 24
4.3.3.2. የትራንስፖርት ሥርዓት እና ትስስር ............ 25
4.3.3.3. ዓይነት እና ደረጃዎች ............ 26
4.3.3.4. የምግብ ደህንነት ............ 27
4.3.3.5. የገበያ መረጃ ............ 27
4.3.3.6. የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት ............ 28
4.3.3.7. የመንገድ እና የገበያ መሰረተ-ልማት ............ 29
4.4. ለድህረ-ምርት አያያዝ የፋይናንስ አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል ............ 31
4.4.1. ዳሰሳ ............ 31
4.4.2. ዓላማ ............ 31
4.4.3. መሰራት የሚገባቸው ተግባራት ............ 31
4.4.3.1. ለድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ገንዘብ መመደብ እና ማፍሰስ ............ 32
4.4.3.2. ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተ የገንዘብ አገልግሎት 32
4.4.3.3. ግብርናዊ- ቢዝነስ፣ የግብርና ኢንተርፕራይዞችን እና ምርት ማቀነባበሪያዎችን በኩታ-ገጠም ማደራጀት ............ 33
4.5. እሴት መጨመርን ማስፋፋት ............ 34
4.5.1. ዳሰሳ ............ 34
4.5.2. ዓላማ ............ 34
4.5.3. መሰራት የሚገባቸው ተግባራት ............ 34
4.5.3.1. የግብርና ግብዓት አቅራቢ ............ 35
4.5.3.2. የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ............ 35

ክፍል ፭ የስትራቴጂ አፈፃፀም ስልት ............ 36
5.1.. ለስኬታማ ትግበራ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ............ 36
5.2. የእቅድ እና ትግበራ ምዕራፍ (ደረጃ) ............ 36
5.3. የውጤት ማዕቀፍ ............ 37
5.4. የኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅድ ............ 37
5.5. ክትትል እና ግምገማ ............ 37
5.6. ስጋት እና ሌሎች ታሳቢዎች ............ 38

ክፍል ፮ በድህረ-ምርት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ............ 39
ክፍል ፯ ለድህረ-ምርት አያያዝ የኢንቨስትመንት እቅድ ............ 50
ክፍል ፰ የድህረ-ምርት አያያዝ የማስፈፀሚያ እቅድ ............ 53
ክፍል ፲ የክትትል እና ግምገማ እቅድ ............ 59

አዝል 1: በድህረ-ምርት አያያዝ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች እና መሰራት የሚገባቸው ተግባራት ............ 63

አዝል 2፡ የድህረ-ምርት አያያዝ የውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ እና ጠቋሚዎች ............ 70

ለተመረጡ ቃላት ፍቺ ............ 90

ዋቢ ጽሁፎች ............ 90

## የጠቋሚ ዝርዝር

ጠቋሚ 1: **ዋና ዋና የድህረ ምርት ሥርዓት ተግባራት**................................... 6

## የሥዕል ዝርዝር

ሥዕል 1: ኢትዮጵያ ውስጥ ለአገር-ውስጥ ፍጆታ የሚውል ምርት የአቅርቦት ወይም የገበያ ሰንሰለት ሥዕላዊ መግለጫ .....................................................5
ሥዕል 2: ከኢትዮጵያ ወደውጭ የሚላኩ ምርቶች የገበያ ሰንሰለት ...........................7
ሥዕል 3፡ ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያየዝ ስትራቴጂ ፅንሰ-ሀሳብ ማዕቀፍ (የውጤት ሰንሰለት) ..................................................................................................................15

## የሠንጠረዥ ዝርዝር

ሠንጠረዥ 1: በመስክ ምልከታ የተለዩ የድህረ-ምርት አያያዝ ቁልፍ ጉዳዮች .......... 8

# አጭር ማጠቃለያ

1) **መግቢያ፡** ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ በዋናነት የያዘው የድህረ-ምርት ብክነትን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ በሁሉም ደረጃ የጋራ የሆኑ ዓላማዎችን እና የሚወሰዱ ርምጃዎችን አቅጣጫ ለማስቀመጥ፣ ለማስፋፋት እና ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ተግባራትን ነው። ይህ ስትራቴጂ የተዘጋጀበት ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ምርት እና ምርታማነትን ለመጨመር ብቻ የተሰሩት ሥራዎች የድህረ-ምርት ዘርፉን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ትኩረት እንዳያገኝ ስላደረጉ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ሁኔታ ባልተሻሻለ የቅድመ-ምርት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በተፈጥሮ አደጋዎች የሚደርሰው ብክነት ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ የምርት መጠን ከ 15 እስከ 25 በመቶ ይሆናል። ባልተሻሻለ የአጨዳ፣ የማንጓዝ፣ አከመቻቸት እና የማከማቻ ተባዮች ቁጥጥር ሥርዓት ምክንያት በድህረ-ምርት ጊዜ የሚደርሰው ብክነት መጠን ደግሞ ጠቅላላ የተመረተውን ምርት 30 በመቶ ይሆናል። ስለሆነም የእህል ድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ አገሪቱ የምግብ ዋስትናን እንድታረጋግጥ እና የግብርናው ዘርፍ ገቢ እንዲጨምር አስተዋፅዖ ከማድረጉ በተጨማሪ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው እድገት ድጋፍ ያደርጋል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ዓላማ ገበያ-መር የሆነ ኢኮኖሚ በመገንባት ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣ ከምግብ እህል ርዳታ መላቀቅ እና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ ነው።

2) **መነሻ፡** ከዓለም አቀፉ የምዕተ-ዓመቱ ዘለቄታዊ እድገት ግብ እና የአፍሪካ አገራት መሪዎች የማላቦ የተፋጠነ የግብርና እድገት እና ትራንስፎርሜሽን ለጋራ ብልጽግና እና የተሻለ ሕይወት ስምምነት ጋር በማጣጣም የኢትዮጵያ መንግስት በ1995 ዓም ባወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እና በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም (ከ 2007 እስከ 2012) የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም አሁን ያለውን ከ 15% እስከ 25% የምግብ ብክነት በፕሮግራሙ መጨረሻ በ 2012 ዓም ወደ 5% ለመቀነስ የተለጠጠ ግብ አስቀምጧል። ይህንን ግብ ለማሳካት የሚደረገውን ሂደት ለማገዝ ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂን መቅረፅ አስፈልጓል።

3) **ዋና ዋና ተግዳሮቶች፡** ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ከአፍሪካ ሁለተኛ ስትሆን 85% የሚሆነው ሕዝቧ ኑሮው የተመሰረተው አነስተኛ የመሬት ይዞታን (0.5 ሄክታር) መሰረት ባደረገ ከእጅ-ወደ-አፍ ግብርና ላይ ነው። የዚህ አነስተኛ ከእጅ-ወደ-አፍ ግብርና ምርታማነት ዝቅተኛ ሲሆን ዋና ዋና ምክንያቶችም የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት፣ የገንዘብ አቅርቦት/ አገልግሎት፣ የተሻሻሉ የማምረቻ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ የመስኖ እና የገበያ ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን፤ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት፣ በቂ የማከማቻ ቴክኖሎጂ እና ሥርዓት አለመኖር እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች በሚፈለገው ደረጃ አለመስፋፋት የመሳሰሉት ናቸው። ስለሆነም የግብርናው ዘርፍ የአገሪቱን የምግብ ፍላጎት መሸፈን አልቻለም። ይህም በመሆኑ እስከ ግማሽ የሚጠጋው የአገሪቱ ሕዝብ ገቢው ከድህነት ወለል በታች ነው ተብሎ ይገመታል። በተባበሩት መንግስታት የዓለም የምግብ እና እርሻ ድርጅት እና የዓለም ምግብ ፕሮግራም የሰብል እና የምግብ ዋስትና ግምገማ ተልዕኮ ሪፖርት እንደሚያሳየው በ 2002 ዓ.ም ብቻ አጠቃላይ የድህረ-ምርት ብክነት 2.04 ሚሊዮን ቶን ነበር። በተቃራኒው ደግሞ አገሪቱ አጠቃላይ የምግብ ፍላጎት ሚዛኗን ለማስተካከል በዛው ዓመት 1.16 ሚሊዮን ቶን እህል ከውጪ ማስገባት እንደነበረባት ይሄው ሪፖርት ያሳያል። በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ ያለው መረጃ በጣም የተለያየ ቢሆንም የአፍሪካዊያን የድህረ-ምርት ብክነት የመረጃ ሥርዓት ሪፖርት እንደሚያሳየው በጤፍ ምርት 12.3%፣ በማሽላ ምርት 11.6%፣ በስንዴ ምርት 9.9% እና በበቆሎ ምርት 16.8% የድህረ-ምርት ብክነት ሊደርስ እንደሚችል ነው። የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ አገሪቱ ከውጪ የምታስገባውን የምግብ እህል መጠን በመቀነስ

የምግብ አቅርቦትን ያሻሽላል፡፡ ይህም የድህረ-ምርት ብክነት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ገቢን ለመጨመር እና የአልሚ ምግብ አቅርቦት ደረጃን ለማሻሻል ማነቆ መሆኑን ያሳያል፡፡

4) **ራዕይ፡** የብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ራዕይ ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተዋፅዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ ነው፡፡

5) **ግብ፡** የብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ግብ የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነትን እና የአልሚ-ምግብ ይዘትን በመጠበቅ፣ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር ነው፡፡

6) **አጠቃላይ ዓለማ እና ዝርዝር ዓላማዎች፡** ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አጠቃላይ ዓላማ አግባብነት ያለው የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን በማላመድ እና ሥራላይ በማዋል በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ ነው፡፡ አራት ዝርዝር ዓላማዎችም ተለይተዋል፡፡ እነሱም

ሀ፡ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ በምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ

ለ፡ የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ቅልጥፍና በማሻሻል የድህረ-ምርት አያያዝ ተግባራትን ማዘመን

ሐ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ የፋይናንስ አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል

መ፡ በሁሉም የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪወች ውስጥ እሴት ለሚጨምሩ አካላት ዘለቄታ ባለው መንገድ ድጋፍ ማድረግ ናቸው፡፡

7) **መሰራት የሚገባቸው ተግባራት፡** እያንዳንዱን ዝርዝር ዓላማ ለማሳካት በርከት ያሉ መሰራት ያለባቸው ተግባራት እና መፍትሄ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡ መሰራት የሚገባቸው ሥራዎች የተለዩት የታተሙ ሰነዶችን በመመርመር፣ የመስክ ቅኝት በማድረግ እና በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ተሳታፊ ከሆኑ ተዋኒያን ጋር ሠፊ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ነው፡፡ ቃለ-መጠይቅ ከተደረገላቸው መካከል የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ገበያ ላይ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች፣ ቴክኖሎጂ በማምረት እና ሌሎች ግብዓቶችን ለግብርናው ዘርፍ የሚያቀርቡ ድርጅቶች፣ ከሙያ እና ቴክኒክ ማሰልጠኛ እስከ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያሉ የማሰልጠኛ ተቋማት፣ የምርምር እና ልማት ተቋማት፣ አርሶ አደሮች ወዘተ ይገኙበታል፡፡ የስትራቴጂውን ዋና ዋና ግቦችን እና የስኬት ጠቋሚዎችን የሚያሳይ የውጤት ማዕቀፍ እንዲሁም አስፈላጊ ወጪችን እና በጀትን የሚያሳይ የኢንቨስትመንት እና የአፈፃፀም እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

8) **የሰነዱ አወቃቀር**: ይህ ሰነድ በአምስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡

**ክፍል ፩፡ ነባራዊ ሁኔታዎች**: ይህ ክፍል በአጠቃላይ ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ዝግጅት መነሻ የሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያብራራል

**ክፍል ፪**: **የድህረ-ምርት ብክነት፡** ይህ ክፍል ከምግብ ዋስትና እና ከገቢ ማመንጨት ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ድህረ-ምርት ሥርዓት እየገጠመው ያለውን መሰረታዊ ተግዳሮቶች (ችግሮች) ይተነትናል፡፡ ስለሆነም ይህ ክፍል ለስትራቴጂው መውጣት መሰረት የሆኑ ምክንያቶችን እና ጭብጦችን የያዘ ነው፡፡

**ክፍል ፫: የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ማዕቀፍ**: በዚህ ክፍል የስትራቴጂው ግብ፣ አጠቃላይ ዓላማ እና ዝርዝር ዓላማዎች ተብራርተዋል፡፡ እነዚህን ግቦች እና ዓላማዎችን ማሳካት ከተቻለ ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ታረጋግጣለች፣ የህዝቧ ገቢ ይጨምራል እንዲሁም አጠቃላይ የህዝቧ ኑሮ ይሻሻላል፡፡

**ክፍል ፬: የድህረ-ምርት አያያዝ የትኩረት አቅጣጫዎች:** *ዋና ዋና ተግዳሮቶች እና ተግዳሮቶችን ለመፍታት መሰራት ያለባቸው ሥራዎች ተለይተው በዚህ ክፍል ውስጥ ተካተዋል፡፡ የእነዚህ ዋና ዋና ተግዳሮቶች እና በተጓዳኝ መሰራት ያለባቸው ሥራዎች የመፈፀሚያ ጊዜ እና የሚያመጡት ተፅዕኖ ባህሪ በጊዜ መስፈርት ሲታይ ከአጭር ጊዜ እስከ ረጅም ጊዜ ይለያያል፡፡ ስለሆነም የኢንቨስትመንት እቅዱ በአምስት ዓመት የተከፋፈለ ሲሆን በዚህ በጊዜ በተገደበ ኢንቨስትመንት መሰራት ያለባቸው ፕሮግራሞች በቅደም ተከተል እና የሚጠበቁ ግቦች ተቀምጠዋል፡፡*

**ክፍል ፭: የስትራቴጂ የአፈፃፀም ስልት:** *በዚህ ክፍል የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የትግበራ/ የአፈፃፀም ስልቶች እንዲሁም ክትትልን እና ግምገማን ጨምሮ በምክረሀሳብ ደረጃ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ የትግበራ/ የአፈፃፀም ስልቶች እንዲሁም የውጤት ማዕቀፍ እና የኢንቨስትመንት እቅድ ስትራቴጂው እየተቀረፀ ሲሄድ አብረው በተጨማሪ የሚሰሩ ናቸው፡፡*

**ክፍል ፮**: *የመጀመሪያው የአምስት ዓመት የትግበራ ምዕራፍ ውጤት ማዕቀፍ እና የኢንቨስትመንት እቅድ በአጭሩ በክፍል ፮ ውስጥ ተቀምጧል፡፡*

9) ***መደምደሚያ:*** *የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት (እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር)፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ያሉ የመንግስት አካላት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን በተሳካ ሁኔታ ሥራላይ ለማዋል ከዚህ በታች የተቀመጡት ጉዳዮች ወሳኝ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡*

*ሀ፡ የኢትዮጵያ ግብርና ወደፊት ሊበለጽግ የሚችል ከፍተኛ አቅም ስላለው ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ዋና አንቀሳቃሽ መሆኑ እና ለምግብ ዋስትና መሻሻል ብሎም ለድህነት ቅነሳ ጉልህ አስተዋፅዖ እንዳለው ግንዛቤ መውሰድ*

*ለ፡ በድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ረገድ ቶሎ ለውጥ በሚያመጡ ጥቂት ተግባሮች እና ዓላማዎች ላይ ብቻ ማተኮር፤ በአንድ ጊዜ መሰራት ለሚገባቸው ለጥቂት ጉዳዮች እና ሰብሎች ብቻ ትኩረት መስጠት*

*ሐ፡ ለስትራቴጂው በጀት (ገንዘብ) መመደብ እና ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነት መኖር*

*መ፡ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ያካተተ ጠንካራ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት መመስረት*

*ሠ፡ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ወደ ስትራቴጂ ትግበራው ሙሉ በሙሉ እንዲገቡ የድህረ-ምርት ልቀት ማዕከል፣ ውጤታማ የምክክር-መድረኮች ግንኙነት፣ ተቋም (ለምሳሌ የኢትዮጵያ የድህረ-ምርት አያያዝ ባለሙያዎች ማህበር) የመሳሰሉትን ማቋቋም እና ማጠናከር*

*ረ፡ የገንዘብ ተቋማት ግብርናውን እንዲደግፉ ማበረታታት*

*ሰ፡ የግብርናውን እድገት (ልማት) ለመደገፍ ወሳኝ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን እንደ መጓጓዣ (ትራንስፖርት) እና የመንገዶች ትስስር፣ የመረጃ እና ግንኙነት ቴክኖሎጂ፣ ኤሌክትሪክ እና ሌሎች ከገበያ ጋር የተገናኙ መሰረተ-ልማቶችን መመስረት*

ሸ፡ ሥርዓተ-ፆታን፣ ወጣቶችን፣ ኤች.አይ. ቪ/ ኤድስን እና ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን (የአየር ንብረት እና ሌሎች ተለዋዋጭ ነገሮችን) በሁሉም ደረጃ ግምባር-ቀደም አጀንዳዎች ማድረግ

# ክፍል ፩

# ነባራዊ ሁኔታዎች

## መግቢያ

10) ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናዋን እንድታረጋግጥ እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ግቦችን እንድታሳካ የግብርናው ዘርፍ የሚያበረክተውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ በመረዳት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሰት በ 1986 ዓ.ም. ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ በመቅረጽ የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለመጨመር እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል የፖሊሲ ምላሽ ሰጥቷል። በዚህ የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ መሰረት የተሰሩ ሥራዎች አነስተኛ አርሶ አደሮች የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ግብርናቸውን ወደ ገበያ ተኮር ግብርና እንዲለውጡ፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ምርቶች እንዲያመርቱ፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ሰብሎች ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ፣ ሰፋፊ እርሻዎች እንዲለሙ ድጋፍ ማድረግ፣ አርሶ አደሮችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ ገበያ ጋር የማስተሳሰር እና የሚሰሩ ሥራዎች የግብርናውን ስነምህዳር መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ማድረግ ነበሩ።

11) በተጨማሪም የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ የግብርና ምርታማነትን ለማሻሻል እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መወሰድ የሚገባቸውን ሌሎቸ የፖሊሲ ርምጃዎችን አስቀምጧል። እነሱም

ሀ፡ ለአነስተኛ አርሶ አደሮች እውቀትን እና ክህሎትን በተሳለጠ እና ዘለቄታ ባለው መንገድ ለማስተላለፍ እና የግብርና ምርምር ውጤቶችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ በልማት ሠራተኛ የሚደገፍ የግብርና ኤክስቴንሽን እና ምርምር ሥርዓትን መዘርጋት

ለ፡ የማምረቻ ማዕከላትን እና ገበያን በማቀናጀት ክልሎች ውስጥ እና በክልሎች መካከል የእሴት ሰንሰለት ለመፍጠር የግብርና ልማት ቀጠናዎችን የመለየት እና ወደሥራ የመግባት

ሐ፡ ትርፋማ የሆኑ ሰብሎችን በማምረት እና ወደውጪ በሰፊው በመላክ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር እና የአገሪቱን የውጪ ንግድ ሚዛን ማስተካከል

መ፡ ለምግብ እጥረት  ሁልጊዜ ተጋላጭ የሆኑ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ህዝቦችን ሥጋት ለመቀነስ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ማድረግ። ከተወሰዱት ርምጃዎች መካከል የሰብል ምርት እና የምግብ አቅርቦት ከዓመት ዓመት የተስተካከለ እንዲሆን መስኖ በሰፊው መጠቀም እና ውሃን በአግባቡ መያዝ፣ የሚመረቱ የሰብል ዓይነቶችን መጨመር፣ ገበያን፣ ትራንስፖርትን እና መረጃን በተሻለ ሁኔታ ማቀናጀት፣ ከግብርና ውጪ ያሉ የሥራ ዕድሎችን እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ እድሎችን ማስፋፋት፣ የብድር ገበያዎችን ማሻሻል፣ ሰብል እና የአየር ጠባይን መሰረት ያደረገ የመድህን ሽፋን ሙከራ የመሳሰሉት ናቸው።

12) ከግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ከመነጩ ብዙ ፖሊሲዎች እና ርምጃዎች መካከል ጥቂቶቹ ዘለቄታዊ ልማት (እድገት) እና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም (ከ 1994 እስከ 1997 ዓም)፣ የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ (1995 ዓም)፣ ድህነትን ለማጥፋት ፈጣን እና ዘለቄታ ያለው ልማት እቅድ (ከ 1994 እሰከ 1997 ዓም)፣ የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ ፖሊሲ እና ኢንቨስትመንት የአስር ዓመት ፍኖተ-ካርታ (ከ 2002 እስከ 2012 ዓም)፣ የአምስት ዓመት የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ከ 2002 እስከ 2007 ዓም) እና የግብርናው ዘርፍ እድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ከ 2007 እስከ 2012 ዓም) ናቸው።

13) ከእነዚህ ስትራቴጂዎች መካከል በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ አገሪቱ ማሳካት የምትፈልገውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት በዝርዝር የያዘ ነው። የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት አጠቃላይ ዓላማ ገበያ-መር የሆነ ኢኮኖሚ በመገንባት (ሀ) ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ፣ (ለ) ከምግብ እህል ርዳታ መላቀቅ እና (ሐ) ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ ነው (MoFED 2003)። ይህን የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ዓላማ ለማሳካት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በዋናነት ግብርናን ማዕከል ያደረገ የገጠር እድገት ፕሮግራም ተግባራዊ አድርጓል። ሆኖም ግን ፕሮግራሙ በሌሎች ዘርፎች እድገት መደገፍ እንደነበረበት በግልጽ ታይቷል።

14) በ 1995 ዓም የወጣውን የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ በመመርመር እና የፖሊሲ ክፍተት ጥናቶችን በማድረግ እንደታወቀው ምርት እና ምርታማነትን ለመጨመር ብቻ የተደረገው ጥረት የድህረ-ምርት አያያዝ ተግባራት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ትኩረት እንዳያገኙ አድርጓል። ሆኖም ግን የተለያዩ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ ሁኔታ ባልተሻሻለ የቅድመ-ምርት ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በተፈጥሮ አደጋዎች የሚደርሰው ብክነት ሊመረት የሚችለውን ጠቅላላ የምርት መጠን ከ 15 እስከ 25 በመቶ ይሆናል። እንዲሁም ባልተሻሻለ የአጨዳ፣ የማጓጓዣ፣ አከመቻቸት እና የማከማቻ ተባዮች ቁጥጥር ሥርዓት ምክንያት በድህረ-ምርት ጊዜ የሚደርሰው ብክነት መጠን ደግሞ ጠቅላላ የተመረተውን ምርት 30 በመቶ ይሆናል (MoARD 2010)። ይህን የድህረ-ምርት ብክነት መጠን ወደ 10 በመቶ ለመቀነስ በ 2002 ዓም ቅድሚያ ከተሰጡት ጉዳዮች መካከል አንዱ ነበር (MoARD 2010)።

15) በ 2006 ዓም የአፍሪካ አገራት መሪዎች ባፀደቁት የማላቦ ስምምነት መሰረት አሁን በአህጉሪቱ ያለውን የድህረ-ምርት ብክነት በ 2017 ዓም በግማሽ ለመቀነስ እና በዚሁ ዓመት ረሀብን ከአህጉሪቱ ለማጥፋት ቃል ገብተዋል (AUC 2014)። በተመሳሳይ መልኩ በዓለም ደረጃም የዘለቄታዊ ልማት ግብ 12 (ፍጆታን እና ማምረትን ዘለቄታ ባለው ሁኔታ ማረጋገጥ) በተጠቃሚዎች እና በችርቻሮ ደረጃ በግለሰብ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት እንዲሁም በማምረት እና አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በድህረ-ምርት ጊዜ የሚደርሰውን ብክነት ጨምሮ በ 2022 ዓም በግማሽ ለመቀነስ ጥሪ አቅርቧል (UN Economic & Social Council: Statistical Commission, 2016)። በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ከ 2007 እስከ 2012 ዓም) የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም አሁን ያለውን ከ 15% እስከ 25% የምግብ ብክነት መጠን በፕሮግራሙ መጨረሻ በ 2012 ዓም ወደ 5% ለመቀነስ የተለጠጠ ግብ አስቀምጧል። ይህንን ግብ ለማሳካት የሚደረገውን ሂደት ለማገዝ ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂን መቅረፅ አስፈልጓል (MoA, 2015)።

16) በተጨማሪም የቡድን 20 የ2007 ዓም የምግብ ዋስትና እና ዘለቄታዊ የምግብ ሥርዓት የድርጊት መርሃ ግብር እንደሚያሳየው ለሰውልጅ ፍጆታ ከተመረተው ምርት ውስጥ ሲሶው (አንድ ሦስተኛው) ይባክናል ወይም ይበላሻል። የምግብ ብክነት ወይም ብልሽት በምግብ ዋስትና፣ በአልሚ-ምግብ አቅርቦት፣ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እና አካባቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው (G20, 2015)። ስለሆነም የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ የምግብ ዋስትናን፣ የአልሚ-ምግብ አቅርቦትን እና ዘለቄታዊ የስነምግብ ሥርዓትን በዓለም ደረጃ ለማሻሻል ይረዳል።

17) በእነዚህ ምክንያቶች እና በ1995 ዓም የወጣውን የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እና የሁለተኛውን የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ከ 2007 እስከ 2012 ዓም) ሥራላይ ለማዋል ይህ ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ወጥቷል።

# ክፍል ፪

# የድህረ-ምርት ብክነት

## ዋና ዋና ትርጓሜዎች

18) **የምግብ ዋስትና**
እንደ የተባበሩት መንግስታት ኮሚቴ አተረጓጎም የምግብ ዋስትና ማለት ሁሉም ሰው በማንኛውም ጊዜ ንቁ እና ጤናማ ህይወት ለመምራት የሚያስፈልገውን በቂ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አልሚ የሆነ ምግብ አካልዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ክልከላ ሳይኖርበት የምግብ ፍላጎቱን እና ምርጫውን አሟልቶ ማግኘት ሲችል የምግብ ዋስትና ይባላል።

19) **የምግብ ብክነት**
የምግብ ብክነት ማለት ሰው የሚመገበውን ነገር በሚያቀርብበት የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርስ የምግብ መጠን መቀነስ ሲሆን ብክነቱ በምግብ አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ በማምረት፣ በድህረ-ምርት እና በማቀነባበር ደረጃ ላይ ይከሰታል ወይም ይፈጠራል (FAO 2011, p. 3)። ከቸርቻሪው እና ከተጠቃሚው ባህሪ ጋር ተያይዞ በምግብ ሰንሰለት ጫፍ በተለይም በችርቻሮ እና በመጨረሻ ገበታ ከቀረበ በኋላ የሚከሰት የምግብ ብክነት ምግብ ማበላሸት ይባላል (Parfitt et al., 2010 as quoted by FAO 2011, p. 3)።

20) **የድህረ-ምርት ምግብ ብክነት**
የድህረ-ምርት ምግብ ብክነት ማለት በምግብ ክምችት የሚደርስ የመጠን እና/ወይም የጥራት መቀነስን ሲያመለክት የማምረት፣ የአጨዳ፣ የክምችት፣ የማሰባሰብ፣ የማጓጓዝ፣ የማቀናበር፣ የስርጭት፣ የአጠቃቀም እና ሌሎች ሂደቶችን በያዘ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የሚከሰት ሊለካ የሚችል የምግብ የመጠን እና የጥራት መቀነስ ተብሎ ይተረጎማል (De Lucia and Assennato, 1994; Hodges, Buzby and Bennett, 2011, as quoted by Aulakh *et al*) (FAO 2014)። ይህም በመሆኑ ድህረ-ምርት ባለብዙ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ዘርፈብዙ መስኮችን እንደ የግብርና ዘርፍ፣ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎችን፣ ስርጭትን፣ የማምረትን (ማኑፋክቸሪንግ) ዘርፍ እና ሌሎችንም ይጨምራል።

21) **የምግብ መጠን መቀነስ**
ሰው ሊበላው በሚችለው የምግብ ክምችት የመጠን መቀነስ ጋር የተያያዘ ሲሆን እህሉ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሳይውል በተለያየ መንገድ እንደ ፍሰት፣ በተበይ መበላት፣ በሙቀት፣ በርጥበት፣ ኬሚካላዊ ለውጦች እና በመሳሰሉት ጉዳቶች ከድህረ-ምርት አቅርቦት በአካል ሲወግድ የሚፈጠር ክስተት ነው (FAO, 1980)። የብክነቱ መጠን በብልሽት ምክንያት ሊበላ የማይችል ወይም ለሰው ምግብነት ወይም ለእንስሳት መኖነት የተቀመጠ ደረጃ ባለማሟላት የሚወድቅ የእህል መጠን ይሆናል።

22) **የጥራት ብክነት**
የጥራት ብክነት የሚባለው ደግሞ የእህል የጥራት ባህሪያት ወይም መገለጫዎች ጠፍተው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የአልሚ ምግብነት ዋጋ ሲቀንስ ነው። የጥራት ብክነት የሚከሰተው እህል በተባዮች፣ በቅንቅን፣ በዘረ-አይጦች እና በወፎች ሲወረር ወይም በአያያዝ ጉድለት በእህሉ ላይ በሚደርስ አካላዊ ወይም ኬሚካላዊ ለውጦች ምክንያት በቅባት፣ በሀይል ሰጪ (ካርቦ ሀይድሬትስ) እና በገንቢዎች (ፕሮቲን) ላይ በሚደርስ ለውጥ፤ በሻጋታ-መርዝ (ማይኮቶክሲን)፣ በፀረ-ተባይ ቅሪት በመመረዝ፣ ከተቆራረጠ የተባይ አካል ወይም ከወፎች እና ከዘረ-አይጦች ጽድጃ (እዳሪ) እና የሞተ አካል ጋር ሲቀላቀል ነው። በጥራት ብክነት ምክንያት ምግብ ለሰው ምግብነት መዋል ሳይችል ቀርቶ ሲወገድ ለምግብ ብክነት አስተዋፅዖ

ያደርጋል። ብዙ ጊዜ የጥራት ብክነት ከፍተኛ ከሆነ የአልሚ ምግብነት መቀነስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በማህበረሰቡ ላይ የጤና ጉዳት ሊያስከትል እና የንጥረምግብ አቅርቦት ደረጃን ሊቀንስ ይችላል (FAO 2014)።

23) **የአቅርቦት ሰንሰለት**

አንድን ምርት ወይም አገልግሎትን ከአቅራቢው ወደ ተጠቃሚው በማስተላለፍ በተሳሰሩ በሰዎች፣ በአደረጃጀቶች እና ክንውኖች ወይም ተግባራት መካከል ያለ የመረጃ እና የሀብት መፍሰሻ ሥርዓት ነው።

24) **የእሴት ሰንሰለት**

አንድ ድርጅት ምርት ለማምረት በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚያከናውናቸው ልዩ ተግባራት ወይም በአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ምርትን ለገበያ ለማቅረብ የሚፈጽማቸው ተግባራት ስብስብ ነው።

25) **እሴት መጨመር**

ጥሬ-እቃን በጊዜ፣ በቦታ እና /ወይም የአገልግሎት ለውጥ እንዲጨምር በማድረግ ቅርጹን እና ይዘቱን በመለወጥ የተጠቃሚውን ፍላጎት ወይም ምርጫ የሚያሟላ ከፍተኛ ጥራት ያለው ያለቀለት ምርት የማምረት ሂደት ነው።

26) **የድህረ-ምርት ሥርዓት**

ከአጨዳ ቦታ እና ስዓት ጀምሮ ለጥቅም (ለገበታ) እስከ ሚቀርብበት ቦታ እና ስዓት ድረስ ብክነትን ቀንሶ፣ ውጤታማነትን አብዝቶ እና በሥርዓቱ ውስጥ ላሉ ተሳታፊዎች ሁሉ ከፍተኛ ጥቅም በማስገኘት እህል የማቅረብ ሂደትን ያጠቃልላል (Grolleaud 2002)።

27) **የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ**[1]

የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ ዘርፈ-ብዙ ሙያን /ሳይንስን/ እና ቴክኒክን በመጠቀም የግብርና ምርትን ከአጨዳ በኋላ በመጠበቅ፣ በማቆየት፣ በማቀነባበር፣ በማሸግ፣ በማሰራጨት፣ ጥራትን በመቆጣጠር ወይም በማሻሻል፣ በመሸጥ እና በመጠቀም የሰውን የምግብ እና የንጥረነገሮችን ፍላጎት ማሟለት ነው። ይህ ቴክኖሎጂ ከማህበረሰቡ ፍላጎት ጋር ተጣጥሞ በማደግ የግብርና እድገትን ማነሳሳት፣ የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ፣ የአልሚምግብ አቅርቦትን ማሻሻል እና ምርት ላይ እሴት መጨመርን ማስቻል አለበት። በእንዲህ ዓይነት ሂደት ውስጥ ቴክኖሎጂው የሥራ እድል መፍጠር ፣ ድህነትን መቀነስ እና ከግብርና ጋር ግንኙነት ያላቸውን የኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት ማነቃቃት አለበት። የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ የማመንጨት ሂደት እና ስኬታማ ትግበራ ሳይንሳዊ ፈጠራን፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራን እና ንግድ ተኮር ፈጠራን ስለሚፈልግ የብዙ ሳይንስ ዘርፎችን ቅንጅት የያዘ እና ከብዙ አቅጣጫዎች የተቃኘ መሆን አለበት። በየጊዜው እድገት የሚጠይቀውን ፍላጎት ለማሟላት ተቋማትም የተቀናጀ ምርምር እና ልማት ለማከናወን በሚያስችል ደረጃ ላይ መሆን አለባቸው።

## የድህረ ምርት ሥርዓት

28) በጠቋሚ 1 ውስጥ ዋና ዋና የድህረ-ምርት ሥርዓት ተግባራት ተዘርዝረዋል። የድህረ-ምርት ብክነት ችግርን ለመፍታት በእያንዳንዱ የግብርና አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ሂደቶችን መገምገም ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ሁኔታ ሁለት ዓይነት የእህል አቅርቦት ሰንሰለቶች አሉ። እነሱም (ሀ) እህልን ለአገር ውስጥ ፍጆታ እና (ለ) እህልን ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡ ሰንሰለቶች ናቸው። እህልን ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚያቀርበው ሰንሰለት ዓይነትን እና ደረጃን፣

[1] http://amickau.nic.in/index.php?option=com_content&task=view&id=53&Itemid=87

ማሸግን፣ ማጓጓዝን፣ የክፍያ ሥርዓትን፣ የገበያ መረጃን እና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የተዋንያኑ ሚና እና ሀላፊነት በግልጽ የተለየ አይደለም። ይህ ሰንሰለት በአርሶ አደሩ እና በተጠቃሚው መካከል ብዙ ነጋዴዎችን የያዘ በመሆኑ አርሶ አደሩ የሚያገኘው ትርፍ በአጠቃላይ ዝቅተኛ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ እህልን ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚያቀርበው ሰንሰለት በሥዕል 1 ተመልክቷል።




ሥዕል 3: ኢትዮጵያ ውስጥ ለአገር-ውስጥ ፍጆታ የሚውል ምርት የአቅርቦት ወይም የገበያ ሰንሰለት ሥዕላዊ መግለጫ (ግንቦት 2008)

ጠቋሚ 2: **ዋና ዋና የድህረ-ምርት ሥርዓት ተግባራት**

**ዋና ዋና የድህረ-ምርት ሥርዓት ተግባራት**

***አጨዳ:*** የአጨዳ ጊዜ በእህሉ የብስለት ወይም የድርቀት ደረጃ ይወሰናል። በብርዕ፣ አገዳ እና ጥራጥሬ ሰብሎች የአገዳ፣ የዛላ፣ የቆባ (እንቡጥ) እና ፍሬ መብሰልን ወይም መድረስን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ተከታይ ተግባራት በተለይም እንደ ማከማቸት እና ማቆየት ላይ ተፅዕኖ ስላላቸው ነው።

***ከአጨዳ በፊት ማድረቅ:*** የብርዕ፣ አገዳ እና ጥራጥሬ ሰብሎችን ከአጨዳ በፊት ማሳ ላይ ማድረቅ ጠቃሚ ቢሆንም ለተራዘመ ጊዜ እንዲደርቁ ማድረግ ሰብሉን ለወፎች፣ ዘረ-አይጦች፣ ተባዮች እንዲሁም ከአየር ጠባይ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ጥቃት ተጋላጭነትን ይጨምራል። በሌላ መልኩ ደግሞ እህሉ ሳይደርቅ ማጨድ ነዶው እንዲበሰብስ ከማድረጉ በተጨማሪ ለሻጋታ እድገት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

***ማጓጓዝ:*** ደርሶ የታጨደ ሰብል ወደ መከመሪያ ወይም አውድማ ቦታ ሲጓጓዝ በተለያየ መንገድ ብክነት እንዳይደርስበት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም ከመሰብሰብ እና ከማጓጓዝ በፊት የሚከመርበትን ወይም የሚወቃበትን ቦታ ሁኔት እሳቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

***ከአጨዳ በኋላ ማድረቅ*** : ዛላ እና ፍሬ ሙሉ ለሙሉ ለመድረቅ የሚወስድባቸው ጊዜ በአየር ጠባይ እና በከባቢ-አየር ሁኔታ ይወሰናል። ማማ በመሳሰሉ ማድረቂያዎች እና አውድማ ላይ ወይም ሌሎች የመውቂያ ቦታዎች ላይ የተቀመጠ ነዶ ለቤት እንስሳት፣ ለወፎች፣ ለዘረ-አይጦች ወዘተ ጥቃት የተጋለጠ ነው። እነዚህ እንስሳት በቀጥታ ከሚያደርሱት ጉዳት በተጨማሪ በሚጥሉት ጽድጃ (እዳሪ) እና በሚሸኑት ሽንት ከፍ ያለ ብክለትን ያስከትላሉ። በተቃራኒው ደግሞ እህል ሳይደርቅ ታጭዶ ከተከመረ በርጥበት ምክንያት ሊሻግት ይችላል።

እህሉ በጣም ከደረቀ ፍሬው በውቂያ ጊዜ ወይም ከውቂያ በኋላ ሊሰባበር ወይም ሊሰነጠቅ ይችላል። እንዲሁም ሩዝ የመሳሰሉ ሰብሎች ሲሸከሸኩ (በሙቀጫ በቀስታ ሲወቀጡ) በከፍተኛ ደረጃ ይሰባበራሉ። የተሰባበረ የእህል ፍሬ በማዝራት ጊዜ በንፋስ ከመወሰዱ በተጨማሪ ለተባይ ጥቃት የተጋለጠ ይሆናል። በጣም የደረቀ እህል ቀላል ክብደት አለው።

***ውቂያ:*** በደንብ ያልደረቀ ነዶ ለመውቃት አስቸጋሪ ነው። ብዙ ርጥበት ያለው ነዶ ከተወቃና እህሉ ወዲያውኑ ከተከማቸ ለጥቃቅን-ዘአካል ጥቃት ከመጋለጡ በተጨማሪ የመከማቻ ጊዜው አጭር ይሆናል።

***ማከማቸት:*** እህልን በተሳካ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ለማከማቸት ጥሩ የማከማቻ እቃ፣ ንጽህና መጠበቅ እና መደበኛ የሆነ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል። ዝግ በሆኑ የማከማቻ ቦታዎች (ጎተራ፣ ጎታ፣ መጋዘን) ንጽህናን፣ ሙቀትን እና የአየር ርጥበትን መቆጣጠር ተገቢ ነው። በተባዮች እና በሻጋታዎች የሚደርስ ጉዳት ከእህሉ አልፎ የማከማቻ እቃውን ስለሚጎዳ የምግብ እህል ላይ የመጠን እና የጥራት ብክነት ያስከትላል።

***ማቀነባበር:*** ከልክ በላይ መውቃት እና መሸክሸክ (በሙቀጫ በቀስታ መውቀጥ) እንደ ሩዝ በመሳሰሉ እህሎች ላይ የፍሬ መሰባበር እና መሰንጠቅን ያስከትላል። እንዲህ ዓይነት እህል ዋጋ የለሽ ከመሆኑ በተጨማሪ ለተባይ እና ሻጋታ ጥቃት የተጋለጠ ነው።

***ሽያጭ:*** መሸጥ የድህረ-ምርት የመጨረሻው እና ወሳኙ ደረጃ ቢሆንም እንደ ሁኔታው በግብርና-ምግብ-ሰንሰለት ውስጥ በማንኛውም ደረጃ ሊከናወን ይችላል። በተጨማሪም ሰንሰለቱን ከሚያስተሳስረው ትራንስፖርት ጋረ በጥብቅ የተሳሰረ ነው።

***ምንጭ*** Grolleaud, 2002

29) ሁለተኛው ሰንሰለት ማለትም እህልን ለውጭ ገበያ የሚያቀርበው ሰንሰለት ዓይነትን እና ደረጃን፣ ማሸግን፣ ማጓጓዝን፣ የክፍያ ሥርዓትን፣ የገበያ መረጃን እና ሌሎችን ጉዳዮች በተመለከተ የተዋንያኑ ሚና እና ሀላፊነት በግልጽ የተለየ ከመሆኑ በተጨማሪ በተገቢ ሁኔታ የተዋቀረ ነው (ሥዕል 2)።

30) ሆኖም ግን በእነዚህ የተያያዙ ሰንሰለቶች ውስጥ የድህረ-ምርት ብክነት በተለያየ ደረጃ እና መጠን ይከሰታል።

**ሥዕል 4:	ከኢትዮጵያ ወደውጭ የሚላኩ ምርቶች የገበያ ሰንሰለት**




*ምንጭ:  በመስክ በተደረገ ቃለ-መጠይቅ የተገኘ (ግንቦት 2008 ዓም)*

## በመስክ ምልከታው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

31) ስትራቴጂውን ለመቅረጽ በተደረገው ቅድመ-የመስክ ቅኝት በግብርና ምርት የአቅርቦት ሰንሰለት ወይም የገበያ ሰንሰለት ውስጥ በሚከሰት የድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ በርካታ ቁልፍ ጉዳዮች ተነቅሰው ወተዋል፡፡ እነሱም ድህረ-ምርትን ያማከለ ግንዛቤ መፍጠር እና መረጃ ልውውጥ፣ በድህረ-ምርት ዙሪያ የፖሊሲ አቅጣጫ አለመኖር፣ የክህሎት፣ የስልጠና እና የሰው ልማት ክፍተት፣ በድህረ-ምርት ብክነት ላይ በሚሰሩ ባለድርሻ አካላት (ተዋናዮች) መካከል ቅንጅት አለመኖር፣ አግባብ ያለው የድህረ-ምርት ምርምር እና ልማት አለመኖር፣ የገበያ፣ የቴክኖሎጂ እና የሜካናይዜሽን ጉዳዮች፣ አጠቃላይ አገራዊ (ማክሮ) ኢኮኖሚ ሁኔታ፣ ተቋማዊ እና ድርጅታዊ አወቃቀር፣ የስርጠት/ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የገበያ መሰረተ-ልማቶች ማለትም የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ፣ የገንዘብ አቅርቦት እና ኢንቨስትመንት፣ ግብርናዊ-ቢዝነስ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ጉዳዮቹ በሠንጠረዥ 1 በአጭሩ ተብራርተዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 2: በመስክ ምልከታ የተለዩ የድህረ-ምርት አያያዝ ቁልፍ ጉዳዮች*

| ቁልፍ ጉዳይ | ዋና ዋና ምሳሌዎች |
|---|---|
| ግንዛቤ መፍጠር እና መረጃ ልውውጥ | 1. የድህረ-ምርት ብክነት የግንዛቤ ጉዳይ በመሆኑ የግንዛቤ አለመኖር ሥራው እንዴት እንደሚሰራ ተፅዕኖ ያደርጋል<br>2. የድህረ-ምርት ብክነትን ተከትለው ስለሚመጡ ጉዳቶች ወይም ተፅዕኖዎች የእውቀት ውስንነት መኖር<br>3. ብዙ ጊዜ የድህረ-ምርት ብክነትን በተሳሳተ መንገድ መረዳት፣ መሰረተ-ሀሳብን መገንዘብ አለመቻል |
| ፖሊሲ | 1. እስከ ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም ድረስ ለድህረ-ምርት ብክነት ትኩረት አልተሰጠም ነበር<br>2. የድህረ-ምርት ብክነት በኢኮኖሚ እና በምግብ ዋስትና ላይ ያለውን ተፅዕኖ አለመገንዘብ<br>3. የድህረ-ምርት ብክነትን ከጤና እና ሌሎች ጉዳዮች ጋር አስተሳስሮ ማየት አለመቻል<br>4. በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ ያሉ የቁጥጥር ማዕቀፎችን የማስፈጸም አቅም ውስንነት |
| የክህሎት፣ የስልጠና እና የሰው ልማት ክፍተት | 1. የሚሰጡ ስልጠናዎችን በድህረ-ምርት ብክነት ሥርዓት-ትምህርት ማጠናከር ማስፈለጉ<br>2. በድህረ-ምርት ብክነት ለሰለጠኑ ባለሙያዎች የሥራ እድል አለመኖር<br>3. ለአርሶ አደሮች እና ለልማት ሠራተኞች ስለ ድህረ-ምርት ብክነት ስልጠና አለመስጠት<br>4. በድህረ-ምርት ብክነት ላይ ለሚሰሩ ተቋማት የአቅም ግንባታ አለማድረግ<br>5. ማምረትን ብቻ ትኩረት ያደረገ ቴክኖሎጂ እና የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ሥራ መስራት |
| የድህረ-ምርት ምርምር እና ልማት | 1. በድህረ-ምርት ብክነት ላይ የሚሰሩ ምርምሮች የተበጣጠሱ እና ያልተቀናጁ መሆን<br>2. ስለድህረ-ምርት የብክነት መጠን ያለው መረጃ በጥናት የተደገፈ አለመሆን |
| ገበያ እና የገበያ መሰረተ-ልማቶች | 1. ለአገር ውስጥ ፍጆታ ለሚውሉ ሸቀጦች ወጥነት ያለው እና የተቀናጀ ገበያ አለመኖር<br>2. ከደረጃ እና ዓይነት፣ ከዋጋ አለመለያየት (ማለትም ጥራት ላለው እና ለሌለው ምርት እኩል ዋጋ መስጠት)፣ ከማሸግ፣ ከመጋዘን አያያዝ ወዘተ ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶች<br>3. ለአገር ውስጥ ፍጆታ ለሚውሉ ሸቀጦች የንግድ ወይም የገበያ ቁጥጥር አለመኖር<br>4. ውስንነት ያለባቸው ቤተ-ሙከራዎች፣ የመንገድ እና የትራንስፖርት መሰረተ-ልማቶች፣ አገልግሎት (ለምሳሌ የሀይል አቅርቦት) ሰጭዎች፣ |

| ቁልፍ ጉዳይ | ዋና ዋና ምሳሌዎች |
|---|---|
| | ማጨጃዎች፣ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምርቶች የሚከማቹባቸው ቦታዎች እና የምርት አያያዝ (ምሳሌ የአስተጣጠን ዘዴ) ወዘተ |
| ቴክኖሎጂ እና ሜካናይዜሽን | 1. ተገቢ እና ተደራሽ የሆኑ የድህረ-ምርት ብክነትን የሚቀንሱ ቴክኖሎጂዎችን መሰረት ያላደረገ እና ደካማ የሆነ የድህረ-ምርት አያያዝ<br>1. ውድ ቴክኖሎጂዎች፣ የጥገና አገልግሎት አለመኖር እና ሲኖርም ውድ መሆን፣ ለማሽነሪዎች የሥራ ብቃት ደረጃ እና ቁጥጥር አለመኖር<br>2. ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ እና ጊዜ ቆጣቢ የማምረቻ እና የማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂዎች እጥረት |
| አጠቃላይ አገራዊ (ማክሮ) ኢኮኖሚ | 1. ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ የእርሻ መሣሪያዎች እና አቅርቦቶች ላይ የሚጣል ከፍተኛ ግብር<br>2. በጉልበት ዋጋ ላይ ቁጥጥር አለመኖር |
| ተቋማዊ እና ድርጅታዊ አወቃቀር | 1. በድህረ-ምርት ብክነት ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶ አለመስራት<br>2. በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ ለሚሰሩ የመልካም ተሞክሮ እና የእውቀት-የምክክር መድረኮች፣ ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለምርምር ተቋማት፣ ለስልጠና ማዕከላት ወዘተ ድጋፍ አለማድረግ<br>3. ስለድህረ-ምርት ብክነት በቂ ክህሎት፣ አቅም እና የሰለጠነ የሰው ሀይል በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር አለመኖር |
| ኢንቨስትመንት እና የገንዘብ አቅርቦት | 1. በግብርና ምርት የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የገንዘብ አቅርቦት ድጋፍ አለመኖር<br>2. በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ ለሚሰሩ ሥራዎች በቂ በጀት አለመስጠት<br>3. በድህረ-ምርት ብክነት ዘርፍ እንዲሰማሩ ለግል ባለሀብቶች ማበረታቻ አለመኖር |
| ግብርናዊ-ቢዝነስ/ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ | 1. የግል ባለሀብቶች በግብዓት ማምረት እና ስርጭት አለመሳተፍ<br>2. ጆንያ (ከረጢት)፣ መፈልፈያ፣ መውቂያ ወዘተ ለሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ አለመስጠት<br>3. የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ ገጠር ውስጥ ለሚሰሩ አነስተኛ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች ድጋፍ አለመስጠት<br>4. የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ በመሆናቸው አብዛኛው እህል ብዙ እሴት ሳይጨመርበት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ከ 80% እስከ 90% የሚሆነው ምርት መሠረታዊ ቅንብር ብቻ ተደርጎበት ለምግብነት ይውላል፡፡ |

# የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ መሠረቶች

## የኢትዮጵያ ግብርና አጠቃላይ ዳሰሳ

32) እንደ የተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ክፍል የህዝብ ንዑስ-ክፍል ግምት በጥር 2009 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ወደ አንድ መቶ ሚሊዮን ይጠጋ ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ከናይጄሪያ በመቀጠል በአፍሪካ ሁለተኛ ደረጃ ትይዛለች፡፡ በ 2008 ዓም የህዝቡ ቁጥር 94.1 ሚሊዮን እንደነበር የዓለም ባንክ ማስረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ ሕዝብ ውስጥ ከ 85% በላይ የሚሆነው በገጠር የሚኖር እና ኑሮውን ግብርና ላይ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች የብርዕ እና የአገዳ (ጤፍ፣ ስንዴ፣ ማሽላ፣ በቆሎ)፣ ጥራጥሬ እና የቅባት እህሎች ናቸው፡፡

33) ከጠቅላላው አገራዊ ምርት ውስጥ ግማሽ ያህሉ፣ 85% የሥራ እድል፣ 70% የሚሆነውን የአነስተኛ እና መካከለኛ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ-እቃ ፍላጎት እና 90% የሚሆነውን የውጭ (ኤክስፖርት) ገበያ ከግብርናው ዘርፍ በሚገኝ ምርት የሚሸፈን ድርሻ ነው (Global Growing Casebook, 2012)፡፡ ይህም ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ-አጥንት እንደሆነ ያሳያል፡፡ የግብርናው ዘርፍ በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች

ላይ ባለው ከፍተኛ ተፅዕኖ ምክንያት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ቅድሚያ የሰጠው ዘርፍ ነው።

34) ሲሶ (አንድ ሦስተኛ) የሚሆነው የገጠር አባወራ (ጢስ) የመሬት ይዞታ ግማሽ ሄክታር ብቻ ነው ተብሎ የሚገመት ቢሆንም (MoFED, 2003; MoARD, 2010) በአንዳንድ ጤፍ እና ስንዴ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የአንድ አባወራ (ጢስ) የመሬት ይዞታ እስከ ሦስት ሄክታር ሊደርስ ይችላል። የኢትዮጵያ ግብርና ዓይነተኛ ከእጅ-ወደ-አፍ ግብርና ሲሆን 95 በመቶ በሚሆነው የእርሻ መሬት ላይ ይከናወናል፤ ከጠቅላላው የእህል ምርት ውስጥ 90% የሚሆነውን እና 98% የቡና ምርት ከዚሁ ዘርፍ ይገኛል (Global Growing Casebook, 2012)።

35) የዚህ አነስተኛ ከእጅ-ወደ-አፍ ግብርና ምርታማነት ዝቅተኛ ሲሆን ዋና ዋና ምክንያቶችም የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት፣ የገንዘብ አቅርቦት/ አገልግሎት፣ የተሻሻሉ የማምረቻ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ የመስኖ እና የገበያ ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን ናቸው። ሌላው ምክንያት ደግሞ እውቀትን መሠረት ባላደረገ የመሬት አጠቃቀም ምክንያት አፈሩ በከፍተኛ ደረጃ መሸርሸሩ ነው (MoARD, 2010)። ትርፍ ምርት በሚኖርበት ጊዜ አርሶ አደሮች የገበያ ችግር ይገጥማቸዋል (MoARD, 2010)። ይህም የሆነው አገሪቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የትራንስፖርት መሰረተ-ልማት ስላላት፣ በቂ የማከማቻ ቴክኖሎጂ አለመኖር እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች አለመስፋፋት በመሳሰሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው።

## የድህረ-ምርት ብክነት እንደ ዋና ተግዳሮት

36) እንደ ግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የኢትዮጵያ ግብርና አጠቃላይ ምርት የአገሪቱን የምግብ ፍላጎት ስለማይሸፍን ወደ ግማሽ የሚጠጋው ሕዝብ ገቢው ከድህነት ወለል በታች ሆኖ በዝቅተኛ ደረጃ ይኖራል (MoARD, 2010)። በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ ተመጣጣኝ የሆነ ገቢ ዘለቄታ ባለው ሁኔታ ሊሰጥ ባለመቻሉ ግብርናን መሰረት ያደረገው አብዛኛው የገጠር ሕዝብ የምግብ ዋስትናውን እንኳ ሳያረጋግጥ በድህነት ይኖራል (MoARD, 2010)። ይህም የሆነበት ምክንያት ቁጥሩ በአርባ ዓመት (ከ1954/55 እስከ 1994/95) ጊዜ ውስጥ ከ38 ሚሊዮን በላይ (በተመሳሳይ ጊዜ የከተማው ሕዝብ በ8 ሚሊዮን ብቻ ቁጥሩ ጨምሯል) የጨመረው የገጠሩ ህዝብ የኑሮ መሠረት የሆነው ግብርና ለረጅም ጊዜ ያለ ትክክለኛ የእድገት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ሲሰራ በመቆየቱ ነው (Gebre-Selassie, 2003)። ቀደም ብለው የነበሩ ፖሊሲዎች የኢኮኖሚውን በተለይም የግብርናውን ዘርፍ መዋቅራዊ ችግር ያላካተቱ ነበሩ (MoARD, 2010)። ከመዋቅራዊ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ እና ለረጅም ጊዜ ትኩረት የተነፈገው ዘርፍ ነገር ግን ጉልህ አስተዋፅዖ ማበርከት የሚችለው የድህረ-ምርት ብክነት ነው።

37) በ 1986 ዓም ግብርና-መር የኢንዱስትሪ ልማት (እድገት) ፕሮግራም ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ የወጡ ግብርና ላይ ያተኮሩ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ስትራቴጂዎች እንደሚያሳዩት የኢትዮጵያ መንግስት ትኩረት ያደረገው እና ቅድሚያ የሰጠው ምርት እና ምርታማነትን መጨመር ሲሆን የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ግን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የተተወ ነው።

38) ቀደም ያለ የአፍሪካዊያን የድህረ-ምርት ብክነት የመረጃ ሥርዓት መረጃ በጤፍ ምርት 12.3%፣ በማሽላ ምርት 11.6%፣ በስንዴ ምርት 9.9% እና በበቆሎ ምርት 16.8% የድህረ-ምርት ብክነት ሊደርስ እንደሚችል ያሳያል። በተባበሩት መንግስታት የዓለም የምግብ እና እርሻ ድርጅት እና የዓለም ምግብ ፕሮግራም የሰብል እና የምግብ ዋስትና ግምገማ ተልዕኮ ሪፖርት እንደሚያሳየው በ2002 ዓም ብቻ አጠቃላይ የድህረ-ምርት ብክነት 2.04 ሚሊዮን ቶን ነበር። በተቃራኒው ደግሞ አገሪቱ አጠቃላይ የምግብ ፍላጎት ሚዛኗን ለማስተካከል በዛው ዓመት 1.16 ሚሊዮን ቶን እህል ከውጪ ማስገባት እንደነበረባት ይሄው ሪፖርት ያሳያል (US Dept. of State, 2013)። ይህም የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ አገሪቱ ከውጪ የምታስገባውን የምግብ እህል መጠን በመቀነስ የምግብ አቅርቦትን ለማሻሻል እንደሚረዳ ነው።

## የመመሪያ መሠረታዊ ደንቦች

39) ይህ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የተቀረጸው ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች የተቀመጡትን የመመሪያ መሠረታዊ ደንቦች በመከተል ነው።

ሀ፡ የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ በባህሪው የመጠን እና የጥራት ጉዳዮችን ያጣመረ በመሆኑ ብዙ አቅጣጫዎችን እና ብዙ ዘርፎችን ይነካል። በመሆኑም ስትራቴጂ ቀረጻው እና ስትራቴጂውን ሥራላይ ማዋል ሁሉንአቀፍ መሆን ስላለበት እንደ ግብርና፣ ጤና፣ ንግድ፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ ማከማቻዎች እና ትራንስፖርት ዘርፍ ጋር ትብብር ይጠይቃል፤

ለ፡ እንደ ባለብዙ አቅጣጫና እና ባለብዙ-ዘርፍ ጉዳይ የድህረ-ምርት አያያዝ ተግባሮች ቀረጻ እና ሥራላይ ማዋል አሳታፊነትን የሚፈልግ በመሆኑ ከተጠቃሚዎች፣ ከአማካሪዎች፣ ከአሰልጣኞች፣ ከተመራማሪዎች እና ከአስተባባሪዎች ጋር በተለያየ መጠን የማማከር ሥራ ይፈልጋል።

ሐ፡ በመሆኑም እላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ደንቦች ለማሟላት የመስክ ሥራ ግንቦት 2008 ዓም ተከናወነ፡፡ በዚህ የመስክ ሥራ ከተለያዩ ተዋንያን እና የተመረጡ መረጃ ሰጭዎች ጋር በአካል ግንኙነት በማድረግ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ የመነሻ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለአስተያየት እና ለጥያቄ ለብዙ ባለሙያዎች ተሰራጨ፡፡

መ፡ በመነሻ ረቂቁ ላይ የተሰጡ ግብዓቶችን በማካተት የመጀመሪያው ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ከተሰራጨ በኋላ የማረጋገጫ ወርክሾፕ ጥቅምት 2008 ዓም ተደረገ፡፡ ከወርክሾፑ የተገኙትን አስተያየቶች እና ምክሮች በማካተት ይህ የመጨረሻው ረቂቅ ተዘጋጅቶ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የተለያዩ አካላት እንዲያጸድቁት እና ሥራ ላይ እንዲያውሉት ቀርቧል፡፡

40) የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ሥርዓት እና ሂደት እንደ ሰብሉ ዓይነት የተለያየ ቢሆንም ይህ ስትራቴጂ የተዘጋጀው በጥቅሉ ሰብልን ትኩረት በማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም አጠቃላይ መሰረተ-ሀሳቡ እንደ ዘርፉ ዓይነት እና ለአካባቢው በሚስማማ ሁኔታ ሊለወጥ እና ተግባር ላይ ሊውል ይችላል፡፡

# ክፍል ፫

# የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ማዕቀፍ

## የስትራቴጂው ጥቅም

41) ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ እንዲሰጥ የታሰበው ጥቅም በድህረ-ምርት ጊዜ የሚደርስን ብክነት ትርጉም ባለው መልክ ለመቀነስ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ በሁሉም ደረጃ የጋራ የሆኑ ዓላማዎችን መለየት እና የሚወሰዱ ርምጃዎችን መምራት፣ ማስፋፋት እና መደገፍ ነው።

## ራዕይ

42) ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ራዕይ ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተዋፅዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ ነው።

## ግብ

43) ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ግብ የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት መጠን በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር ነው።

## ዓላማዎች

44) ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አጠቃላይ ዓላማ አግባብነት ያለው የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን በማላመድ እና ሥራላይ በማዋል በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መጠን መቀነስ ነው። የስትራቴጂው ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ፡ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ በምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ

ለ፡ የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ቅልጥፍና በማሻሻል የድህረ-ምርት አያያዝ ተግባራትን ማዘመን

ሐ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ የፋይናንስ አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል

መ፡ በሁሉም የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ እሴት የሚጨምሩ አካላትን ዘለቄታ ባለው መንገድ መደገፍ ናቸው።

45) ለድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት አስፈላጊ ከሆኑ ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች መካከል ሥርዓተ-ፆታ፣ ወጣቶች፣ ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ፣ የአካባቢ ነገሮች ወይም ጉዳዮች እና የግብርና መረጃ አያዝ ሲሆኑ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማሳካት በሚሰሩ ተግባራት ሁሉ ግንባር-ቀደም ስፍራ ሊሰጣቸው ይገባል።

## አጠቃላይ የማዕቀፉ ፅንሰ-ሀሳብ

46) ይህ ስትራቴጂ በፊት ሥራላይ የዋሉ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ያካተተ ቢሆንም በአብዛኛው በ 1995 ዓም ከወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እና ከሁለተኛው እድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ (ከ 2007 እስከ 2012) የተወሰደ ነው። የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት አጠቃላይ የማዕቀፉ ፅንሰ-ሀሳብ በሥዕል 3 ላይ ተመልክቷል።




ሥዕል 3፡ ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያየዝ ስትራቴጂ ፅንሰ-ሀሳብ ማዕቀፍ (የውጤት ሰንሰለት)

# ክፍል ፬

# የድህረ-ምርት አያያዝ የትኩረት አቅጣጫዎች

### የአካሄዶች እና የትኩረት አቅጣጫዎች አወቃቀር

47) ከድህረ-ምርት የጽንሰ-ሀሳብ ማዕቀፍ አንፃር ዋና ዋና ዓላማዎችን ለማሳካት እንደ ትኩረት አቅጣጫ ወይም እንደ ቁልፍ ተግዳሮት የተለዩ ጉዳዮች በዚህ ክፍል ተዘርዝረዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ቁልፍ (ወሳኝ) ጉዳይ በርከት ያሉ መሰራት ያለባቸው ተግባሮች የተጠቆሙ ሲሆን እነዚህ መሰራት ያለባቸው ተግባሮች ተለይተው የተቀመጡበት ዓላማ ዋና ዋና የድህረ-ምርት አያያዝ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚሰሩ ሥራዎች ሲታቀዱ መካተት ያለባቸውን ጉዳዮች ለመለየት እንደ መመሪያ እንዲያገለግሉ ነው፡፡

48) ውጤትን መሠረት ያደረገ አካሄድ ሥርዓትን በመጠቀም እያንዳንዱ መሰራት የሚገባው ተግባር ሲፈፀም የሚገኘው ውጤት ከእያንዳንዱ ዝርዝር (ልዩ) ዓላማ ጋር በማዛመድ በውጤት ሥር ተካቷል፡፡ ውጤቱ በአጭር ጊዜ እና በመካከለኛ ጊዜ ሥራው ለሚያመጣቸው ለውጦች ወይም ተፅዕኖዎች መነሻ እና አስተዋፅዖ አበርካች በመሆኑ አጠቃለይ የመጣውን ለውጥ ወይም የግብ ስኬትን ያሳያል፡፡

49) በዚህ አወቃቀር ማሳየት የተፈለገው የተለዩት ቁልፍ ጉዳዮች ወይም ተግዳሮቶች ሙሉ በሙሉ የሚፈቱት ወይም ዓላማ የሚሳካው ከመካከለኛ እስከ ረጅም ጊዜ በሚወስድ የጊዜ-ማዕቀፍ ውስጥ ቢሆንም በእያንዳንዱ መሰራት በሚገባቸው ሥራዎች ሥር የተቀመጡት ተግባራትን ሙሉ ለሙሉ ለማሳካት እና ተግዳሮቶችን ለመፍታት ከአጭር እስከ መካከለኛ ጊዜ በሚፈልግ የጊዜ-ማዕቀፍ ውስጥ መሆኑን ነው፡፡ መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ የተካተተው የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ በጊዜ ያልተገደበ በመሆኑ ወደፊት የሚመጡ አዳዲስ ጉዳዮችን ለማካተት እንደ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

50) በክፍል 4 ሥር ያሉት ንዑስ ክፍሎች በክፍል 3 የተዘረዘረውን እያንዳንዱን ዋና ዓላማ ያንፀባርቃሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ዋና ዓላማ ሰነዱ

ሀ፡ የኢትዮጵያ እህል ስለሚገጥመው ተግዳሮት አጭር ዳሰሳ ይሰጣል

ለ፡ ከተለዩት ተግዳሮቶች በመነሳት በእያንዳንዱ የትኩረት ጉዳይ ላይ መፈጸም ያለባቸውን ሥራዎች ወይም ተግባሮች ይዘረዝራል

ሐ፡ መሰራት ያለባቸውን ጉዳዮች በመለየት በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚፈጸሙ ተግባራት ለተግዳሮቶች መፍትሄ በማምጣት ስላላቸው ተጽዕኖ ይዘረዝራል

## ዋና ዓላማ 1: ምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ

#### ዳሰሳ

በድህረ-ምርት ጊዜ የሚደርስ የመጠን እና የጥራት ብክነት የኢትዮጵያን የግብርና እሴት ሰንሰለት የሚገጥም ዋና ተግዳሮት ነው፡፡ አጠቃላይ ማስረጃዎች "የድህረ-ምርት ብክነት እንደ ዋና ተግዳሮት" በሚለው ርዕስ ሥር አንቀጽ ቁጥር 38 ውስጥ ተካተዋል፡፡

## ዓላማ

51) በምግብ ብክነት ቅነሳ ጉዳይ ሥር ተለይተው መሰራት የሚገባቸው ተግባራት ዋና ዓላማ ምግብ ደህንነቱ ተረጋግጦ ለሰው ፍጆታ እንዲውል እና በአጠቃላይ የምግብ አቅርቦትን ማሻሻል ነው።

### ተለይተው መሰራት የሚገባቸው ተግባራት

52) የምግብ ብክነት ቅነሳን ዓላማ ለማሳካት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ወሳኝ ተግባራት የተለዩ ሲሆን በመቀጠልም በዝርዝር ይቀርባሉ።

ሀ፡ ውጤታማ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ማስፋፋት
ለ፡ የማላመድ ምርምር እና ልማትን ለድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት መጠቀም
ሐ፡ የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት
መ፡ ትክክለኛ የክህሎት፣ የስልጠና እና የሰው ሀብት ልማት
ሠ፡ ከአካባቢ ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የሚደረግ ጥንቃቄ

### ውጤታማ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ማስፋፋት

53) የድህረ-ምርት ብክነት በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ላይ ስላለው ተፅዕኖ ያለው እውቀት በአጠቃላይ ከፖሊሲ አውጪዎች አንስቶ እስከ አርሶ አደሩ ድረስ ባለው ደረጃ ዝቅተኛ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ምን አልባትም በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ ግልጽ ፖሊሲ ባለመኖሩ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም የድህረ-ምርት ብክነት ጽንሰ-ሀሳብ ብዙ አቅጣጫ ያለውና ዘርፈ-ብዙ ሳይንስን የያዘ መሆኑን መረዳት አለመቻል ሌላው ምክንያት ነው። ስለሆነም የሚወሰዱ ርምጃዎች የድህረ-ምርት ሥርዓቱን ሳይነኩ ክስተት ላይ ብቻ ያተኮሩ ይሆናሉ። ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች “በነባራዊ ሁኔታዎች” ርዕስ ሥር በአንቀጽ ቁጥር 14 እና 15 ውስጥ ተዘርዝረዋል።

54) ኢትዮጵያ ውስጥ በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ በፖሊሲ ደረጃ፣ በትምህርት እና ስልጠና ደረጃ እዲሁም በምርምር እና ልማት ደረጃ ጅምር ሥራዎች አሉ። ብዙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች፣ የምርምር ማዕከላት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የግሉ ዘርፍ እና ሌሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ ሥራዎችን ይሰራሉ። ሆኖም ግን እያንዳንዱ ተቋም (ኢንስቲትዩት) ሌሎች የሚሰሩትን ሥራ እሳቤ ውስጥ ሳያስገባ የራሱን ግዴታ ብቻ ይወጣል። ይህ ሁኔታ የመደጋገፍ እድልን አጥፍቷል፣ ውጤታማ ያልሆነ የሀብት አጠቃቀም ከማስከተሉ በተጨማሪ በድህረ-ምርት ቅነሳ ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎች የተበታተኑ እንዲሆኑ አድርጓል። ይህን ችግር ለማስቀረት በድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ዙሪያ ሚሰሩ ሥራዎችን በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ለማስተባበር ጠንካራ ተቋማዊ አሰራር መዘርጋትን ይጠይቃል።

55) ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ
ሀ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ አመች የሆነ የተቋም የክትትል እና የግምገማ ሥርዓትን ጨምሮ እና የአሰራር መዋቅር በመመስረት እና በማጠናከር ለመንግስታዊ ድርጅቶች እና ለግሉ ዘርፍ ግልጽ ሀላፊነት እና ሚና ከተጠያቂነት ጋር መስጠት
ለ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ውስጥ ያሉ መልካም ተሞክሮዎችን በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ማስተማር እና ማስፋፋት
ሐ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን የሚያስተባብር የተለያዩ ዘርፎችን (ግብርና፣ ጤና፣ ሥነምግብ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ወዘተ) ያካተተ አስተባባሪ መመስረት

መ፡ በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ለሚሰሩ ሥራዎች በቂ ገንዘብ መመደብ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ

## የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ የማላመድ ምርምርን እና ልማትን ማስፋፋት

56) እህል ጥቅም ላይ እስከሚውልበት ድርስ የሚኖረው ጥራት በቅድመ-አጨዳ እና በአጨዳ ጊዜ ባሉ ነገሮች እንደ ዝርያው ዓይነት፣ ሰብሉ ያደገበት ሁኔታ እና አካባቢ፣ በአጨዳ እና ከአጨዳ በኂላ ባለው አያያዝ ይወሰናል። ሰብሉ ከመድረሱ በፊት ማጨድ የርጥበት መጠኑ ከፍተኛ ስለሚሆን ይበሰብሳል፣ ሲከማችም ለሻጋታ እና ለሌሎች ተባዮች ጥቃት ይጋለጣል። ሰብሉ ከደረሰ በኂላ ዘግይቶ ማጨድ ደግሞ ከመጠን በላይ ስለሚደርቅ ከአጨዳ በፊት እና በአጨዳ ጊዜ ፍሬው ሊበተን ይችላል፣ የእህሉ ፍሬ የርጥበት መጠኑ ዝቅተኛ ስለሚሆን ክብደቱ አነስተኛ ይሆናል። በተጨማሪም ሰብልን በትክክለኛ ጊዜ አለማጨድ ለተባይ እና ለሻጋት ጥቃት ሊያጋልጥ እና ጥቃቱም ወደ ማከማቻ በመዛመት የጥራት ጉድለት ያመጣል።

57) ፈጥኖ ወይም ዘግይቶ የሚደርስ ትክክለኛ ዝርያ መምረጥ እና መጠቀም አጨዳ መቼ መከናወን እንዳለበት ለመወሰን ስሊሚያስችል ብክነትን ለመቀነስ ይረዳል። መበተንን ወይም መርገፍን የሚቋቋሙ ዝርያዎች የሚገኙ ከሆነ ዝርያዎቹን ማምረት በአጨዳ ጊዜ የሚደርስ ብክነትን ለመቀነስ ይረዳል። በተመሳሳይ መልኩም የጎተራ ተባይን የሚቋቋሙ ዝርያዎች የሚገኙ ከሆነ ዝርያዎቹን ማምርት በክምችት ጊዜ በተባዮች የሚደርስ ብክነትን ለመቀነስ ይረዳል። በርጥበታማ ስነ-ምህዳሮች ወይም አካባቢዎች ውሃ በደንብ ባልተንጣፈፈ ማሳ የበቀለ ሰብል መሬቱ ውሃ ስለሚይዝ ተክሎች ሊወድቁ ስለሚችሉ አጨዳን በተለይም ኮመባይን መጠቀምን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ስለሆነም ውሃን ከማሳ ውስጥ አንጠፍጥፎ ማስወጣት የኮምባይን አጨዳ ውጤታማነትን ይጨምራል።

58) ከአጨዳ በፊት እና በአጨዳ ጊዜ ባሉ ሂደቶች የምርምር፣ የልማት እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት በየደረጃው ሊፈጠር የሚችለውን የምግብ የመጠን እና የጥራት ብክነት ለመቀነስ ያስችላል። የግብርና ምርምርን እና ቴክኖሎጂዎችን ማሻሻል ምርት እና ምርታማነትን ለመጨመር እና ለማሻሻል ከመጥቀሙ በተጨማሪ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቆጣጠር ይረዳል። ሆኖም ግን በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ስድስት አስርተ ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም አሁንም ድረስ ለድህረ-ምርት አያያዝ ምንም ትኩረት አልተሰጠውም። ምርምር እና ልማት ከሚፈልጉ ጉዳዮች መካከል የድህረ-ምርት ብክነት ዓይነቶችን እና መንስኤ መለየት፣ በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ብክነት የት፣ መቼ እና ለምን እንደሚፈጠር ማወቅ፤ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ ምን መደረግ እንዳለበት እና መወሰድ ያለባቸውን ርምጃዎች ተገቢነትን ማወቅ የመሳሰሉት ናቸው።

59) ስለሆነም የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ ከማላመድ ምርምር እና ልማት ጋር በተገናኘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ

ሀ፡ የምርምር እና ልማት ተቋማት እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎች በድህረ-ምርት አያያዝ ዙሪያ ምርምር እንዲሰሩ እና ስልጠና እንዲሰጡ ማመቻቸት

ለ፡ የመንግስት እና የግል ዘርፉ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ በጋራ ምርምር እና ልማት እንዲሰሩ ማበረታታት

ሐ. በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ በሁሉም ደረጃ የሚከሰተውን ብክነት በመጠን እና በገንዘብ ተመን ለመለካት እንዲሁም ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚረዱ በጥናት የተደገፉ ማስረጃዎችን ለማመንጨት የሚካሄዱ ጥናቶችን መደገፍ

## የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች

60) የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ከምርምር እና ልማት ጋር የተቆራኙ ወይም የተሳሰሩ ቢሆንም ራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ለብቻ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የግብርናውን ዘርፍ ከድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ጋር በተያያዘ ከገጠሙት ተግዳሮቶች መካከል አንዱ አነስተኛ አርሶ አደሮች በሰፊው የሚጠቀሙት ያልተሻሻለ (ባህላዊ) የአጨዳ፣ የማድረቅ፣ የውቂያ፣ ማዝራት እና የማከማቻ ዘዴ ነው፡፡ የተሻሻሉ የማምረቻ፣ የማጨጃ እና የማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የግብርና ምርት አምራቾችን ሊያነቃቃ እንደሚችል፣ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ እንዲሁም የግብርና ምርቶች ላይ እሴት ለመጨመር እንደሚረዳ ይታመናል፡፡

61) ጤናማ፣ ጠንክሮ የሚሰራ እና በግብርና መስክ በቂ ትምህርት እና ስልጠና የወሰደ የሰው ሀይል ለተፋጠነ እድገት መሠረት ቢሆንም የሰው ሀይሉ ምርታማነትን በዘለቄታ ለማሳደግ በሚረዳ ቴክኖሎጂ ካልታገዘ እድገት የተፋጠነ እንደማይሆን አጽዕኖት በመስጠት በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የቴክኖሎጂን አስፈላጊነት ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን ተገቢ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የድህረ-ምርት ብክነትን በተጓዳኝ ሳይቀንሱ ምርት እና ምርታማነትን መጨመር ብቻ በምግብ ራስን-መቻልን ብሎም አጠቃላይ የምግበ ዋስትናን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

62) እንደ የግብርና ገበያ ጥናት ማዕከል ትስስር[2] (ኔትዎርክ) እና ከአሁን በፊት እንደ ተተረጎመው የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ ዘርፈ-ብዙ ሙያን /ሳይንስን/ እና ቴክኒክን ሥራላይ በማዋል የግብርና ምርትን ከአጨዳ በኂላ በመጠበቅ፣ በማቆየት፣ በማቀነባበር፣ በማሸግ፣ በማሰራጨት፣ ጥራትን በመቆጣጠር ወይም በማሻሻል፣ በመሸጥ እና በመጠቀም የሰውን የምግብ እና የንጥረ-ነገሮችን ፍላጎት ማሟላት ነው፡፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ የማመንጨት ሂደት እና ስኬታማ ትግበራ ሳይንሳዊ ፈጠራን፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራን እና ንግድ ተኮር ፈጠራን ስለሚፈልግ የብዙ ሳይንስ ዘርፎችን ቅንጅት እና ከብዙ አቅጣጫዎች የተቃኘ ከመሆን በተጨማሪ የባለድርሻ አካላትን ግብዓት ይጠይቃል፡፡

63) ኢትዮጵያ ውስጥ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ ውድ በመሆኑ አርሶ አደሮች እና አነስተኛ የግብርና ሥራ ያላቸው ድርጅቶች ቴክኖሎጂውን መግዛት አይችሉም፡፡ በተጨማሪም የአዕምሮ ንብረት ጥበቃ የሚደረግላቸውን ቴክኖሎጂዎች ገዝቶ ለማላመድ ወጪው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ለድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ የብድር አገልግሎት እና የገንዘብ ተደራሽነት አለመኖር ለዚህ ችግር መባባስ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የገንዘብ ተቋማት ለግብርና ኢንቨስትመንት ቅድሚያ እና ትኩረት ስለማይሰጡ ነው፡፡

64) የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ በዋሉባቸው አንዳንድ ቦታዎች ችግሮች ተፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ በማሽን የማጨድ እና የመውቃት ቴክኖሎጂ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የድህረ-ምርት ብክነት ይከሰታል፡፡ ሆኖም ግን ብክነቱ የሚከሰተው በቴክኖሎጂው ድክመት ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ ቴክኖሎጂውን ያለአግባብ መጠቀም ለምሳሌ ቴክኖሎጂውን ያመረተው አምራች የሚሰጠውን መመሪያ አለመከተል፣ ማሽኑን ወይም መሳሪያውን እንደ ሥራው ዓይነት ማስተካከል አለመቻል ወይም ጥገና እና በየጊዜው ፍተሻ አለማድረግ ብክነት እንዲፈጠር የሚያደርጉ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር የሚመነጨው ከክህሎት እና የሰው ልማት ጋር በተያያዘ ጉድለት፣ ለመለዋወጫ መግዣ በቂ የገንዘብ አቅርቦት አለመኖር እንዲሁም ስለመሣሪያው አጠቃቀም የተሰጡትን ዝርዝር ደንቦች ተጠቃሚው እንዲከተል የሚያስገድድ የቁጥጥር ማዕቀፍ እና አስፈጻሚ ተቋም አለመኖር ነው፡፡ .

[2] http://amickau.nic.in/index.php?option=com_content&task=view&id=53&Itemid=87

65) ስለሆነም  የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን ከሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ጋር  በተገናኘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ

ሀ፡ አግባብነት ያለው እና ተደራሽ የሆነ ቴክኖሎጂ በማመንጨት አጨዳን፣ ውቂያን፣ ማድረቅን፣ ማሸግን፣ ማጓጓዝን እና የማከማቸት ሥራን በማገዝ  የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ ተቀናጅተው የሚሰሩ ምርምሮችን እና ልማቶችን ማስፋፋት

ለ፡ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ እንዲሁም ለጥገና እና ሰርቪስ አገልግሎት የሚውል የገንዘብ አቅም እንዲኖር አበረታች እና በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የገንዘብ አቅርቦት መፍጠር

ሐ. የድህረ-ምርት ብክነትን የሚያስከትሉ ማሽነሪዎችን ብቃት ለማሻሻል መሣሪያዎችን ወይም ማሽኖችን የሚያንቀሳቅሱ እና የሚጠግኑ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት

መ፡ ስለመሣሪያው አጠቃቀም የተሰጡትን ዝርዝር ደንቦች ተጠቃሚው እንዲከተል የሚያስገድድ የቁጥጥር ማዕቀፍ እና አስፈጻሚ ተቋም መመስረት

ሠ፡ የመሣሪያ እና የማሽነሪ ጥገና እና ሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ማቋቋም እና ማስፋፋት

## ክህሎት፣ ስልጠና እና የሰው ልማት

66) አሁን ዝቅተኛ የትምህርት እድል ያለውን ማህበረሰብ በተለይም የገጠሩን ማህበረሰብ የማሰልጠን እና የማስተማር ሥራ ስፋት እና ክብደት በ 1995 ዓም በወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ውስጥ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አገር-በቀል የግብርና ሥራዎችን እና እውቀቶችን እሳቤ ውስጥ ያስገባ የኤክስቴንሽ አገልግሎትን በመዘርጋት የግብርና አሰራርን ማሻሻል እደሚገባ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ የአርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከላት የልማት ሠራተኞች አርሶ አደሮችን ለማሰልጠን የሚጠቀሙባቸው ዋና ዋና ቦታዎች ናቸው፡፡ በእነዚህ ማዕከላት ውስጥ ጠንካራ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት በእያንዳንዱ ቀበሌ አራት የልማት ሠራተኞች ተመድበው በሰብል፣ በቤት እንስሳት፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማት እና ጥበቃ እና በጤናው ዘርፍ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ሆኖም ግን ዋናው ተግዳሮት የልማት ሠራተኞች በድህረ-ምርት ጉዳዮች ዙሪያ ያላቸው እውቀት ደረጃ ነው፡፡ አሁን ለልማት ሠራተኞች የሚሰጠው የስልጠና ሥርዓተ-ትምህርት በማምረት እና በምርታማነት ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ ስለድህረ-ምርት የጽንሰ-ሀሳብ እና የተግባር ስልጠና በዝቅተኛ ደረጃ ይሰጣል፡፡ ይህ በመሆኑም ለድህረ-ምርት ብክነት የሚሰጠው ትኩረት እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

67) በኢትዮጵያ ውስጥ ከአስር በላይ ዩኒቨርሲቲዎች በድህረ-ምርት ዙሪያ ትምህርት እና ስልጠና የሚሰጡ ቢሆንም ሁሉም በጀማሪ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በድህረ-ምርት አያያዝ ለሰለጠኑ ባለሙያዎች በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ ያለው የሰው ሀይል ፍላጎት አነስተኛ በመሆኑ በዘርፉ ለመሰልጠን ያለው ፍላጎት እጅግ አነስተኛ ነው፡፡

68) መደበኛ ትምህርትን ለአብዛኛው ማህበረሰብ ማዳረስ አለመቻል የአርሶ አደሮችን አቅም ውስን ስላደረገው አርሶ አደሮች ቴክኖሎጂዎችን ለመረዳት እና ለመጠቀም አልቻሉም፡፡ በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ክህሎትን እና የቴክኖሎጂ እውቀትን በአጭር እና በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ወደ አርሶ አደሮች ብሎም ለጠቅላላው ማህበረሰብ ለማስተላለፍ በተግባር ሰርቶ-ማሳየትን እና የልምድ ልውውጥን እንደ ዋና አካሄድ አስቀምጧል፡፡ የአርሶ አደሩን እና የገጠሩን ማህበረሰብ የትምህርት ደረጃ በተጓዳኝ ለማሳደግ ጥረቶች እንደሚደረጉ ሰነዱ ይጠቁማል፡፡

69) ሥርዓተ-ፆታ እና ወጣቶች በግብርና ውስጥ ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ አካሎች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ሴቶች በግብርና ሥራ በመሳተፍ ከፍተኛ የጉልበት አስተዋፅዖ ከማበርከታቸው በተጨማሪ ምግብ በማምረት፣ በማዘጋጀት እና በማቀናበር ሂደት እና የቤተሰብን የንጥረምግብ

ፍላጎት በማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ሆኖም ግን አስተዋፆዐቸው ዋጋ አይሰጠውም። ወጣቶች ደግሞ የወደፊቱን የግብርና ሥራ የሚረከቡ በመሆናቸው በግብርና ሥራ ውስጥ እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ወጣቶች በእውቀት እየበለጸጉ ሲሄዱ የለውጥ ምንጭ ስለሚሆኑ ወደፊት ድህረ-ምርት አያያዝ ቅድሚያ ሊሰጠው ይችላል። ሆኖም ግን ወጣቶች በግብርና ሙያ እንዲቀጥሉ ከተፈለገ የግብርናው ዘርፍ በበቂ ሁኔታ መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ያስፈልጋል።

70) ስለሆነም የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ ከክህሎት፣ ከስልጠና እና ከሰው ልማት ጋር በተገናኘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ

ሀ፡ በግብርና ሙያ እና ቴክኒክ ስልጠና ኮሌጆች እና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለሚሰጡ የድህረ-ምርት የንድፈ-ሀሳብ እና የተግባር ስልጠናዎች አገልግሎት የሚውል ድህረ-ምርትን ያካተተ ጠንካራ ሥርዐተ-ትምህርት መቅረጽ

ለ፡ ስለ ድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ስልጠና የሚሰጡ የልቀት ማዕከላትን መመስረት

ሐ. በድህረ-ምርት ብክነት፣ መንስኤ እና መፍትሄዎች ዙሪያ ያሉ ሳይንሳዊ እና አገር-በቀል እውቀቶችን ማሰራጨት

መ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ለሰለጠኑ ባለሙያዎች ማበረታቻ መስጠት እና የሥራ እድል ማመቻቸት

ሠ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ በሚሰሩ የክህሎት እና የሰው ልማት ሥራዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን በተለይም ለሴቶች እና ለወጣቶች ትኩረት መስጠት

**ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች**

71) እንደ ሌሎች የግብርና ሥራዎች የድህረ-ምርት ሥራዎችም በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ ያደርሳሉ። ለምሳሌ ብዙ እንጨት በመጠቀም የሚሰሩ ማከማቻዎች እና የማድረቂያ ማማዎች ለደን መመናመን ብሎም ለመሬት መራቆት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ የመሬት መራቆት ትልቁ የአካባቢ ችግር ከመሆኑ በተጨማሪ አሁን ላለው የግብርና ምርታማነት ማሽቆልቆል ዋናው ምክንያት ነው። ይህም በመሆኑ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና በገጠር ያለውን ድህነትን መቀነስ አልተቻለም (Gashaw et al 2014)። ለመሬት መራቆት በከፊል ምክንያት ከሆኑ ነገሮች መካከል በፍጥነት በተለይም በገጠር እያደገ የመጣው የሕዝብ ብዛት ጫና እንደሆነ ይታመናል። ሰብል ማምረት እና የቤትእንስሳት ማምረት ያልተመጣጠኑ መሆን እና ተገቢ ያልሆነ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ለችግሩ መባባስ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

72) የደን መመናመን ችግርን ለመቅረፍ አርሶ አደሮች እና ነጋዴዎች እንደ ሸራ፣ አየር-አልባ ጆንያዎች (ከረጢት)፣ የብረት ጎተራ የመሳሰሉትን ዘመናዊ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን እህልን ለማድረቅ እና ለማከማቸት እንዲጠቀሙ ማበረታታት ያስፈልጋል። ሆኖም ግን እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ውድ ስለሆኑ ተጠቃሚዎች መግዛት እንዲችሉ የገንዘብ አቅርቦትን ማሻሻል ይጠይቃል። በሌላ ቦታ እንደተገለፀው የገንዘብ አቅርቦት ችግርን ለመፍታት እና ሊያሰራ የሚችል ሁኔታ ለመፍጠር መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እና ጠንክሮ መስራት አለበት።

73) የማከማቻ ተባዮችን ለመከላከል የሚውል ፀረ-ተባይ በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋለ አካባቢ ላይ በተለይም የውሃ አካላትን እና አፈርን ይበክላል፣ ብዝሀሕይወት ላይ ጉዳት ያደርሳል፣ የምግብ መመረዝን ያስከትላል እንዲሁም ሰዎች ለማጠኛ ፀረ-ተባዮች ይጋለጣሉ። ለምሳሌ የፎስፊን ክኒኖች ዝግ በሆነ ቦታ እና በሰለጠነ ሰው ብቻ ጥቅም ላይ መዋል ሲገባቸው በማንኛውም ሰው በክፍት ጆንያዎች፣ ቤት ውስጥ እና የጭነት መኪኖች ላይ ጥቅም ላይ ሲውሉ በመስክ ሥራው ወቅት መመልከት ተችሏል። እንደዚህ ዓይነቱን አደገኛ የፀረ-ተባይ አጠቃቀም ለማስቀረት የአደገኛ ፀረ-ተባዮችን አጠቃቀም እና ስርጭት መቆጣጠር እና ለተጠቃሚዎች ስለ መልካም የፀረ-

ተባይ አጠቃቀም ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል። በተጨማሪም በፀረ-ተባይ በተበከለ ምግብ ዙሪያ ተገቢ የሆነ ሕግ እና ሕግ አስፈፃሚ ሊኖር ይገባል።

74) ፀረ-ተባይ ያለአግባብ ጥቅም ላይ እንዳይውል ለማድረግ እና አካባቢን ከብክለት ለመጠበቅ የፀረ-ተባይ ሽያጭ እና አጠቃቀም ላይ ቁጥጥር መደረግ አለበት። በተጨማሪም ፀረ-ተባይ መጠቀምን ለመቀነስ ወይም ለማስቀረት ተባዮችን በቅድመ-መከላከያ መንገዶች መቆጣጠር ያስፈልጋል። ቅድመ-መከላከያ መንገዶች የተቀናጀ ተባይ መከላከል አካል ናቸው። የተቀናቀጀ ተባይ መከላከል ሁለገብ አካሄድን ስለሚከተል በሰው ጤና እና በአካባቢ ላይ ሊያመጣ የሚችለው ስጋት ዝቅተኛ ነው።

75) የኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የአየር ንብረት ለውጥን የመላመድ እና የመቀነስ ዓላማዎችን የያዘ ሲሆን የአደገኛ ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ ግብ አስቀምጧል። የአደገኛ ጋዞች ልቀት ቅነሳ እቅድ አራት ምሰሶዎች አሉት። እነሱም (ሀ) የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ ደረጃ ለማረጋገጥ እና የአርሶ አደሩን ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ለመጨመር የሰብልን እና የእንስሳት አመራረትን የአደገኛ ጋዝ ልቀትን በሚቀንስ መልኩ ማሻሻል (ለ) ደኖችን በመጠበቅ እና እንዲያገግሙ በማድረግ ለኢኮኖሚያዊ እና ለሥርዓተ-ምህዳር (ኢኮሲስተም) አገልግሎት በማዋል ካርቦን ዳይኦክሳይድን እንዲመጡ እና እንዲያከማቹ ማድረግ (ሐ) የኤሌክትሪክ ሀይልን ከታዳሽ ምንጮች ማመንጨት እና (መ) በትራንስፖርት ዘርፍ፣ በኢንዱስትሪው ዘርፍ እና በግንባታው ዘርፍ ዘመናዊ እና ሀይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ናቸው። ይህም ማለት የድህረ-ምርት አያያዝ ሥራዎች እና ቴክኖሎጂዎች በሚመነጩበት ጊዜ ብሎም ተግባር ላይ ሲውሉ በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥሩ ጥንቃቄ የተሞላበት ውሳኔ እና ትግበራ እንደሚያስፈልግ ነው።

76) ማህበረሰቡ ብዙ ምርት ባመረተበት ዘመን ምግብ እና መኖ ሳይበላሽ አከማችቶ እጥረት ባለበት ዘመን መጠቀም እንዲችል ለማድረግ አሁን ሥራላይ ያሉትን ባህላዊ የማከማቻ መንገዶችን በማሻሻል በብልሽት የሚባክነውን ምግብ እና መኖ ሳይንስን ወይም እውቀትን መሠረት ባደረገ መልኩ መቀነስ እንደሚያስፈልግ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

77) ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እና የድህረ-ምርት ሂደቶች አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ተፅዕኖ ስላላቸው ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን መዘርጋት እና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ የግብርና አመራረት ዘዴዎችን በመጠቀም የእጽዋት ሽፋን እንዲጨምር ማድረግ። የአፈር መከላትን መቀነስ፣ በእጽዋት የተወሰዱ ወይም በአፈር መሸርሸር የተወገዱ ማዕድናትን መተካት፣ የውሀ ፍጥነትን እና የሚባክነውን ይዘት መጠን ለመቀነስ እርከን ፣ የአፈር ክትር ወዘተ መስራት

ለ፡ ከድህረ-ምርት ተግባራት ጋር በተያያዘ የጠፋ ደንን እንደገና እንዲለማ ማድረግ እና ደንን ለኢኮኖሚያዊ እና ለሥርዐተ-ምህዳር (ኢኮሲስተም) ጥቅም እንዲውሉ እንደገና መትከል እና መጠበቅ

ሐ፡ የተቀናጀ ተባይ መከላከልን ሥራላይ በማዋል የፀረ-ተባይ እና የሌሎች ኬሚካሎችን አጠቃቀምን መከታተል እና መቆጣጠር፣የፀረ-ተባይ ሽያጭን፣ አጠቃቀምን እና አወጋገድን በህጋዊ መንገድ ማስከበር

## ዋና ዓላማ 2:

## የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ቅልጥፍና ማሻሻል

**ዳሰሳ**

78) በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንደሚያሳየው ግብርና ገበያ-መር በሆነ ሁኔታ ሊያድግ የሚችለው ቀልጣፋ የሆነ የግብርና ገበያ ሥርዓት በመመስረት በትክክለኛው ስዓት፣ በትክክለኛው ቦታ፣ በተገቢ ዋጋ እና ጥራቱ የታወቀ ምርት ለገበያ ማቅረብ ሲቻል ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጭ ገበያ ከሚቀርቡ ምርቶች እንደ ቡና፣ ቦሎቄ እና ሰሊጥ በስተቀር ለሌሎች ሸቀጦች ወይም ምርቶች መገበያያ ወጥ የሆነ የገበያ ሥርዓት የለም።

79) ከገበያ ጋር በተያያዘ የድህረ-ምርት ብክነት ችግሮችን ከሚያባብሱ ተግዳሮቶች መካከል ብቃት እና ጥራት የሌላቸው የማከማቻ እቃዎች፣ ኋላቀር የማከማቻ አያያዝ ዘዴ፣ በቂ ያልሆነ የትራንስፖርት መሰረተ-ልማት እና ትስስር፣ ደረጃ እና ዓይነት ላይ ያተኮሩ ሕጎችን ማስፈጸም አለመቻል፣ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ለሚውሉ ሸቀጦች ወይም ምርቶች ጥራትን መሠረት ያደረገ ክፍያ አለመኖር፣ ጊዜ ያለፈባቸው የማሸጊያ ቁሳቁሶች እና አያያዝ ዘዴዎች እና የገበያ መረጃ እጦት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የገበያ መረጃ እጥረት የተከሰተው ከገበያ እና ንግድ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በኤክስቴንሽን አገልግሎት ውስጥ አለመካተታቸው እና በአብዛኛው የኤክስቴንሽን አገልግሎት ትኩረት የሚሰጠው ምርት እና ምርታማነትን መጨመር ላይ ብቻ በመሆኑ ነው። ዘመናዊ የሆነ መሰረተ-ልማት ባለመኖሩ እና በስርጭት እና በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ ብዙ ጉድለቶች በመኖራቸው የኢትዮጵያ የእህል እሴት ሰንሰለት ኋላቀር እና ውጤታማ ባልሆነ መንገድ የተዋቀረ ነው።

**ጥቅል ዓላማ**

80) የግብርና ገበያን ቅልጥፍና ማሻሻል ግቡን እንዲመታ መስራት የሚገባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ጥቅል ዓላማ በትክክለኛው ስዓት፣ በትክክለኛው ቦታ፣ በተገቢ ዋጋ እና ጥራቱ የታወቀ ምርት ለገበያ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የግብርና ገበያ ሥርዓት መፍጠር እና በተጓዳኝ የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ሥርዓትን ሥራላይ ማዋል እና ማስፋፋት ነው።

**ተለይተው መስራት የሚገባቸው ጉዳዮች**

81) ቀጥሎ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ይህ ስትራቴጂ ግቡን እንዲመታ በዋናነት መስራት ከሚገባቸው ጉዳዮች መካካል ሲሆኑ ዘርዘር ያለ ማብራሪያም ቀጥሎ ይቀርባል።

ሀ. የማከማቸት እና የአያያዝ ሥርዓት
ለ. የትራንስፖርት ሥርዓት እና ትስስር
ሐ. ደረጃ እና ዓይነት
መ. የምግብ ደህንነት
ሠ. የገበያ መረጃ
ረ. የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት እና
ሰ. የመንገድ እና የገበያ መሰረተ-ልማት ናቸው።

## የማከማቸት እና የአያያዝ ሥርዓት

82) ወሳኝ ቦታ ወይም አካባቢ ላይ የሚገኝ እና በአግባቡ የተያዘ የማከማቻ ድርጅት የድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስና እና የምርት ግብይትን በማቀላጠፍ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። የማከማቸት ጥቅም የሸቀጥን ጥራት እና መጠን ጠብቆ ለማቆየት፣ ግብይትን ለማሳለጥ እና ሸቀጥን ለብድር እንደ ማስያዣነት መጠቀም ናቸው። በተጨማሪም በዓመት ውስጥ ወደ ማከማቻው የገባውን እና የወጣውን የእህል መጠን ስልታዊ በሆነ መንገድ መመዝገብ በሚቀጥለው ዓመት የሚመረተውን መጠን ለማቀድ እና/ወይም መውጣት ወይም መግባት ያለበትን ተጨማሪ የምርት መጠን ለማወቅ ከመርዳቱ በተጨማሪ ስለ ምርቱ አቅርቦት እና ፍላጎት ሚዛን አቅጣጫ ይሰጣል።

83) የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ብክነትን የሚቀንሰው እና ውጤታማ የሚሆነው በሁሉም የአቅርቦት ሰንሰለት ደረጃዎች አስተማማኝ እና በቂ የማከማቻ ድርጅት ሲኖር ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ማከማቻ በቤት ደረጃ፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን እና በክልል ደረጃ ቢኖር የድህረ-ምርት አያያዝን ውጤታማ ከማድረጉ በተጨማሪ ብክነትን በተገቢው ደረጃ ይቀንሳል። በቤት ደረጃ ምርትን የማከማቸት ዓላማ የገበያ አቅርቦትን እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ነው። በወረዳ ደረጃ የማከማቸት ዓላማ ደግሞ በአብዛኛው ትንንሽ የምርት መጠኖችን በአንድ ላይ አሰባስቦ ለመደበኛ ገበያ መቅረብ የሚችል ቢያንስ ዝቅተኛውን መጠን ለመፍጠር ነው። ብዙዎች ግለሰብ ነጋዴዎች፣ ህብረት ሥራ ማህበራት ወይም አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ሸቀጥ የማሰባሰቢያ ማዕከላት አላቸው። በተጨማሪም ማዕከላዊ የሆነ መጋዘን ያላቸው ነጋዴዎች ማሰባሰቢያ ማዕከላት በመክፈት ወደ መጋዘናቸው የሚገባ ሸቀጥ ወይም ምርት ማሰባሰብ ይችላሉ።

84) በዞን ወይም በክልል ደረጃ የሚደረግ ክምችት ለሰፊ የንግድ ሥራ የሚውል ስለሆነ ማዕከላዊ ማከማቻ ተብሎ ይመደባል። የማዕከላዊ ማከማቻ ዋና ዓላማ ለግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች፣ ለተቋማት፣ በምርት ገበያዎች ውስጥ የሚከናወኑ ግብይቶችን ለመደገፍ እና ዓለም ዓቀፍ ደራጃዎችን አሟልተው ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ለማከማቸት ነው።

85) የማከማቸት እና የአያያዝ ሥርዓት ጋር በተገናኝ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ለእያንዳንዱ የአቅርቦት ሰንሰለት ደረጃ ተስማሚ እና ተደራሽ የሆነ ማከማቻ በቤት (በአባወራ)፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን እና በክልል ደረጃ ማቋቋም
ለ፡ ውጤታማ እና ተደራሽ የሆኑ የማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን ለምሳሌ የብረት ጎተራ እና የተሻሻሉ አገር-ብቀል ማከማቻዎችን ማምረትን እና በሰፊው ማሰራጨትን ማሳለጥ እና ማስፋፋት
ሐ፡ ከምግብ ደህንነት ጋር የተያያዙ እንደ የማከማቻ ቦታ ስፋት፣ የእህል ንጽህና እና ጥራትን ለመሳሰሉት ጉዳዮች ደረጃ ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ
መ፡ የማጠኛ ፀረ-ተባዮችን አጠቃቀም እና አወጋገድ ጨምሮ ተገቢ የሆነ የማከማቻ ተባዮች መቆጣጠሪያ መንገዶችን ማስተዋወቅ እና ማስፋፋት
ሠ፡ ለመጋዘኖች ደረጃ መስጠት እና ደረጃ ላሟሉ እውቅና የመስጠት ሥርዓትን ማስፋፋት
ረ፡ በማከማቻ መሰረተ-ልማት አቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ የመንግስት እና የግል ዘርፉን ማስተሳሰር

## የትራንስፖርት ሥርዓት እና ትስስር

86) ብክነት በዝቅተኛ ደረጃ የከሰትበት የምግብ አቅርቦት ሰንሰለት ውጤታማነት ሥራላይ ባለው የምርት እና ተያያዥ ነገሮች ማጓጓዣ ሥርዓት ብቃት ይወሰናል። በተመሳሳይ መልኩ የማጓጓዣ ሥርዓት ውጤታማነት ሥራላይ ባለው የመንገድ መሰረተ-ልማት እና ትስስር፣ የሽቀጥ ማሸጊያ ዓይነት እና አጠቃቀም እና በማጓጓዣ ዓይነቶች ይወሰናል። የትራንስፖርት ሥርዓት እና ትስስር በ1995 ዓም በወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚከተለው ተቀምጧል።

> “ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሸቀጦች ማጓጓዣ መንገድ መኪኖችን፣ የጭነት እንስሳትን እና ሰውን መሰረት ያደረገ ነው። ሌሎች የማጓጓዣ አማራጮች ቢኖሩም በሚፈለገው ደረጃ አላደጉም። ገጠር ውስጥ የሚደረገውን ማጓጓዝ በአህያ፣ በፈረስ ወይም በበቅሎ የሚጎተት ጋሪ (ባለ ሁለት ወይም ባለ አራት ጎማ) በመጠቀም ማሻሻል ቢቻልም በአብዛኛው የገጠር አካባቢ ጋሪ ጥቅም ላይ ሲውል አይታይም። በተመሳሳይ መልኩ ከከተሞች ውጭ ብስክሌትን እና ሞተር ሳይክሎችን መጠቀም ብዙ የተለመደ አይደለም። እንደነዚህ ዓይነት የማጓጓዣ አማራጮችን መጠቀም ካልተቻለ የትራንስፖርት ሥርዓቱን ማሻሻል አይቻልም። ጋሪ እና ሌሎች የማጓጓዣ አማራጮች በሰፊው ጥቅም ላይ ለማዋል የግል ባለሀብቶች እና የህብረት ሥራ-ማህበራት መዋዕለ-ንዋያቸውን እንዲያፈሱ የቀበሌ እና የወረዳ ባለስልጣናት ማበረታታት አለባቸው (MoFED 2003)።”

87) የድህረ-ምርት አያያዝ ተገቢ የሆነ ትራንስፖርት በማህበረሰብ ደረጃ እና በማከፋፈያ ደረጃ ሊኖረው ይገባል። በማህበረሰብ ደረጃ የሚያስፈልገው ማጓጓዣ አርሶ አደሮች እና ሌሎች ተዋኒያን ምርታቸውን ከማሳ ማሳ፣ ከማሳ ወደ መውቂያ ቦታ፣ ከቤት ቤት እና ከቤት ወደ ገበያ እና ምርት ማቀነባበሪያ ቦታዎች ለማጓጓዝ ነው። በአንድ ጊዜ የሚጓጓዘው የጭነት መጠን ወይም ልክ ከአምስት ኪሎ እስከ አምስት ቶን ሊደርስ ስለሚችል የተለያየ መጠን ያለውን ምርት ለማጓጓዝ የሚያስችል እና ለገጠር ሁኔታ ተስማሚ የሆነ የማጓጓዣ ዘዴ መኖር አለበት። ትንንሽ ጭነቶችን ለማጓጓዝ በእጅ የሚገፋ ጋሪ (ኩርኩር (ካሬታ)) ተመራጭ ነው። ከአንድ ቶን እስከ አምስት ቶን የሚደርስ ጭነትን ለማጓጓዝ ደግሞ ተሳቢ ጋሪ (የስኮች ጋሪ) ለገጠር አካባቢ ተስማሚ ነው። የሰለጠኑ የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ተሳቢ ጋሪ (የስኮች ጋሪን) ከወዳደቁ የመኪና አካላት መስራት ይችላሉ።

88) ብዙ መጠን እና ረጅም ርቀት ተጓጉዞ የሚሰራጭ ጭነትን ለማጓጓዝ ተሽከርካሪን መሰረት ያደረገ የማጓጓዝ ዘዴ ስለሚፈልግ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋቢ መንገዶችን መገንባት ያስፈልጋል። ጭነትን ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች ጭነቱን በቀላሉ ወደ መጋዘን ለማስገባት ወይም ለማስወጣት የሚያስችሉ መሆን አለባቸው። ሸቀጦች በሚጓጓዙበት ጊዜ በዝናብ እና ሌሎች ነገሮች ጉዳት እንዳይደርስባቸው በሸራ መሸፈን አለባቸው። ማህበረሰቡን ከማከማቻ ድርጅቶች ወይም ቦታዎች የሚያገናኙ እና ወንዝ የሚያቋርጡ መጋቢ መንገዶች በአግባቡ መጠገን እና ከዋናው መንገድ ጋር የተገናኙ መሆን አለባቸው።

89) ስለሆነም የትራንስፖርት ሥርዓትን እና ትስስርን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ምርታቸውን ከማሳ ወይም ከቤታቸው ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የሚያስችሉ አነስተኛ እና ጉልበት ቆጣቢ የማጓጓዣ መሳሪያዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጥሙ ድርጅቶች በየአካባቢው እንዲፈጠሩ እና እንዲጎለብቱ ማመቻቸት

ለ፡ የመጋቢ እና የዋና ዋና መንገዶችን ትስስር ማሻሻል እና ማልማት
ሐ፡ ሸቀጦችን ከወረዳ ወደ ዞን፣ ከዞን ወደ ክልል ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎችን ግዥ መደገፍ
መ፡ የአስተሻሸግ እና የማጓጓዝ ደረጃ እና ደንብ ማስተዋወቅ እና ተፈጻሚ ማድረግ

## ዓይነት እና ደረጃዎች

90) የምርት ዓይነትን እና ደረጃን የመለየት አስፈላጊነት በ 1995 ዓም በወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ውስጥ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

> "ጥራቱ የተጠበቀ ምርት ቀልጣፋ ወደሆነ የግብይት ሥርዓት ውስጥ ለማስገባት የምርት ዓይነትን መለየት እና ደረጃ የማውጣትን ሥርዓት ይፈልጋል፡፡ አንድ ምርት ተቀባይነት ያለው የጥራት ደረጃ ማሟላቱ የሚታወቀው ምርቱ የታወቀ ዓይነት እና ደረጃ ሲኖረው ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አምራቹ ደረጃ ያሟላ ምርት ማምረት የሚችለው የምርቱ ደረጃ ሲታወቅ እና በግልጽ ተለይቶ ሲቀመጥ ነው፡፡ ሸማቹም ትክክለኛ ምርት መግዛቱን የሚያውቀው የምርቱ ደረጃ የታወቀ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የምርት ደረጃ ሲወጣ አምራቹን እና ሸማቹን እሳቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ተቀባይነት ያለው የዓይነት ሥርዓት መዘርጋት እና ለሥርዓቱ ተስማሚ የሆነ መለኪያ አብሮ ማቅረብ ያስፈልጋል (MoFED 2003)፡፡

91) ዓይነት እና ደረጃ ማለት ሊለኩ የሚችሉ የሸቀጥ ወይም የምርት ባህሪዎችን እና ሥልጣን ባለው አካል የወጡ እና የሚፈጸሙ የመለኪያ ደንቦችን መሠረት በማድረግ ሸቀጦችን ወይም ምርቶችን የመመደቢያ ሥርዓት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢ ኤጀንሲ በ 2002 ዓም የኢትዮጵያ የጥራት እና ደረጃ ባለስልጣንን በአዲስ መልክ በማደራጀት የተቋቋመ ቢሮ ነው፡፡ ከግብርና ጋር በተያያዘ ዓይነት እና ደረጃ የምርቱን የጥራት ደረጃ የሚገልጹ ዝርዝር መገለጫዎችን ወይም ባህሪን ከመስጠቱ በተጨማሪ ስለ ምርቱ አንድ ዓይነት ቋንቋ እንዲነገር ያደርጋል፡፡ ዓይነት እና ደረጃ ገበያ ውስጥ ለሚሸጠው ምርት የተለያየ ዋጋ ለመክፈል ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በአወንታዊ መልኩ ዓይነት እና ደረጃ ገበያን ለመከፋፈል እና ምርቱ በጣም የሚፈለግበትን ገበያ (ቦታ) ለመለየት ይረዳል፡፡ በአሉታዊ ጎኑ ደግሞ ዓይነት እና ደረጃ በማደግ ላይ ያሉ ወይም መስፈርቱን ሟሟላት የማይችል ምርት የሚያመርቱ አምራቾች ገበያ ውስጥ እንዳይሳተፉ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ችግር ገበያው እያደገ ሲሄድ በሚደረግ የዓይነት እና የደረጃ ክለሳ ሊስተካከል ይችላል፡፡

92) ሰፊ የሆነው የዓይነት እና የደረጃ ሥርዓት ባህሪ የገበያን ቅልጥፍና እና ግልጽነትን በብዙ መንገድ ያጎለብታል፡፡ ለምሳሌ የዓይነት እና የደረጃ ሥርዓት ምርቱ በአካል ሳይኖር አቅራቢው እና ገዥው በምርቱ ዝርዝር መገለጫ ብቻ ዋጋ መደራደር እና መስማማት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ሥርዓቱ ጥራትን እና ለአያያዝ አመችነትን መሠረት ያደረገ ዋጋ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ የዓይነት እና የደረጃ ሥርዓት በአገራት ወይም በክፍለ-አህጉር መካከል ያለን ዋጋ ወይም ጥራትን ለማወዳደር፣ የተለያዩ የግብይት አማራጮችን እንደ ምርት ገበያ፣ የወደፊት ግብይት፣ በባንክ የሚከፈል የሽያጭ ውል፣ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ፕሮግራም የመሳሰሉትን ውጤታማ ከማድረጉ በተጨማሪ የገበያ መረጃ ዋጋ ያለው እንዲሆን ያደርጋል፡፡ የዓይነት እና ደረጃ ሥርዓት በጥራት እና/ወይም በተላከው ምርት ይዘት የሚነሳ ግጭትን ለመፍታት ይረዳል፡፡

93) እላይ እንደ ተገለጸው የዓይነት እና የደረጃ ሥርዓት ባህሪ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል፡፡ ምክንያቱም ሥርዓቱ አግባብ እና የተሻለ የሰብል ዓይነት

ምርጫን፣ በአቅርቦት ሰንሰለቱ ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ ማከማቻ፣ አስተሻሸግ፣ ማጓጓዝ እና አያያዝ ሥርዓት መጠቀምን ስለሚያስገድድ ነው።

ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት እንዲሁም መኖራቸውን ማረጋገጥ እና ተፈፃሚ ማድረግ የተለያዩ ጉዳዮች ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ የዓይነት እና የደረጃ ደንቦችን ተፈፃሚ ማድረግ አለመቻል አንዱ ተግዳሮት ነው። ስለሆነም እንደ የምግብ፣ የመዳህኒት እና ጤና እንክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የመሳሰሉ የመንግስት አካላት የዓይነት እና ደረጃ ደንቦች በአቅርቦት ሰንሰለቱ ውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆኑ መንገድ ማመቻቸት አለባቸው። በሰፊው መሰራት ካለባቸው ሥራዎች መካከል የዓይነት እና ደረጃ ደንቦች ሥራ ላይ እንዲውሉ ማስተማር፣ የዋጋ አተማመን ሥርዓትን ማሻሻል (ዋጋ እንደ ምርቱ የጥራት ደረጃ እዲከፈል ማድረግ)፣ የዓይነት እና የደረጃ ደንቦችን ለሚጠብቁ ማበረታቻ መስጠትን እና የዓይነት እና ደረጃ ደንቦችን ለሚጥሱ የማስተካከያ ርምጃዎችን መውሰድ ናቸው።

94) ስለሆነም የሽቀጥ ወይም ምርት ዓይነት እና ደረጃ ደንቦችን ከማስፈጸም ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ዓለም ዓቀፍ የእህል ዓይነትን እና ደረጃን እንደ መነሻ በመጠቀም ለሰብል ምርቶች ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት

ለ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓቱን የሚደግፉ የጥራት መፈተሻ ቤተ-ሙከራዎችን (ላቦራቶሪዎችን) ማቋቋም

ሐ. የተሻሻሉ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥራዎች ይበልጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ዋጋ እንደ ምርቱ የጥራት ደረጃ እንዲከፈል የሚያደርግ ሥርዓት መመስረት

መ፡ የወጡትን የዓይነት እና ደረጃ ደንቦች ለሚያስፈጽሙ አካላት የአቅም ግንባታ ማድረግ

### የምግብ ደህንነት

95) የምግብ ደህንነት ጉዳይ ከምግብ ጥራት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ከድህረ-ምርት ጋር በቀጥታ ይገናኛል። እህል ውስጥ ያለ የሻጋታመርዝ (አፍላቶክሲን)፣ ጥቃቅን ዘአካል እና ሌሎች መርዛማ ነገሮች ምግቡ ለሰው ፍጆታ አንዳንዴም ለእንስሳ መኖነት እንዳይውል ያደርጋሉ። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የግብይት ሥርዓት የኩንታል መጠንን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ከተለያዩ አቅራቢዎች የተገኘ እህልን ወይም ምርትን ማደባለቅ ያስችላል። አርሶ አደሮች ከአምስት ኪሎ ግራም ጀምሮ የተለያየ መጠን ያለው እህል ለነጋዴዎች ስለሚያቀርቡ ነጋዴዎች ደግሞ ኩንታልን እንደ ደረጃ ስለሚወስዱ ኩንታል ለመሙላት እህል ያደባልቃሉ። እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ወደ ገበያ የሚቀርበውን የእህል ንጽህና እና ጥራት ይጎዳል። የግብርና ምርቶች በድህረ-ምርት አያያዝ ጊዜ የምግብ ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ዘርፈብዙ ሙያዎችን ማህበራዊ ሳይንስን ጨምሮ በማካተት የመስራት ስልትን መከተል ያስልጋል።

96) ስለሆነም የምግብ ደህንነትን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ለምግብ ደህንነት ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ሃላፊነት መስጠት እና አቅም መገንባት

ለ፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን በማጓጓዣዎች፣ በመጋዘኖች፣ በማከማቻዎች እና በገበያዎች ተፈፃሚ ማድረግ

### የገበያ መረጃ

97) ትክክለኛ እና ጊዜውን የጠበቀ የግብርና ገበያ መረጃ ማቅረብ ለውጤታማ የግብይት ሥርዓት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በድህረ-ምርት ብክነት ዙሪያ የሚሰሩ ሥራዎችን የማስተባበር እና የማገዝ ዓላማ ያለው የድህረ-ምርት ብክነት የምክክር-መድረክ ቢኖርም ሥራ ሙሉ በሙሉ

አልጀመረም። የመረጃ ልውውጥ ለፖሊሲ አውጭዎች፣ ለነጋዴዎች፣ ለተመራማሪዎች፣ ለአርሶ አደሮች እና ሌሎች ተዋኒያን ጠቃሚ ስለሆነ የምክክር-መድረኩ መስራት እንዲችል ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

98) ስለሆነም የገበያ መረጃ አቅርቦትን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።
ሀ፡ የድህረ-ምርት ብክነት የምክክር-መድረክ ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማስቻል
ለ፡ የግብርና መረጃ አያያዝ ሥርዓት መመስረት
ሐ፡ መረጃ የማግኘት መብትን የግብርና ገበያ መረጃ ለማግኘት ተግባራዊ ማድረግ

**የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት**

99) አስተሻሸግ የዓይነት እና የደረጃ አንድ አካል ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት የተለየ በመሆኑ ለብቻ ነጥሎ ማየት ያስፈልጋል። እህል ለመያዝ ጥቅም ላይ የሚውለው የጆንያ ዓይነት እና ጆንያው ጥቅም ላይ የዋለበት መንገድ በሽቀጥ ወይም ምርት ግብይት እና በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። ተገቢ ያልሆነ ጆንያ እና ጆንያውን አግባብ በሌለው መንገድ መጠቀም የድህረ-ምርት ብክነት ሊያስከትል እና የአቅርቦት ሰንሰለቱን ሊጎዳ ይችላል። ስለሆነም ትክክለኛ ጆንያ መመረጡን እና ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ የጆንያውን ዓይነት መወሰን እና እንዴት እንደሚሞላ ደረጃ ማውጣት ያስልጋል።

100) ከድህረ-ምርት አያያዝ ጋር በተያያዘ ለጆንያ ደረጃ ማውጣት ያለው ጠቀሜታ ብዙ ነው። ዋና ዋና ጥቅሞችም የሚሸጠው እህል እኩል መጠን ይኖረዋል፣ ትክክለኛ ናሙና መውሰድ ያስችላል፣ ያለውን የእህል መጠን በትክክል ለማስላት ይረዳል፣ እንዲሁም ለማጓጓዝ እና ለማከማቸት አመች ይሆናል። በተጨማሪም የዓለም የሠራተኞች ድርጅት (International Labour Organisation) አንድ ሠራተኛ ከ 55 ኪ.ግ. በላይ እንዳይሸከም የጆንያ ደረጃ እንዲኖር ያስገድዳል። በሰኔ ወር 1959 ዓም የዓለም የሠራተኞች ድርጅት ባካሄደው 51ኛው መደበኛ ስብሰባ አንድ ጎልማሳ ወንድ መሸከም እና ማጓጓዝ ያለበት ከፍተኛው መጠን 55 ኪ.ግ. እንዲሆን እና ጎልማሳ ሴቶች ደግሞ ከወንዶች በጣም ያነሰ መጠን ያለው ክብደት እንዲሸከሙ እና እንዲያጓጉዙ ውሳኔ አሳልፏል።

101) ለምግብነት ያልተዘጋጀ እህልን ለመሸጥ በ 50 ኪ.ግ መጠን ማሸግ የተለመደ ነው። ድንበር ተሻጋሪ እና ለውጪ ገበያ የሚቀርብ እህል የእርዳታ እህልን ጨምሮ በ 50 ኪ.ግ መጠን ይታሸጋል። በ 50 ኪ.ግ. መጠን ማሸግ ለጥራት ቁጥጥር የሚወሰድ ናሙናን በቀላሉ መውሰድ ያስችላል፣ አያያዝን አመች ያደርጋል፣ ማጓጓዝን ቀላል ያደርጋል እንዲሁም የማከማቻ አያያዝን በተለይም አስተጣጠንን ቀላል ያደርጋል። በተጨማሪም የዚህ ጆንያ መጠን ማከማቻ ውስጥ ለመደርደር ቀላል ስለሆነ ቦታን በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል።

102) ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው ዋና እና ተቀባይነት ያለው የጆንያ መጠን ኩንታል (100 ኪ.ግ) ነው። አንድ ኩንታል ለመሙላት እህልን ከተለያዩ አቅራቢዎች በመሰብሰብ ማደባለቅ ይጠይቃል። ይህ ሂደት የጥራት፣ የዓይነት እና የደረጃ ያለማሟላት ችግር ያመጣል። አነስተኛ መጠን ያላቸው ጆንያዎች መጠቀም አርሶ አደሩ ምርት ሳያደባልቅ አንድ እቃ መሙላት ይችላል። 50 ኪ.ግ. መጠን ያለው ጆንያ ለእህል ገበያ እንደ ዋና ደረጃ ቢወሰድ አርሶ አደሮች ያንን የሚያክል መጠን የማሸግ አካሄድ ወይም ልምድ ያዳብራሉ እንዲሁም ሚዛን ሳያስፈልጋቸው የእህሉን መጠን ወደ ገበያ ከመውሰዳቸው በፊት ያውቃሉ። አርሶ አደሮች በቅድሚያ የእህሉን መጠን ማወቅ ከቻሉ በነጋዴዎች የሚደርስባቸውን ብዝበዛ ማስቀረት ይችላሉ።

103) ስለሆነም አስተሻሸግን እና አያያዝን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ በአብዛኛው የዓለም ክፍል ጥቅም ላይ የዋለውን የ 50 ኪግ የእሽግ መጠን ማስተዋወቅ
ለ፡ ማሸጊያው ከምን ቁስ መሰራት እንዳለበት፣ የማሸጊያው የቁመት እና የወርድ ስፋት ስንት መሆን እንዳለበት፣ የአሰራሩን ዓይነት (የማጠን ሥራን እና ለአየር ጠባይ ተጋላጭነትን እሳቤ ውስጥ ያስገባ አሰራር)፣ ከተሞላ በኋላ አሰፋፉን ወይም አስተሳሰሩን፣ መለያ አፃፃፍ እና ሌሎች የማሸጊያ ዝርዝር ደንቦችን ማውጣት
ሐ፡ ለአያያዝ አመች የሆነውን፣ ፍሰትን እና ብክነትን የሚቀንሰውን እንዲሁም ተባይን እና ዘረ-አይጦችን ለመከላከል የሚያመቸውን አነስተኛ እና በ 50 ኪግ መጠን ያለውን ማሸጊያ በመጠቀም መልካም የመጋዘን አያያዝ ሥርዓትን ማስፋፋት
መ፡ የማይገባ ማሸጊያ መጠቀምን ብሎም የድህረ-ምርት ብክነትን ለማስቀረት እንዲቻል የተለያየ ዲዛይን እና አወቃቀር ያላቸውን ማሸጊያዎች በተገቢ ሁኔታ አርሶ አደሮች እንዲጠቀሙ ማበረታታት

**የመንገድ እና የገበያ መሰረተ-ልማት**

104) የመንገድ እና የገበያ መሰረተ-ልማትን በተመለከተ በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ውስጥ እንደሚከተለው በግልጽ ተቀምጧል፡፡

> የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ መሠረተ-ልማቶች መስፋፋት ለግብርና እና ገጠር ልማት አስፈላጊ ናቸው፡፡ የትምህርት፣ የስልጠና፣ የጤና፣ የገጠር መንገድ እና ትራንስፖርት አገልግሎት በሌለበት ሁኔታ ፈጣን እና ዘለቄታ ያለው የግብርና እና አጠቃላይ የገጠር እድገት ማምጣት አይቻልም፡፡ የገጠር እድገት እና የመሠርተ-ልማት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የማይነጣጠሉ ስለሆኑ እነዚህን የገጠር መሠረተ-ልማቶች መንግስት የማስፋፋት ግዴታ አለበት፡፡ የመንግስት ዋና ሥራ የገጠር መሠረተ-ልማቶችን ማስፋፋት፣ አርሶ አደሮችን ማነቃቃት እና ማስተባበር እንዲሁም በአጠቃላይ ለእድገት አመቺ ሁኔታ መፍጠር ነው (MoFED, 2003)፡፡

105) በቂ እና አመች የሆነ የመንገድ እና የገበያ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ለግብርና በአጠቃላይ አስፈላጊ ቢሆንም የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ እና የገጠሩን ማህበረሰብ ገቢ ለመጨመር እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመገበያያ ወጪ በተለይም የማጓጓዣ ወጪ ከፍተኛ የሚሆነው በዋናነት በደካማ የመንገድ እና የገበያ መሠረተ-ልማት ምክንያት ነው፡፡ ውስን ወይም ደካማ የመንገድ ትስስር ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎ ምርትን በማጓጓዝ የሚካካስ ቢሆንም አብዛኛውን የማካካሻ ክፍያ የሚከፍለው ግን አርሶ አደሩ ነው፡፡ ስለሆነም ግብርናን ለሚያገለግሉ የገበያ መሠረተ-ልማቶች በአጠቃላዩ የአገሪቱ የመሠረተ-ልማት እቀድ ውስጥ ወሳኝ ቦታ መሥጠት ያስፈልጋል፡፡
106) በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንደሚያሳየው የስልክ እና የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ማስፋፋት ቀስበቀስ የሚከናወን እና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ቢሆንም አርሶ አደሮች ትክክለኛ እና ጊዜውን የጠበቀ መረጃ ማግኘት ስላለባቸው ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ቁልፍ የልማት ዘርፍ እንደሆነ ነው፡፡ የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ እድገት የገጠሩን የግብይት መሠረተ-ልማት ለማገዝ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ የአርሶ አደሮችን የግብርና ሸቀጥ ወይም ምርት የዕለት ተዕለት ግብይት እና ንግድ ለማሻሻል እና ለመደገፍ በገጠሩ አካባቢ የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ሽፋንን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡ የሞባይል ባንኪንግ መጠቀም በገጠሩ አካባቢ የቁጠባ ባህልን ሊያመጣ ስለሚችል የቁጠባ መጎልበት ደግሞ ለኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

107) በ 1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ እንደሚያሳየው እያደጉ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች (ለምሳሌ ፀሀይን ፣ ንፋስን ተጠቅሞ ኤሌክትሪክ ማመንጨት) የኤሌክትሪክ አገልግሎትን ለማስፋፋት ቢረዱም እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በገጠሩ አካባቢ ለማዳረስ አሁንም አስቸጋሪ ነው፡፡ በገጠሩ አካባቢ የሀይል አቅርቦትን ማስፋፋት አነስተኛ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ይደግፋል፣ ሥራቸውንም ያሳልጣል እንዲሁም ምርቱ በሚመረትበት እና

ጥቅም ላይ በሚውልበት አካባቢ እሴት መጨመር ያስችላል። ስለሆነም ምርቱን ከማምረቻ ቦታ ወደ ማቀነባበሪያ ቦታ በማጓጓዝ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት ለመቀነስ ይረዳል።

108) ስለሆነም የመንገድ እና የገበያ መሠረተ-ልማትን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ የገጠር መጋቢ መንገዶች ትስስርን ከዋና መንገዶች ጋር በማገናኘት የገጠሩን አካባቢ በቀላሉ እና በአግባቡ የሚያገለግል የትራንስፖርት ሥርዓት በመዘርጋት ምርቶችን በማጓጓዝ ሊደርስ የሚችለውን ብክነት መቀነስ

ለ፡ የትምህርት ደረጃን ለማሻሻል፣ እውነተኛ እና የዕለት መረጃ ለማግኘት፣ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ለመጠቀም እና ሌሎች የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ሊሰጣቸው የሚችለውን ጥቅሞችን የገጠሩ ሕዝብ እንዲያገኝ የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂን ማስፋፋት

ሐ፡ እህል በተመረተበት አካባቢ እንዲቀነባበር በማድረግ በማጓጓዝ እንዲሁም ያልተቀነባበረ ምርት በማከማቸት የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት ለመቀነስ በገጠሩ አካባቢ አነስተኛ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማቋቋም እና እሴት መጨመርን ማስፋፋት

መ፡ እንደ የምርት መፈተሻ ማዕከል የመሳሰሉ አገልግሎት መስጪያ ድርጅቶችን በገጠሩ አካባቢ መመስረት

ሠ፡ በገበያ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ተበረታትተው የግል ድርጅት ለማቋቋም የሚፈልጉ አርሶ አደሮችን እና በገጠሩ አካባቢ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱ ድርጅቶችን ከገንዘብ ብድር እና ቁጠባ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር

## ዋና ዓላማ 3:

## ለድህረ-ምርት አያያዝ የፋይናንስ አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል

**ዳሰሳ**

109) ኢንቨስትመንት የሚለው ቃል የመንግስት እና የግሉ ዘርፍ በተለያዩ የልማት ዘርፎች ከሚያውሉት የመዋዕለ-ንዋይ (ሀብት) ፍሰት ጋር የተያያዘ ቢሆንም አርሶ አደሮች እና ሌሎች ግብርና ተኮር ቢዝነስ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ገቢን እና ቁጠባን ለመጠቀም በየጊዜው የሚወስኑት ውሳኔ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ከእርሻው ጋር ያልተገናኙ ጉዳዮች ካለቁ በኋላ መዋዕለ-ንዋይ (ሀብት) ሥራላይ ሲውል ካለው ሀብት ውስጥ ምን ያክሉ ለማምረት፣ ቴክኖሎጂ ለመግዛት እና ለሌሎች ከእርሻ ጋር ለተያያዙ ነገሮች መዋል አለበት በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ መስጠት ይጠይቃል፡፡ አነስተኛ እና በዋናነት በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ያሉ አርሶ አደሮች ለኢንቨስትመንት የገንዘብ ምንጫቸው ከእርሻቸው የሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ ሆኖም ግን ገቢው እጅግ ዝቀተኛ በመሆኑ ለኢንቨስትመንት መዋል የሚችል የገንዘብ አቅም የላቸውም፡፡ ስለሆነም አርሶ አደሩ የድህረ-ምርት ብክነት መቀነሻ ቴክኖሎጂን ጨምሮ በሌሎች የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ ማዋል የሚችለው የኢንቨስትመንት መጠን በገንዘብ አቅርቦት እጥረት የተወሰነ ነው፡፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች እንዲያድጉ እና ግብርናን ቢዝነስ (ንግድ) ተኮር እንዲያደርጉ መንግስት እና ትልልቅ ድርጅቶች ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

110) የግል ባለሀብቶች በግብርናው ዘርፍ በተለይም በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት እንዲገቡ እና ሀብታቸውን እንዲያፈሱ ዘርፉን ትርፋማ ሊያደርግ የሚያስችል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሊኖር ይገባል፡፡ መንግስት እና የመንግስት አካላት በግብርናው ዘርፍ የሚያፈሱት የኢንቨስትመንት መጠን የግል ባለሀብቶች ሀብታቸውን ግብርና ላይ እንዲያውሉ ለማበረታታት እና ለመሳብ ይጠቅማል፡፡ በመጋቢ መንገዶች፣ በዋና ዋና መንገዶች ትስስር፣ በመረጃ እና በመገናኛ ቴክኖሎጂዎች፣ በኤሌክትሪክ አቅርቦት ወዘተ ላይ መንግስት ስለሚያፈሰው መዋዕለ-ንዋይ ከዚህ ቀደም ተጠቅሷል፡፡ በመንግስት የሚደረግ ማበረታቻ እንደ የተከፈለ ግብር የመመለስ ፕሮግራም በድህረ-ምርት አያያዝ ዙሪያ የኢንቨስትመንትን ፍላጎት እና የገንዘብ አቅርቦትን ይጨምራል፡፡ ቀልጣፋ የሆነ የግብይት ሥርዓት መመስረት እና ማስቀጠል በግብርና እና በድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ሌላው የማበረታቻ ስልት ነው፡፡

**ዓላማ**

111) ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦትን እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ለማሻሻል መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች ዋና ዓለማ የግል ባለሀብቱ በግብርናው ዘርፍ ሀብቱን እንዲያፈስ የሚያበረታታ ሁኔታ መፍጠር፣ በግብርናው የአቅርቦት እና የእሴት ሰንሰለቶች ውስጥ የእርሻ ኢንተርፕራይዞች የተሻሻሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም እንዲችሉ የገንዘብ አቅርቦት ተደራሽነትን ማሻሻል ነው፡፡

**መሰራት የሚገባቸው ተግባራት**

112) እላይ የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ስትራቴጂው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል
ሀ፡ ለድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ገንዘብ መመደብ እና ማፍሰስ
ለ፡ ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራን ያካተተ የገንዘብ አገልግሎት
ሐ፡ አርሶ አደሮችን እና የህብረት ሥራ ማህበራትን በኩታ-ገጠም ማደራጀት

**ለድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ገንዘብ መመደብ እና ማፍሰስ**

113) አነስተኛ አርሶ አደሮች ለግብርና ሥራ በተለይም ለድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ የሚያውሉት ገንዘብ ከገንዘብ ተቋማት ለማግኘት ዋና ችግር ከሆኑት መካከል አርሶ አደሩ ብድሩን መልሶ ለመክፈል የሚያስችል የገቢ አቅም እንዳለው በአጥጋቢ ሁኔታ መገመት ባለመቻሉ ነው። ይህ ችግር ከዋጋ አለመረጋጋት፣ የግብዓት እና የምርት ገበያ ብዙ ጊዜ ለአርሶ አደሩ አመች ያለመሆን፣ ከአየር ንብረት ወይም ከተባይ ጋር በተያያዘ ጉዳት ሰብል መውደም፣ በደካማ መሠረተ-ልማቶች ምክንያት የሚመጣ ከፍተኛ ወጪ ወዘተ ጋር የተገናኘ ነው። እነዚህ ሁሉ ችግሮች አርሶ አደሩ ገንዘብ እንዳይበደር አሉታዊ ተፅዕኖ አላቸው።

114) ስለሆነም የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ውጤታማ እንዲሆን ለመደገፍ ለግብርናው ዘርፍ ገንዘብ ከመመደብ ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ጥሬ-እቃዎችን ከውጪ አስገብተው የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለሚያመርቱ አምራቾች እና/ወይም የዕደ ጥበብ ሙያተኞች ከግብር ጋር በተገናኘ ድጋፍ ማድረግ

ለ፡ የህብረት ሥራ ማህበራትን እና ዩኒየኖችን የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲገዙ እና ለአርሶ አደሮች አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

**ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተ የገንዘብ አገልግሎት**

115) አርሶ አደሮች የገንዘብ ብድር እንዳያገኙ የሚያግዳቸው ሌላው ችግር ለብድሩ በመያዣነት የሚያስይዙት ሀብት አለመኖር ነው። በተለምዶ የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ገንዘብ ለመበደር እንደ ማስያዣ ሲያገለግል ኑሯል። ይህም ማለት የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የለለው አርሶ አደር ብድር አያገኝም ማለት ነው። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ውስጥ መድን እና /ወይም የብድር ዋስትና ፕሮግራም እንደ አማራጭ ባለመኖሩ አነስተኛ አርሶ አደሮች ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ተበዳሪዎች ተብለው በገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ይፈረጃሉ።

116) ቀልጣፋና እና የተደራጀ የገበያ ሥርዓት ባለመኖሩ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝን በመጠቀም አነስተኛ አርሶ አደሮች ገንዘብ መበደር እንዳይችሉ አድርጓል። በተጨማሪም በአብዛኛው የገጠር አካባቢ ባንክ ወይም ሌሎች የገንዘብ ተቋማት ስለሌሉ በተበዳሪው እና በአበዳሪው መካከል ያለው የመረጃ ልውውጥ አስቸጋሪ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ አለመተማመንን ያመጣል። በቅርቡ የተጀመረው ሞባይል ባንኪንግ ሥርዓት ይህን ችግር ሊያቃልል ይችላል።

117) ስለሆነም ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተ የገንዘብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቆጣጠር የሚረዳቸውን ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች መግዛት እንዲችሉ የመድህን (የዋስትና) ፕሮግራም፣ የብድር ዋስትና ፕሮግራም ወይም ሌላ የገንዘብ ማቅረቢያ ሥርዓት መዘርጋት

ለ፡ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያን የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማግኘት እንዲችሉ አዳዲስ የገንዘብ አገልግሎቶችን መስጠት

ሐ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ከሚፈጽሙት የድህረ-ምርት ብክነትን መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች ግዥ ጋር በተገናኘ በዝቅተኛ ወለድ ብድር ከአበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ማግኘት እንዲችሉ ለአነስተኛ አበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ስልታዊ ድጎማ ማድረግ

መ፡ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዮኒየኖች ለአርሶ አደሮች ብድር ማቅረብ እንዲችሉ አቅማቀቸውን መገንባት

## ግብርናዊ- ቢዝነስ፣ የግብርና ኢንተርፕራይዞችን እና ምርት ማቀነባበሪያዎችን በኩታ-ገጠም ማደራጀት

118) የኩታ-ገጠም አደረጃጀት ጽንሰ-ሀሳብ አዲስ ሊሆን ቢችልም መሰረታዊ መርሆዎቹ ግን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሥራዎችን ለማደራጀት ጥቅም ላይ ውለዋል። ከግብርና አኳያ የኩታ-ገጠም አደረጃጀት ጽንሰ-ሀሳብ የአቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋኒያንን አርሶ አደሮችን ጨምሮ በአንድ ላይ በማሰባሰብ ሰፊ መጠን ያለው ሥራ መመስረት ነው። ሰፊ መጠን ያለው የሥራ አደረጃጀት ለብድር አገልግሎት በር ይከፍታል። ምክንያቱም ከግብርና ጋር ለተያያዙ ስጋቶች ኩታ-ገጠሙ አደረጃጀት ዋስትና ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው። የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ ተያያዥነት ያላቸውን የግብርና ሥራዎች (አካላት) በኩታ-ገጠም ማደራጀት ያስፈልጋል።

119) ሌሎች አደረጃጀቶች ለምሳሌ የአርሶ አደሮች ማህበራት፣ የህብረት ሥራ ማህበራት የመሳሰሉት ገንዘብ በማቅረብ፣ ስልጠና በመስጠት፣ የገበያ መረጃ፣ የማከማቻ እና የማጓጓዣ አገልግሎት እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን ስለሚሰጡ ለኩታ-ገጠም አደረጃጀት አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

120) ስለሆነም ለድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ አስተዋፅዖ ያለው ሰፊ የሥራ መጠን (ትልቅ ድርጅት) ለመፍጠር በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያንን በኩታ-ገጠም ከማደራጀት ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ሰፊ የሥራ መጠን በመፍጠር እርስ በእርስ መጠቃቀም እንዲችሉ እና በቀላሉ የገንዘብ ብድር አገልግሎት በማግኘት የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ እንዲችሉ በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ባሉ ተዋንያን መካከል ሽርክና መፍጠር

ለ፡ ለአርሶ አደሮች ስልጠና፣ የገበያ መረጃ፣ የብድር እና ቁጠባ አገልግሎት፣ የመደራደር ክህሎትን እና ሌሎች ከድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በብቃት መስጠት እንዲችሉ የአርሶ አደሮችን ድርጅቶች እና ህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር

## ዋና ዓላማ 4:

# እሴት መጨመርን ማስፋፋት

**ዳሰሳ**

121) በ1995 ዓም የወጣው የገጠር ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ውስጥ እንደ ተመለከተው ለውጤታማ የግብርና ገበያ ሥርዓት ሦስተኛው አስፈላጊ ነገር የህብረት ሥራ ማህበራትን ማስፋፋት እና ማጠናከር ነው። ሌሎች ሁለቱ አስፈላጊ ነገሮች ማለትም ዓይነት እና ደረጃ እና የገበያ መረጃ አቅርቦት ከዚህ በፊት ተብራርተዋል። የህብረት ሥራ ማህበራት እና/ወይም ዩኒየኖች ለግብርና ምርቶች መሰብሰቢያ እና ማከማቻ ቦታ እና ቁሳቁስ ከማቅረብ በተጨማሪ እሴት የተጨመረበት ምርት ለማምረት በተጓዳኝም የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ እንዲችሉ አነስተኛ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን እንዲያቋቁሙ በስትራቴጂው ውስጥ ተቀምጧል። የተደራጀ የግብርና ገበያ ሥርዓት ባለበት ሁኔታ የግል ባለሀብቱም የግብርና ምርቶችን በማቀነባበር ሥራ ቢሰማራ ለድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ የበኩሉን ሊያበረክት ይችላል። የህብረት ሥራ ማህበራቶች እና/ወይም ዩኒየኖች የእርሻ መሣሪያዎችን እና ማሽነሪዎችን በመግዛት እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በግል ለመግዛት ወይም ማግኘት ለማይችሉ አርሶ አደሮች ማከራየት ይችላሉ።

122) በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የማይነጣጠሉ ነገር ግን የየራሳቸው የሆነ ተግዳሮት ያላቸው እና የተለያየ መፍትሄ የሚፈልጉ ሦስት አካላት አሉ። በተጨማሪም እነዚህ አካላት በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ የየራሳቸው የሆነ ሚና እና ተፅዕኖ አላቸው። ከእነዚህ የግብርና እሴት ሰንሰለት አካላት መካከል አንዱ ለግብርና ሥራ ግብዓት በማቅረብ የሚሳተፍ አካል ነው። ግብዓቶችም ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ አግሮ-ኬሚካል እና እንደ ጆንያ ያሉ የማሸጊያ ቁሳቁሶች፣ መመዘኛ መሣሪያዎች እና የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች የመሳሰሉት ናቸው። በአጠቃላይ በግብዓቱ ዘርፍ የሚከሰቱ ሁነቶች በግብርና ሥራ ትርፋማነት ላይ እንዲሁም የድህረ-ምርት ብክነት መጠንን በመቀነስ ከባድ ተፅዕኖ አላቸው።

123) በሌላ መልኩ ደግሞ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች እሴት የተጨመረበት ምርት ለተጠቃሚው ለማቅረብ ከግብርና ሥራ የተገኘ ጥሬ-እቃን ይጠቀማሉ። ስለሆነም በሰንሰለቱ ውስጥ አርሶ አደሩ ሁልጊዜ በግብዓት አቅራቢዎች እና በግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች መካከል ነው። ስለሆነም የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ለእነዚህ የተለያዩ ነገር ግን ለማይነጣጠሉ ሦስት አካላት ማለትም የግብርና ግብዓት አቅርቦት፣ የግብርና ሥራ እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች ላይ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው ልዩ ትኩረት ያደርጋል።

**ዓላማ**

124) እሴት መጨመርን የማስፋፋት ዋና ዓለማ  በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ አድሎ የሌለበት እና ሁሉን-አቀፍ የሆነ እሴት መጨመሪያ ሥርዓት በማስፋፋት የድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ አርሶ አደሩ እና ሸማቹ እንዲጠቀም ማድረግ ነው።

**መሰራት የሚገባቸው ተግባራት**

125) አላይ የተቀመጠውን ዓላማ ለማሳካት ስትራቴጂው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል
ሀ፡ የግብርና ግብዓቶች አቅራቢ
ለ፡ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ

## የግብርና ግብዓት አቅራቢ

126) በሌሎች አገሮች እንዳሉ የግብርና ግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ ድርጅቶችም ለግብርና ሥራ የሚውል የተለያዩ ግብዓቶችን ያመርታሉ። እነሱም

ሀ፡ በድህረ-ምርት ብክነት ላይ ተፅዕኖ ያላቸውን ማጨጃዎች፣ መውቂያዎች፣ ወፍጮዎች የመሳሰሉትን ጨምሮ ሌሎች የእርሻ መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች አምራቾች

ለ፡ ለመስክ እና ለማከማቻ ተባዮች ቁጥጥር የሚውል ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች አምራች እና አከፋፋዮች

ሐ፡ የማሸጊያ ቁሳቁሶች እና እንደ የብረት ጎተራ የመሳሰሉ ማከማቻዎችን አምራቾች

መ፡ ምርት እና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ ምርጥ ዘር አምራቾች

ሠ፡ እንደ የማጓጓዣ መሳሪያዎች እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች ሰጭዎች

127) በመስክ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ለግብርና ሥራ የሚያስፈልጉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን እና መሣሪያዎችን ለማምረት እና ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ዋና ችግራቸው የጥሬ-እቃ ውድነት እንደሆነ ተለይቷል። በተጨማሪም ኢንዱስትሪዎች ምርት የሚያመርቱት ለግብርና ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ለተለያዩ ተጠቃሚዎች ጭምር ነው። በታክስ፣ በወለድ ምጣኔ ወይም መንግስት ለኢንዱስትሪው በሚያደርገው እዳ ስረዛ ምክንያት ኢንዱስትሪው ያመረተውን ወይም የሰራውን እቃ መቆጣጠር አይችልም። ይህም ለተወሰኑ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ድጎማ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች ብድር ለመስጠት፣ እዳ ለመሰረዝ ወይም ገንዘብ ለማቅረብ የግብርና ሥራ ብድር መልሶ ለመክፈል የሚያስችል የገቢ አቅም የለውም የሚል ፍራቻ አለባቸው።

128) ስለሆነም ምርትን በማሻሻል እና የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓቱን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል ግብዓት አቅራቢዎች ያሉበትን ሁኔታ ማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ለግብርናው ሥራ ትርጉም ባለው መጠን ወጭን ለመቀነስ ለግብርና ግብዓት አምራቾች እና አቅራቢዎች የተቀናጀ፣ የተጣጣመ እና ለሚገባው ብቻ ድጎማ ማድረግ

ለ፡ የአገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪ ልማትን ማስፋፋት

## የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ

129) የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ የድህረ-ምርት ብክነትን ቀንሶ የግብርና ምርቶችን ለንግድ፣ ለማከማቸት (ለከመዘን)፣ ለማቀነባበር እና ለማጓጓዝ የሚያመች እንዲሁም ጥራቱ ወደ ተጠበቀ ሸቀጥ የመለወጥ ሂደትን ይይዛል። በምግብ እህል ላይ እሴት ሲጨመር በግብርናው የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያን በሙሉ ሸቀጡ ወይም ምርቱ ዓይነት እና ደረጃ ማሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ለንግድ እና ለማከማቸት የቀረበው ሸቀጥ ወይም ምርት ተፈላጊ የሆኑትን የዓይነት እና ደረጃ መስፈርቶች ማሟላቱን ማረጋገጥ ወሳኝ የእሴት መጨመር ተግባር በመሆኑ ለድህረ-ምርት አያያዝ የጀርባ አጥንት ነው።

130) ስለሆነም በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት ቀንሶ፤ ጥራት ያለው ጥሬ-እቃ ዘላቂነት እና ወጥነት ባለው መንገድ ለማቅረብ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማሻሻል ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ፡ ለግብርና ድርጅቶች የቴክኖሎጂ እና የገንዘብ እንዲሁም የሰው ክህሎትን በማዳበር ድጋፍ ለማድረግ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎች እና በግብርና ድርጅቶች መካከል ሽርክናን ማጠናከር

ለ፡ እሴት የሚጨምሩ የህብረት ሥራ ማህበራትን እና ዩኒየኖችን ማስፋፋት

ሐ፡ እሴትን በመጨመር የምርት ጥራትን መለየት ለሰንሰለቱ ተዋንያን በተለይም ለአርሶ አደሮች ስለሚሰጠው ጥቅም ግንዛቤ መፍጠር እና ማስፋፋት

## ክፍል ፭

## የስትራቴጂ አፈፃፀም ስልት

### ለስኬታማ ትግበራ መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

131) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት (እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር)፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ያሉ የመንግስት አካላት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን በተሳካ ሁኔታ ሥራላይ ለማዋል ከዚህ በታች የተቀመጡት ጉዳዮች ወሳኝ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡
ሀ፡ የኢትዮጵያ ግብርና ወደፊት ሊበለጽግ የሚችል ከፍተኛ አቅም ስላለው ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ዋና አንቀሳቃሽ እና ለምግብ ዋስትና መሻሻል ብሎም ለድህነት ቅነሳ ጉልህ አስተዋፅዖ እንዳለው ግንዛቤ መውሰድ

ለ፡ በድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ረገድ ቶሎ ለውጥ በሚያመጡ ጥቂት ተግባሮች እና ዓላማዎች ላይ ብቻ ማተኮር፤ በአንድ ጊዜ መሰራት ለሚገባቸው ለጥቂት ጉዳዮች እና ሰብሎች ብቻ ትኩረት መስጠት

ሐ፡ ለስትራቴጂው በጀት (ገንዘብ) መመደብ እና ጠንካራ የፖለቲካ ቁርጠኝነት መኖር

መ፡ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ጠንካራ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት መመስረት

ሠ፡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወደ ስትራቴጂ ትግበራው ሙሉ በሙሉ እንዲገቡ የድህረ-ምርት ልቀት ማዕከል፣ ውጤታማ የምክክር-መድረኮች ግንኙነት፣ ተቋም (ለምሳሌ የኢትዮጵያ የድህረ-ምርት አያያዝ ባለሙያዎች ማህበር) የመሳሰሉትን ማቋቋም እና ማጠናከር

ረ፡ የገንዘብ ተቋማት ግብርናውን እንዲደግፉ ማበረታታት

ሰ፡ የግብርናውን እድገት (ልማት) ለመደገፍ ወሳኝ የሆኑ መሰረተ-ልማቶችን እንደ መጓጓዣ (ትራንስፖርት) እና የመንገዶች ትስስር፣ የመረጃ እና ግንኙነት ቴክኖሎጂ፣ ኤሌክትሪክ እና ሌሎች ከገበያ ጋር የተገናኙ መሰረተ-ልማቶችን መመስረት

ሸ፡ ሥርዓተ-ፆታን፣ ወጣቶችን፣ ኤች.አይ. ቪ/ ኤድስን፣ ከአካባቢ ጋር የተያያዙ ነገሮችን (የአየር ንብረት እና ሌሎች ተለዋዋጭ ነገሮችን) በሁሉም ደረጃ ግንባር ቀደም አጀንዳዎች ማድረግ

### የእቅድ እና ትግበራ ምዕራፍ (ደረጃ)

132) ይህ ስትራቴጂ በአምስት ዓመት የትግበራ ምዕራፍ ተከፋፍሎ እንዲሰራ የታሰበ ሲሆን ቀጣይነቱም በመጀመሪያው አምስት ዓመት በሚገኘው ልምድ እና ውጤት መሰረት ይሆናል፡፡ እንዲሰሩ የተለዩትን ጉዳዮች (ተግባሮች) እንደ ክብደታቸው (አንገብጋቢነታቸው) በቅደም-ተከተል በማስቀመጥ በአጭር ጊዜ እና በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ ፈጣን ለውጥ የሚያመጡትን በቅድሚያ መፈፀም፡፡ ሆኖም ግን አሁን መጀመር ያለባቸው ነገር ግን በረጅም ጊዜ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች አይጀመሩ ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ ተግባራት በተገቢው ጊዜ እንዲጀመሩ ፕሮግራም ይወጣላቸዋል፡፡

133) ስለሆነም ይህ ስትራቴጂ ወደ ተግባር እንዲለወጥ የውጤት ማዕቀፍ፣ የኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅድ እና የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ተዘጋጅቷል፡፡ እነዚህ ሥራዎች በራሳቸው የሚቆሙ ስለሆነ በዚህ ስትራቴጂ ውስጥ በሙሉ ቁመና አልተዘጋጁም፡፡ ሆኖም ግን የሚቀጥሉት ንዑስ ክፍሎች ስለ እያንዳንዳቸው አጫጭር ገለጻ ይሰጣሉ፡፡

### የውጤት ማዕቀፍ

134) የውጤት ማዕቀፍ እቅድ ለማቀድ እና የክትትል እና የግምገማ ሥራ ለመስራት የሚረዳ ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ የውጤት ማዕቀፍ የስትራቴጂውን የውጤቶች ሰንሰለት ያንፀባርቃል፣ እንዲሁም ለክትትል መመዘኛ (አመላካቾች እና ዒላማዎችን) ይሰጣል፣ ሥራው እንደታቀደው ወደ ሚጠበቁት ውጤቶች፣ ተፅዕኖዎች እና ለውጦች እያመራ እንደሆነ ለመገምገም ይጠቅማል፡፡ የውጤት ማዕቀፍ ስትራቴጂው ሥራላይ በሚውልበት ወቅት ኢንቨስትመንትን ለማስተካከል እና ለማስተባበር የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡ ከአጠቃላይ የስትራቴጂ ማዕቀፍ መሰረታዊ ደንቦች እና በዚህ ሰነድ ውስጥ እንዲሰሩ የተለዩትን ተግባራት መሰረት በማድረግ ስትራቴጂውን ሥራላይ ለማዋል እንዲረዳ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የውጤት ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፡፡ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ የውጤት ማዕቀፍ ሞዴል በአዝል 2 ተቀምጧል፡፡

### የኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅድ

135) ከውጤት ማዕቀፍ በመነሳት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅድ ተሰርቷል፡፡ በእያንዳንዱ የአምስት ዓመት የትግበራ ምዕራፍ የሚፈጸሙ ፕሮግራሞችን እና ንዑስ-ፕሮግራሞችን ከውጤት ማዕቀፍ ውስጥ በማውጣት ከሚጠበቀው ወጪ ጋር በኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅድ ውስጥ ተሳስረው ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም የኢንቨስትመንት እቅዱ ስትራቴጂው ሥራላይ የሚውልበትን መንገድ እና በአፈፃፀም ጊዜ መኖር ያለበትን የተቋማዊ፣ የድርጅታዊ እና አስተዳደራዊ አወቃቀር ጭምር ያሳያል፡፡

136) በተጨማሪም የኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅዱ ወጪ እና በጀትን፣ የገንዘቡን ምንጭ ዓይነት፣ የገንዘቡን ደረጃ እና መጠን እና ሌሎችንም መረጃዎች ይሰጣል፡፡

### ክትትል እና ግምገማ

137) የስትራቴጂው ክትትል እና ግምገማ አካሄድ ውጤትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይመከራል፡፡ ውጤትን መሰረት ያደረገ ማለት ለግብ ወይም ለተፅዕኖ አስተዋፅዖ የሚያበረክቱት ውጤቶች ስኬት ላይ፣ ተቋማት እና የባለድርሻ አካለት ስለስትራቴጂው እና ስትራቴጂው ስላለው ተፅዕኖ ያላቸው እውቀት መሻሻል፣ ውሳኔ የመወሰን ችሎታ መሻሻል እና የተጠያቂነትን ባህል ማስፋፋት የመሳሰሉት ላይ ትኩረት ማድረግ ነው፡፡

138) ስለሆነም የስትራቴጂው ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ውጤታማ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ሁለንተናዊ ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የባለድርሻ አካላት በሥርዓቱ መግባት ወይም መሳተፍ በስትራቴጂው ትግበራ ወቅት ግልጽነትን ያሰፍናል፣ የምክክር መድረክ ይፈጥራል እንዲሁም የባለቤትነት ስሜትን ይጨምራል፡፡

139) በተጨማሪም የስትራቴጂው ክትትል እና ግምገማ ሊፈፀም የሚችል ሂደትን መሰረት ያደረገ፣ ተጨባጭ እና ሊለኩ የሚችሉ መመዘኛዎችን የያዘ፣ ቀላል፣ ጊዜ እና ወጪ ቆጣቢ መሆን እና ከአፍሪካ ሁሉን አቀፍ የግብርና እድገት ፕሮገራም እና ከማላቦ ስምምነት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

## ስጋት እና ሌሎች ታሳቢዎች

140) ከዚህ ስትራቴጂ ጋር በተገናኘ ሊገጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና ሌሎች ታሳቢዎች በውጤት ማዕቀፍ እና በኢንቨስትመንት እና የትግበራ እቅድ ውስጥ ተዘርዝረዋል።

# ክፍል ፮

# በድህረ-ምርት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች

## የፕሮግራም ቅደም ተከተል

በመጀመሪያው የአምስት ዓመት (2010/11- 2014/15) ትግበራ ምዕራፍ የሚሰሩ ፕሮግራሞች በውጤት ማዕቀፉ መሰረት በቅደም ተከተል ተለይተዋል። እያንዳንዱ ፕሮግራም በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ንዑስ-ፕሮግራም የተከፋፈለ ነው። ለእያንዳንዱ ንዑስ ፕሮግራም በርከት ያሉ ሊሰሩ የሚገባቸው *ሥራዎች* (እዝል 1 እና ከሠንጠረዥ *ሀ* እስከ *መ* ይመልከቱ) ተዘርዝረዋል። እነሱም የሚከተሉት ናቸው።

## ፕሮግራም 1: *የምግብ ብክነትን መቀነስ*

የምግብ ብክነትን መቀነስ ውጤት ዓላማ ለሰው ፍጆታ ተስማሚ በሆነ መልኩ የምግብ አቅርቦትን በከፍተኛ ደረጃ ማሻሻል ነው።

**ለዚህ ዓላማ ስኬት አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ አምስት ዋና ዋና *ሥራዎች* እና ሌሎች መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተዋል**

***ንዑስ-ፕሮግራም 1.1: ውጤታማ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ማስፋፋት***

ውጤታማ የድህረ-ምርት አያያዝ *ሥርዓትን* ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፡-

*ሀ*፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ አመች የሆነ የተቋም የክትትል እና የግምገማ *ሥርዓትን* ጨምሮ እና የአሰራር መዋቅር በመመስረት እና በማጠናከር ለመንግስታዊ ድርጅቶች እና ለግሉ ዘርፍ ግልጽ ሀላፊነት እና ሚና ከተጠያቂነት ጋር መስጠት

ለ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ *ሥርዓት* ውስጥ ያሉትን መልካም ተሞክሮዎች በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ማስተማር እና ማስፋፋት

ሐ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ *ሥርዓትን* የሚያስተባብር የተለያዩ ዘርፎችን (ግብርና፣ ጤና፣ *ሥነ*ምግብ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ወዘተ) ያካተተ አስተባባሪ መመስረት

መ፡ በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ለሚሰሩ *ሥራዎች* በቂ ገንዘብ መመደብ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ ናቸው

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም *ሥራዎች* ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

***ሀ*: ሁሉን ዓቀፍ የሆነ በፌደራል፣ በክልል እና በወረዳ ደረጃ የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ መመስረት እና ማጎልበት**

**ለ፡ በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር *ሥር* በሁሉም ደረጃ የድህረ-ምርት ክፍል መክፈት እና ማጠናከር**

**ሐ፡ የድህረ-ምርት አያያዝን ለማስፋፋት የድህረ-ምርት አያያዝ መገናኛ እና ግንዛቤ መፍጠሪያ እቅድ ማዘጋጀት**

**መ፡ ዓመታዊ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ኤግዚቢሽን መመስረት**

### *ንዑስ-ፕሮግራም 1.2: የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ የማላመድ ምርምርን እና ልማትን ማስፋፋት*

*የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ የማላመድ ምርምርን እና ልማትን ለማስፋፋት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች*

*ሀ፡ የምርምር እና ልማት ተቋማት እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎች በድህረ-ምርት አያያዝ ዙሪያ ምርምር እንዲሰሩ እና ስልጠና እንዲሰጡ ማመቻቸት*

*ለ፡ የመንግስት እና የግል ዘርፉ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ በጋራ ምርምር እና ልማት እንድሰሩ ማበረታታት*

*ሐ. በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ በሁሉም ደረጃ የሚከሰተውን ብክነት በመጠን እና በገንዘብ ተመን ለመለካት እንዲሁም ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚረዱ በጥናት የተደገፉ ማስረጃዎችን ለማመንጨት የሚካሄዱ ጥናቶችን መደገፍ*

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ ስለድህረ-ምርት አያያዝ የተግባር ትምህርት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመስረት እና መቆጣጠር***
***ለ፡ በመስክ እና በቤተ-ሙከራ (ላቦራቶሪ) ውስጥ ለሚሰሩ የድህረ-ምርት ግመታ እና ትንተና ሥራዎችን ለመደገፍ ለዩኒቨርሲቲዎች እና /ወይም ለምርምር ተቋማት ገንዘብ በውድድር የመስጫ ሥርዓት መመስረት***
***ሐ፡ በየዓመቱ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት የሚዘግብ ዓመታዊ የስታትስቲክስ መጽሔት ማተም መጀመር***
***መ፡ ለድህረ-ምርት ግምገማ የሚውሉ ግልጽ አካሄዶችን እና መንገዶችን ማውጣት***
***ሠ፡ ተደራሽ የሆኑ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን ከውጪ በማስገባት ማላመድ እና ማስፋፋት***
***ረ፡ የምግብ ብክነትን ለመቀነስ የድህረ-ምርት አያያዝ ዘዴዎችን እና ቴክኒኮችን ማላመድ እና ማስፋፋት***
***ሰ፡ ምግብ ሳይበላሽ ለማቆየት የሚያስችሉ አዳዲስ የምግብ አዘገጃጀት ዘዴዎችን ማሰፋፋት***

### *ንዑስ-ፕሮግራም 1.3: የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማመንጨት እና ማሰራጨት*

*የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለማመንጨት እና ለማሰራጨት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፡-*

*ሀ፡ አግባብነት ያለው እና ተደራሽ የሆነ ቴክኖሎጂ በማንጨት አጨዳን፣ ውቂያን፣ ማድረቅን፣ ማሸግን፣ ማጓጓዝን እና የማከማቸት ሥራን በማገዝ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀንስ ተቀናጅተው የሚሰሩ ምርምሮች እና ልማቶችን ማስፋፋት*
*ለ፡ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ እንዲሁም ለጥገና እና ሰርቪስ አገልግሎት የሚውል የገንዘብ አቅም እንዲኖር አበረታች እና በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የገንዘብ አቅርቦት መፍጠር*

*ሐ. የድህረ-ምርት ብክነትን የሚያስከትሉ ማሽነሪዎችን ብቃት ለማሻሻል መሣሪያዎችን ወይም ማሽኖችን የሚያንቀሳቅሱ እና የሚጠግኑ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት*

መ፡ ስለመሣሪያው አጠቃቀም የተሰጡትን ዝርዝር ደንቦች ተጠቃሚቀው እንዲከተል የሚያስገድድ የቁጥጥር ማዕቀፍ እና አስፈጻሚ ተቋም መመስረት

ሠ፡ የመሣሪያ እና የማሽነሪ ጥገና እና የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ማቋቋም እና ማስፋፋት

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ የሜካናይዜሽን ስትራቴጂን ለመተግበር የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን መለየት እና ተያያዥ ኢንቨስትመንት እቀድ ማውጣት**

**ለ፡ ቅድሚያ የተሰጣቸውን የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ወይም እንዲገጣጠሙ እና እንዲሰራጩ ማበረታታት**

**ሐ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በተግባር ለማሳየት ስርቶማሳያ ማዕከላትን መመስረት**

**ሠ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ ማሽኖች ጥገና፣ ማቆያ፣ ማሰልጠኛ እና የኪራይ አገልግሎት መስጫ ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር እንዲሁም ከ RTCs ጋር በማጣጣም በወረዳ ደረጃ የአገልግሎት ማዕከላትን ማቋቋም**

**ረ፡ በወረዳ ደረጃ ለሚመሰረቱት የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎች ማሟላት**

**ሰ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን ዲዛይን፣ አመራረት እና ብቃት ደረጃ መሟላቱን ለማወቅ ብሔራዊ የቁጥጥር እና የማስፈፀሚያ ሥርዓት መመስረት**

**ሸ፡ ለማሽነሪዎች የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ ለመፈተሽ ብሔራዊ የመፈተሻ እና ማረጋገጫ ማዕከል ለማቋቋም የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ**

### *ንዑስ-ፕሮግራም 1.4: በድህረ-ምርት አያያዝ የክህሎት፣ ስልጠና እና የሰው ልማትን ማሻሻል*

በድህረ-ምርት አያያዝ የክህሎት፣ ስልጠና እና የሰው ልማትን ማሻሻል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል

ሀ፡ በግብርና ሙያ እና ቴክኒክ ስልጠና ኮሌጆች እና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለሚሰጡ የድህረ-ምርት የጽንሰ-ሀሳብ እና የተግባር ስልጠናዎቸ የሚያገለግል ድህረ-ምርትን ያካተተ ጠንካራ ሥርዓተ- ትምህርት

ለ፡ ስለ ድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ስልጠና የሚሰጡ የልቀት ማዕከላትን መመስረት

ሐ. በድህረ-ምርት ብክነት፣ መንስኤ እና መፍትሄዎች ዙሪያ ያሉ ሳይንሳዊ እና አገር-በቀል እውቀቶችን ማሰራጨት

መ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ለሰለጠኑ ባለሙያዎች ማበረታቻ መስጠት እና የሥራ እድል ማመቻቸት

ሠ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ በሚሰሩ የክህሎት እና የሰው ልማት ሥራዎች ውስጥ ሥርዓተ-ፆታን በተለይም ለሴቶች እና ለወጣቶች ትኩረት መስጠት

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ በዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ውስጥ የድህረ-ምርት ኢንጂነሪንግ ፕሮግራም**

ለመጀመር የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ

ለ፡ ለአርሶ አደሮች እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የንግድ (የቢዝነስ) አያያዝ ክህሎትን የሚያበለጽጉ ስልጠናዎችን ለሚሰጡ የስልጠና ማዕከላት በጀት መመደብ

ሐ፡ ከግል ባላሀብቶች ጋር በመተባበር የድህረ-ምርት አያያዝ የስልጠና ወይም የመለማመጃ ፕሮግራም መመስረት እና እንደ ሙያ እውቅና መስጠት

መ፡ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን በድህረ-ምርት አያያዝ ባለሙያዎች ማጠናከር

ሠ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ የአገር-በቀል እውቀቶችን ጨምሮ አገልግሎት የሚሰጡ የልቀት፣ የስልጠና እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማጠናከር

ረ፡ የድህረ-ምርት አያያዝን ጨምሮ ደረጃ እንዲያወጣና እንዲፈትሽ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ቢሮን ማጠናከር

ሰ፡ የልማት ሠራተኞች ስለድህረ-ምርት አያያዝ ያላቸውን እውቀት ለማበልጸግ ለግብርና ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ

ሸ፡ በልማት ሠራተኞች የፓኬጅ መመሪያ ውስጥ የድህረ-ምርት አያያዝ ፓኬጅን መጨመር

ቀ፡ ሴቶች እና ወጣቶች ላይ ያተኮረ ስለድህረ-ምርት አያያዝ መሰረታዊ እውቀትን የሚያስጨብጥ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም መጀመር

በ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎች ላይ የጥገና እና አያያዝ አገልግሎት በመስጠት ሴቶች እና ወጣቶች እንዲሳተፉ ማስቻል

ተ፡ መልካም የግብርና አሰራርን የተሻሻለ  የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኒክን ጨምሮ ለመጠቀም የብሀሪ ለውጥን ማስፋፋት

*ንዑስ-ፕሮግራም 1.5: ዘላቂነት ያለው የአካባቢ አያያዝን ማስፋፋት*

ዘላቂነት ያለው የአካባቢ አያያዝን ማስፋፋት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል

ሀ፡ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን መዘርጋት እና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ የግብርና አመራረት ዘዴዎችን በመጠቀም የእጽዋት ሽፋን እንዲጨምር ማድረግ፡፡ የአፈር መከላትን መቀነስ፣ በእጽዋት የተወሰዱ ወይም በአፈር መሸርሸር የተወገዱ ማዕድናትን መተካት፣ የውሀ ፍጥነትን እና የሚባክነውን ይዘት መጠን ለመቀነስ እርከን ፣ የአፈር ክትር ወዘተ መስራት

ለ፡ ከድህረ-ምርት ተግባራት ጋር በተያያዘ የጠፉ ደንን እንደገና እንዲለማ ማድረግ እና ደንን ለኢኮኖሚያዊ እና ለሥርዓተ-ምህዳር (ኢኮሲስተም) ጥቅም እንዲውሉ እንደገና መትከል እና መጠበቅ

ሐ፡ የተቀናጀ ተባይ መከላከልን በመተግበር የፀረ-ተባይ እና የሌሎች ኬሚካሎችን አጠቃቀምን መከታተል እና መቆጣጠር፣ የፀረ-ተባይ ሽያጭን፣ አጠቃቀምን እና አወጋገድን በህጋዊ መንገድ ማስከበር

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

ሀ፡ ስለአግሮ-ኬሚካል (ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር) አጠቃቀም፣ አሻሻጥ፣ አያያዝ እና አወጋገድ መመሪያ ማውጣት

ለ፡ ስለአግሮ-ኬሚካል (ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር) አጠቃቀም፣ አሻሻጥ፣ አያያዝ እና አወጋገድ የወጣውን መመሪያ ለሚያስፈጽሙ አካላት አስፈላጊ ነገሮችን ማሟላት እና ማጠናከር

ሐ፡ ስለአግሮ-ኬሚካል (ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር) አጠቃቀም፣

**አሻሻጥ፣ አያያዝ እና አወጋገድ የስልጠና ፕሮግራም መጀመር**

**መ፡ ስልጠና፣ እውቅና እና ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡ የተመሰከረላቸው የኬሚካል አያያዝ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ መደገፍ**

**ሠ፡ ፀረ-ተባይን ያለአግባብ መጠቀም ከድህረ-ምርት አያያዝ ጋር በተገናኘ ጨምሮ ስላለው ያልተፈለገ ጉዳት ግንዛቤ መፍጠር**

**ፕሮግራም 2፡ የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያ ቅልጥፍና ማሻሻል**

የዚህ ውጤት ጥቅል ዓላማ በትክክለኛው ስዓት፣ በትክክለኛው ቦታ፣ በተገቢ ዋጋ እና ጥራቱ የታወቀ ምርት ለገበያ ማቅረብ የሚያስችል ቀልጣፋ እና ውጤታማ የግብርና ገበያ ሥርዓት መፍጠር እና በተጓዳኝ የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ሥርዓትን መተግበር እና ማስፋፋት ነው፡፡

**ለዚህ ዓላማ ስኬት አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ ሰባት ዋና ዋና ሥራዎች እና ሌሎች መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች ተለይተዋል**

*ንዑስ-ፕሮግራም 2.1: ዘለቄታ ያለው እና ተደራሽ የሆነ የድህረ-ምርት ሥርዓት ማስፋፋት*

ዘለቄታ ያለው እና ተደራሽ የሆነ የድህረ-ምርት ሥርዓት ማስፋፋት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-

ሀ፡ ለእያንዳንዱ የአቅርቦት ሰንሰለት ደረጃ ተስማሚ እና ተደራሽ የሆነ ማከማቻ በቤት (በአባወራ)፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን እና በክልል ደረጃ ማቋቋም

ለ፡ ውጤታማ እና ተደራሽ የሆኑ የማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን ለምሳሌ የብረት ጎተራ እና የተሻሻሉ አገር-በቀል ማከማቻዎችን ማምረት እና በሰፊው የማሰራጨት ሥራን ማሳለጥ እና ማስፋፋት

ሐ፡ በማከማቻ መሰረተ-ልማት አቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ የመንግሰት እና የግል ዘርፉን ማስተሳሰር

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ የተሻሻሉ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን ማስፋፋት**

**ለ፡ በሁሉም ሥርዓት ተቀባይነት እና ታማኝነት ያለው የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ሥርዓትን ማስፋፋት**

**ሐ፡ የተሻሻሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ መደገፍ**

**መ፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ ለሚያመርቱ አምራቾች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ የግብር እፎይታ እና የመሳሰሉትን ድጋፎች ማድረግ**

**ሠ፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን እንዲያሰራጩ የግብርና ግብዓት ነጋዴዎችን ማስፋፋት**

*ንዑስ-ፕሮግራም 2.2፡ ውጤታማ የማከማቻ አያያዝ ሥርዓትን ሥራላይ ማዋል*

ውጤታማ የማከማቻ አያያዝ ሥርዓትን ሥራላይ ማዋል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል

ሀ፡ ከምግብ ደህንነት ጋር የተያያዙ እንደ የማከማቻ ቦታ ስፋት፣ የእህል ንጽህና እና ጥራትን ለመሳሰሉት ጉዳዮች ደረጃ ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ

ለ፡ የማጠኛ ፀረ-ተባዮችን አጠቃቀም እና አወጋገድ ጨምሮ ተገቢ የሆነ የማከማቻ ተባዮች መቆጣጠሪያ መንገዶችን ማስተዋወቅ እና ማስፋፋት

ሐ፡ ለመጋዘኖች ደረጃ መስጠት እና ደረጃ ላሟሉ እውቅና የመስጠትን ሥርዓት ማስፋፋት

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መስራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ የመጋዘን ደረጃ አጽዳቂ እና ቁጥጥር ሥርዓትን መዘርጋት**
**ለ፡ የመጋዘን ደረጃ አጽዳቂ እና ቁጥጥር ኤጀንሲ ማቋቋም**
**ሐ፡ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን መጋዘኖች በተለይም በአነስተኛ (የገጠር) የገበያ ቦታዎች ግንባታን መደገፍ**
**መ፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን ያገናዘበ የእህል አያያዝ፣ የመጋዘን አስተዳደር እና መጋዘን ውስጥ ለሚሰሩ ሥራዎች መመሪያ ማውጣት**
**ሠ፡ ለማከማቻ ተባዮች ቁጥጥር የተቀናጀ ተባይ መከላከል ሥርዓትን ማጠናከር**
**ረ፡ የመጋዘን ሠራተኞችን በእህል አያያዝ እና አስተዳደር ማሰልጠን**
**ሰ፡ ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካሎችን የምዝገባ፣ የአያያዝ፣ የአስተዳደር እና የቁጥጥር ሥርዓትን ማዘመን**

### *ንዑስ-ፕሮግራም 2.3: የትራንስፖርት ሥርዓትን እና የግብይት ትስስርን ማሻሻል*

የትራንስፖርት ሥርዓትን እና የግብይት ትስስርን ማሻሻል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-

ሀ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ምርታቸውን ከማሳ ወደ ቤታቸው ወይም ከቤታቸው ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የሚያስችሉ አነስተኛ እና ጉልበት ቆጣቢ የማጓጓዣ መሳሪያዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጥሙ ድርጅቶች በየአካባቢው እንዲፈጠሩ እና እንዲጎለብቱ ማመቻቸት
ለ፡ የመጋቢ እና የዋና ዋና መንገዶችን ትስስር ማሻሻል እና ማልማት
ሐ፡ ሸቀጦችን ከወረዳ ወደ ዞን፣ ከዞን ወደ ክልል ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎችን ግዥ መደገፍ
መ፡ የትምህርት ደረጃን ለማሻሻል፣ እውነተኛ እና የዕለት መረጃ ለማግኘት፣ ሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ለመጠቀም እና ሌሎች የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ሊሰጣቸው የሚችለውን ጥቅሞችን የገጠሩ ሕዝብ እንዲያገኝ የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂን ማስፋፋት
ሠ፡ እንደ የምርት መፈተሻ ማዕከል የመሳሰሉ አገልግሎት መስጪያ ድርጅቶችን በገጠሩ አካባቢ መመስረት
ረ፡ በገበያ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ተበረታትተው የግል ድርጅት ለማቋቋም የሚፈልጉ አርሶ አደሮችን እና በገጠሩ አካባቢ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱ ድርጅቶችን ከገንዘብ ብድር እና ቁጠባ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መስራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ አነስተኛ መጠን ያላቸውን የግብርና እና በእርሻ ደረጃ የማጓጓዣ መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ መደገፍ**
**ለ፡ አማራጭ የተሻሻለ የእርሻ ትራንስፖርት ሥርዓት ማስፋፋት**
**ሐ፡ መጋቢ መንገዶችን ማሻሻል እና ጥገናን መደገፍ**
**መ፡ ሞባይልን በመሳሰሉ መሳሪያዎች መረጃ ማስተላለፍን ለማሳለጥ አግባብ ያለው የመረጃ እና ግንኙነት ቴክኖሎጂን መንደፍን እና ሥራላይ ማዋልን ማበረታታት**

*ንዑስ-ፕሮግራም 2.4፡ ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል*

*ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-*

*ሀ፡ ዓለም ዓቀፍ የእህል ዓይነት እና ደረጃን እንደ መነሻ በመጠቀም ለሰብል ምርቶች ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት*
*ለ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓቱን የሚደግፉ የጥራት መፈተሻ ቤተ-ሙከራዎችን (ላቦራቶሪዎችን) ማቋቋም*
*ሐ. የተሻሻሉ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥራዎች ይበልጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ዋጋ እንደ ምርቱ የጥራት ደረጃ እንዲከፈል የሚያደርግ ሥርዓት መመስረት*
*መ፡ የወጡትን የዓይነት እና ደረጃ ደንቦች ለሚያስፈጽሙ አካላት የአቅም ግንባታ ማድረግ*

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ የእህል ዓይነትን እና ደረጃን ማሻሻል***
***ለ፡ የዓይነት፣ የደረጃ  እና የጥራት ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር***
***ሐ፡ የዓይነት፣ የደረጃ  እና የጥራት መፈተሻ እና ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋም***
***መ፡ የተመሰከረለትን ዓይነት፣ ደረጃ እና ጥራት ለሚቀጣጠሩ ተቋሞች ድጋፍ ማድረግ***
***ሠ፡ የቤተ-ሙከራ ቴክኒሻኖችን በዓይነት፣ በደረጃ እና በጥራት ፍተሻ ላይ ማሰልጠን***

*ንዑስ-ፕሮግራም 2.5፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል*

*የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-*

*ሀ፡ ለምግብ ደህንነት ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ሃላፊነት መስጠት እና አቅም መገንባት*
*ለ፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን በማጓጓዣዎች፣ በመጋዘኖች፣ በማከማቻዎች እና በገበያዎች ተፈፃሚ ማድረግ*

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን ሥራላይ እንዲያውል፣ ክትልል እና ተፈጻሚ እንዲያደርግ የምግብ እና ደህንት ተቆጣጣሪን እንደገና ማቋቋም***
***ለ፡ የምግብ ደህንነት መርማሪዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማሟላት***
***ሐ፡ የምግብ ደህንነት እና ከምግብ ደህንነት ጋር የተያያዙ የመጋዘን እና የትራንስፖርት ደረጃዎችን መገምገም እና ማሻሻል***
***መ፡ የምግብ ደህንነት መርማሪዎችን በምግብ ደህነት ላይ ማሰልጠን***

*ንዑስ-ፕሮግራም 2.6፡ የግብርና ገበያ የመረጃ ሥርዓትን ማሳደግ*

*የግብርና ገበያ የመረጃ ሥርዓትን ማሳደግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-*

*ሀ፡ የድህረ-ምርት ብክነት የምክክር-መድረክ ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማስቻል*
*ለ፡ የግብርና መረጃ አያያዝ ሥርዓት መመስረት*
*ሐ፡ መረጃ የማግኘት መብትን የግብርና ገበያ መረጃ ለማግኘት ተግባራዊ ማድረግ*

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ የግብርና ገበያ መረጃ ሥርዓት መመስረት***
***ለ፡ የምርት ግብይትን እና ልውውጥን ማሳደግ***

### *ንዑስ-ፕሮግራም 2.7: የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል*

የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት ማውጣት እና በሥራላይ ማዋል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-

ሀ፡ በአብዛኛው የዓለም ክፍል ጥቅም ላይ የዋለውን የ 50 ኪግ የእሽግ መጠን ማስፋፋት
ለ፡ ማሸጊያው ከምን ቁስ መሰራት እንዳለበት፣ የማሸጊያው የቁመት እና የወርድ ስፋት ስንት መሆን እንዳለበት፣ የአሰራሩን ዓይነት (የማጠን ሥራ እና ለአየር ጠባይ ተጋላጭነትን እሳቤ ውስጥ ያስገባ አሰራር)፣ ከተሞላ በኋለ አሰፋፉን ወይም አስተሳሰሩን፣ መለያ አፃፃፍ እና ሌሎች የማሸጊያ ዝርዝር ደንቦችን ማውጣት
ሐ፡ ለአያያዝ አመች የሆነውን፣ ፍሰትን እና ብክነትን የሚቀንሰውን እዲሁም ተባይን እና ዘረ-አይጦችን ለመከላከል የሚያመቸውን አነስተኛ እና በ 50 ኪግ መጠን ያለውን ማሸጊያ በመጠቀም መልካም የመጋዘን አያያዝ ሥርዓትን ማስፋፋት
መ፡ የማይገባ ማሸጊያ መጠቀምን ብሎም የድህረ-ምርት ብክነትን ለማስቀረት እንዲቻል የተለያየ ዲዛይን እና አወቃቀር ያላቸውን ማሸጊያዎች በተገቢ ሁኔታ አርሶ አደሮች እንዲጠቀሙ ማበረታታት

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ የማሸጊያውን ዓይነት፣ ጥቅም እና ጥራት የመሳሰሉትን መስፈርቶች ከዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም የአስተሻሸግ ደረጃ ማውጣት***
***ለ፡ አየርአልባ ከረጢትን (ጆንያዎችን) መጠቀምን ማስፋፋት***
***ሐ፡ የማዳበሪያ ከረጢት እና አየርአልባ ከረጢትን በአገር ውስጥ እንዲሰሩ ማበረታታት***

## ፕሮግራም 3: ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነተን ማሻሻል

የዚህ ውጤት ዋና ዓለማ የግል ባለሀብቱ በግብርናው ዘርፍ ሀብቱን እንዲያፈስ የሚያበረታታ ሁኔታ መፍጠር፣ በግብርናው የአቅርቦት ሰንሰለት እና የእሴት ሰንሰለቶች ውስጥ የግብርና ኢንተርፕራይዞች የተሻሻሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም እንዲችሉ የገንዘብ አቅርቦት ተደራሽነትን ማሻሻል ነው፡፡

### *ንዑስ-ፕሮግራም 3.1: ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ አቅርቦት ተደራሽነትን እና ኢንቨስትመንትን ማሻሻል*

ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ አቅርቦት ተደራሽነትን እና ኢንቨስትመንትን ማሻሻል የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-

*ሀ፡ ጥሬ-እቃዎችን ከውጪ አስገብተው የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለሚያመርቱ አምራቾች እና/ወይም የዕደ ጥበብ ሙያተኞች ከግብር ጋር በተገናኘ ድጋፍ ማድረግ*

*ለ፡ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒየኖች የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲገዙና ለአርሶ አደሮች አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት*

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ በከፊል አገር ውስጥ ለተገጣጠሙ ወይም ሙሉ በሙሉ ለተመረቱ ቴክኖሎጂዎች ወይም ማሽነሪዎች ግብር ቅናሽ ማድረግ***
***ለ፡ ለሥራ ፈጣሪዎች የንግድ ስልጠና እና አገልግሎት የድጋፍ ፕሮግራም መጀመር***
***ሐ፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ የኪራይ አገልግሎት ሰጭዎችን መደገፍ***
***መ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ አገልግሎት እንደብድር ማስያዣ የሚያገለግል የብድር ዋስትና አገልግሎት ከገንዘብ ተቋማት እና ከመድህን ድርጅቶች ጋር በተባበር መመሥረት***

### *ንዑስ-ፕሮግራም 3.2: ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተ የገንዘብ አገል ግሎት*

*ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተ የገንዘብ አገልግሎት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-*

*ሀ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቆጣጠር የሚረዳቸውን ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች መግዛት እንዲችሉ የመድህን (የዋስትና) ፕሮግራም፣ የብድር ዋስትና ፕሮግራም ወይም ሌላ የገንዘብ ማቅረቢያ ሥርዓት መዘርጋት*

*ለ፡ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያን የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማግኘት እንዲችሉ አዳዲስ የገንዘብ አገልግሎቶችን መስጠት*

*ሐ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ከሚፈጽሙት የድህረ-ምርት ብክነትን መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች ግዥ ጋር በተገናኘ በዝቅተኛ ወለድ ብድር ከአበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ማግኘት እንዲችሉ ለአነስተኛ አበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ስልታዊ ድጎማ ማድረግ*

*መ፡ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዮኒየኖች ለአርሶ አደሮች ብድር ማቅረብ እንዲችሉ አቅማቀቸውን መገንባት*

***ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡***

***ሀ፡ ለብድር አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጡ የአቅም ግንባታ (የሰው እና የቁሳቁስ) ስራዎችን ማጠናከር***
***ለ፡ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ሥርዓትን ማስፋፋት***
***ሐ፡ የቡድን የብድር ዋስትና ሥርዓትን ማጠናከር***
***መ፡ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በአካባቢ ደረጃ አነስተኛ የገንዘብ አበዳሪ ተ ቋማትን ማስፋፋት***
***ሠ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ ለሚውል ብድር በቅናሽ ወለድ ማበደር***
***ረ፡ የወደፊት ርክክብ-ውል እና የኮንትራት እርሻ ሥርዓትን ማስፋፋት***

*ንዑስ-ፕሮግራም 3.3: ግብርናዊ- ቢዝነስ፣ የግብርና ኢንተርፕራይዞችን እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችን በኩታ-ገጠም ማደራጀት*

ግብርናዊ ንግድን (ቢዝነስን)፣ የአርሶ አደሮችን ኢንተርፕራይዞችን (ድርጅቶችን) እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችን በኩታ-ገጠም ማደራጀት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-

ሀ፡ ሰፊ የሥራ መጠን (ትልቅ ድርጅት) በመፍጠር እርስ በእርስ መጠቃቀም እንዲችሉ እና በቀላሉ የገንዘብ ብድር አገልግሎት በማግኘት የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ እንዲችሉ በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ባሉ ተዋንያን መካከል ሽርክና መፍጠር

ለ፡ ለአርሶ አደሮች ስልጠና፣ የገበያ መረጃ፣ የብድር እና ቁጠባ አገልግሎት፣ የመደራደር ክህሎትን እና ሌሎች ከድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በብቃት መስጠት እንዲችሉ የአርሶ አደሮችን ድርጅቶች እና ህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ ለኩታ-ገጠም ሥራ ገንዘብ ለማግኘት የመነሻ-ሀሳብ (ፕሮፖዛል) መቅረጽ**
**ለ፡ ድህረ-ምርትን ጨምሮ በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለቶች የንግድ ኩታ-ገጠም ጽንሰ-ሀሳብን ማስፋፋት**
**ሐ፡ የአርሶ አደሮች ማህበራት ለአባላቶቻቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የንግድ ስልጠና በመስጠት መደገፍ**

**ፕሮግራም 4: እሴት መጨመርን ማስፋፋት**

የዚህ ውጤት ዋና ዓለማ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ አድሎ የለለበት እና ሁሉን-አቀፍ የሆነ እሴት መጨመሪያ ሥርዓት በማስፋፋት የድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ አርሶ አደሩ እና ሸማቹ እንዲጠቀም ማድረግ ነው፡፡

*ንዑስ-ፕሮግራም 4.1: የግብርና ግብዓት አቅራቢዎችን ማስፋፋት*

የግብርና ግብዓት አቅራቢዎችን ማስፋፋት የሚከተለውን ሁኔታ ይፈልጋል፡-

ለግብርናው ሥራ ትርጉም ባለው መጠን ወጭን ለመቀነስ ለግብርና ግብዓት አምራቾች እና አቅራቢዎች የተቀናጀ፣ የተጣጣመ እና ለሚገባው ብቻ ድጎማ ማድረግ

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

**ሀ፡ በገጠር ለሚከናወኑ እሴት መጨመር ሥራዎች የገንዘብ አቅርቦትን መደገፍ**
**ለ፡ በገጠር አካባቢ የሚሰሩ አነስተኛ የብድር ተቋማትን መደገፍ**
**ሐ፡ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርኮች የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ**

### *ንዑስ-ፕሮግራም 4.2: የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማስፋፋት*

የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማስፋፋት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈልጋል፡-

ሀ፡ ለግብርና ድርጅቶች የቴክኖሎጂ እና የገንዘብ እንዲሁም የሰው ክህሎትን በማዳበር ድጋፍ ለማድረግ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎች እና በግብርና ድርጅቶች መካከል ሽርክናን ማጠናከር

ለ፡ እሴት የሚጨምሩ የህብረት ሥራ ማህበራትን እና ዩኒየኖችን ማስፋፋት

ሐ፡ እሴትን በመጨመር የምርት ጥራትን መለየት ለሰንሰለቱ ተዋንያን በተለይም ለአርሶ አደሮች ስለሚሰጠው ጥቅም ግንዛቤ መፍጠር እና ማስፋፋት

መ፡ እህል በተመረተበት አካባቢ እንዲቀነባበር በማድረግ በማጓጓዝ እንዲሁም ያልተቀነባበረ ምርት በማከማቸት የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት ለመቀነስ በገጠሩ አካባቢ አነስተኛ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማቋቋም እና እሴት መጨመርን ማስፋፋት

**ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ በተጠቀሱት መሰራት በሚገባቸው ጉዳዮች ወይም ሥራዎች ላይ ሀብት መመደብ ወይም ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፡፡**

***ሀ፡ ሴቶችን እና ወጣቶችን መሰረት ያደረገ የእሴት መጨመር እና የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ሥራዎችን መደገፍ***
***ለ፡ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ የምክክር-መድረክ መፍጠር***
***ሐ፡ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ዙሪያ ስልጠና ለሚሰጡ አገልግሎት ሰጭዎች ድጋፍ ማድረግ***
***መ፡ ደረጃ እና ዓይነትን መሠረት ያደረገ ንግድን በየአካባቢው ማጎልበት***
***ሠ፡ እሴት መጨመርን ምግብ ማቀነባበርን ጨምሮ በቀበሌ ደረጃ ማስፋፋት***

### ***የፕሮግራሞች ቅደም-ተከተል እና መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች ማጠቃለያ***

አዝል 1 እና ከ ሀ እስከ መ ያሉ ሠንጠረዦች የፕሮግራሞችን ቅደም-ተከተል፣ ዓላማዎቻቸውን እና መሰራት የሚገባቸውን ጉዳዮች ማጠቃለያ ይዘዋል፡፡ ይህ መረጃ ለድህረ-ምርት አያያዝ የኢንቨስትመንት እቅድ ወጪዎችን ለማስላት እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

# ክፍል ፯
## ለድህረ-ምርት አያያዝ የኢንቨስትመንት እቅድ (2010/11 — 2014/15)

### በጀትና ወጪዎች

ይህ የኢንቨስትመንት እቅድ ቀደም ብሎ በውጤት ማዕቀፍ የተለዩትን እና የተዘረዘሩትን ፕሮግራሞች እና ንዑስ-ፕሮግራሞች ከወጪያቸው ጋር ያስተሳስራል። የኢንቨስትመንት እቅድ በጀት እና ወጭዎች በተለያየ መንገድ ሊመደቡ እንደሚችሉ ማወቅ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው የሥራ ማስኬጂያ መደብ ሲሆን በውጤት ማዕቀፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሥራዎች ለማስፈፀም ሚያስፈልገውን ወጪ የያዘ ነው። በዚህሥር የሚጠቃለሉ ወጪዎች ምሳሌዎች ለጥናቶች ማስፈፀሚያ፣ የመነሻ-ሃሳብ (ፕሮፖዛል) መቅረጫ፣ የቅኝት ጥናት ማከናወኛ ወዘተ ወጪዎች ናቸው።
የኢንቨስትመንት እቅድ ሁለተኛው መደብ ደግሞ የካፒታል ወጪ ነው። የመሣሪያዎች ግዥ፣ የከረጢት ማምረቻ ፋብሪካ ማቋቋም፣ ቴክኖሎጂ ወይም መሣሪያ ማምረት፣ የማቀነባበሪያ ፋብሪካ ማቋቋም ወዘተ የካፒታል ወጪዎች ውስጥ የሚካተቱ ምሳሌዎች ናቸው። የካፒታል ወጪ በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ሊሆን ይችላል። የካፒታል ወጪ እንደ ፕሮጀክቱ የሚለያይ እና ለመገመትም አስቸጋሪ ነው። የካፒታል ወጪዎች በዚህ የኢንቨስትመንት እቅድ ውስጥ አልተካተቱም።

### የድህረ-ምርት አያያዝ የኢንቨስትመንት እቅድ በጀት እና ወጪዎች

ሠንጠረዥ 1 ከ 2010/11 እስከ 2014/15 እንዲፈፀም ለታቀደው የኢንቨስትመንት እቅድ በጀት እና ወጪዎች ማጠቃለያ ነው። ጠቅላላ የተገመተው ወጪ ወይም በጀት 212 ሚሊዮን (10.6 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) ነው። ከጠቅላላው በጀት 47 በመቶ የሚሆነው ምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት ለመቀነስ ዓላማ የሚውል ነው። ከዚህ ቀጥሎ 20 በመቶ የሚሆነው በጀት ደግሞ ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ለማሻሻል ዓላማ፤ 20 በመቶ የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ቀልጣፋ ለማድረግ እና ቀሪው 13 በመቶ በጀት ደግሞ እሴት መጨመርን ለማስፋፋት ዓላማ የሚውል ነው።

ሠንጠረዥ 1፡ ለዋና ዓላማዎች ማስፈፀሚያ የኢንቨስትመንት እቅድ በጀት እና ወጪዎች ማጠቃለያ (ዋዓ = ዋና ዓላማ)

| | 1ኛ ዓመት | 2ኛ ዓመት | 3ኛ ዓመት | 4ኛ ዓመት | 5ኛ ዓመት | ንዑስ ድምር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 37,825,000 | 57,240,000 | 50,760,000 | 38,280,000 | 27,820,000 | 211,925,000 | ብር |
| **አጠቃላይ የድህረ-ምርት አያያዝ ኢንቨስትመነት እቅድ (2010/11 — 2014/15)** | 1,891,250 | 2,862,000 | 2,538,000 | 1,914,000 | 1,391,000 | 10,596,250 | የአሜሪካ ዶላር |
| ዋዓ 1፡ ምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ | 974,250 | 1,232,000 | 1,264,000 | 917,000 | 617,000 | 5,004,250 | 47 |
| ዋዓ 2፡ የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ቀልጣፋ ማድረግ | 427,000 | 708,000 | 457,000 | 310,000 | 252,000 | 2,154,000 | 16 |
| ዋዓ 3፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦትን እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል | 325,000 | 497,000 | 482,000 | 437,000 | 337,000 | 2,078,000 | 20 |
| ዋዓ 4፡ እሴት መጨመርን ማስፋፋት | 165,000 | 425,000 | 335,000 | 250,000 | 185,000 | 1,360,000 | 13 |

**ሠንጠረዥ 2** ለዋና ዓላማዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን የኢንቨስትመንት እቅድ በጀት እና ወጪዎችን በዝርዝር ያሳያል፡፡ እያንዳንዱን የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ ለማምጣት መፈፀም ላለባቸው ዋና ዋና ሥራዎች ለእያንዳንዳቸው በጀት በተናጠል ተቀምጧል፡፡

# ሠንጠረዥ 2:  የሥራ ማስኬጃ ወጪ የኢንቨስትመንት እቅድ (ዋዓ = ዋና ዓላማ)

| | | የምንዛሬ ተመን ብር / የአሜሪካ ዶላር | 1ኛ ዓመት | 2ኛ ዓመት | 3ኛ ዓመት | 4ኛ ዓመት | 5ኛ ዓመት | ንዑስ ድምር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 20 | 37,825,000 | 57,240,000 | 50,760,000 | 38,280,000 | 27,820,000 | 211,925,000 | ብር |
| አጠቃላይ የድህረ-ምርት አያያዝ ኢንቨስትመንት እቅድ (2010/11 እስከ 2014/15) | | | 1,891,250 | 2,862,000 | 2,538,000 | 1,914,000 | 1,391,000 | 10,596,250 | US$ |
| ዋዓ 1. ምግብ ላይ የሚደርሰውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ | | | 974,250 | 1,232,000 | 1,264,000 | 917,000 | 617,000 | 5,004,250 | 47 |
| የመካከለኛ ጊዜ ውጤት | 1.1 | ውጤታማ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት መተግበር | 340,250 | 25,000 | 134,000 | 122,000 | 24,000 | 825,250 | 16 |
| | 1.2 | የማላመድ ምርምርን እና ልማትን ለድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት መጠቀም | 81,000 | 216,000 | 434,000 | 69,000 | 9,000 | 809,000 | 16 |
| | 1.3 | የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማመንጨት እና ማሰራጨት | 141,000 | 152,000 | 56,000 | 220,000 | 64,000 | 633,000 | 13 |
| | 1.4 | የድህረ-ምርት አያያዝ ክህሎት፣ ስልጠና እና የሰው ልማትን ማሻሻል | 362,000 | 364,000 | 461,000 | 382,000 | 341,000 | 1,910,000 | 38 |
| | 1.5 | ዘለቄታ ያለው የአካባቢ አያያዝን ማስፋፋት እና ማጎልበት | 50,000 | 295,000 | 179,000 | 124,000 | 179,000 | 827,000 | 17 |
| ዋዓ 2:  የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያን ውጤታማ ማድረግ | | | 427,000 | 708,000 | 457,000 | 310,000 | 252,000 | 1,665,000 | 16 |
| የመካከለኛ ጊዜ ውጤት | 2.1 | ዘለቄታዊ  እና ተደራሽ የሆነ የድህረ-ምርት ሥርዓት ማስፋፋት | 235,000 | 35,000 | 25,000 | 25,000 | 25,000 | 345,000 | 21 |
| | 2.2 | ውጤታማ የሆነ የማከማቻ አያያዝ ሥርዓት ማስፋፋት | 65,000 | 197,000 | 77,000 | 12,000 | 12,000 | 363,000 | 22 |
| | 2.3 | የትራንስፖርት ሥርዓት እና ትስስር መሻሻል | 10,000 | 45,000 | 20,000 | 10,000 | 20,000 | 105,000 | 6 |
| | 2.4 | ደረጃ እና ዓይነት ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል | 55,000 | 137,000 | 12,000 | 227,000 | 47,000 | 478,000 | 29 |
| | 2.5 | የምግብ ደህንነት ደረጃ ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል | - | 117,000 | 199,000 | 24,000 | 34,000 | 374,000 | 22 |
| | 2.6 | የግብርና እና ገበያ የመረጃ ሥርዓት ማስፋፋት | - | 107,000 | 72,000 | 12,000 | 62,000 | 253,000 | 15 |
| | 2.7 | የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል | 62,000 | 70,000 | 52,000 | - | 52,000 | 236,000 | 14 |
| ዋዓ 3: ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦትን እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል | | | 325,000 | 497,000 | 482,000 | 437,000 | 337,000 | 2,078,000 | 20 |
| የመካከለኛ ጊዜ ውጤት | 3.1 | ለድህረ-ምርት አያያዝ የሚውል የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦት እና ኢንቨስትመንትን ማሻሻል | 90,000 | 57,000 | 112,000 | 12,000 | 22,000 | 293,000 | 14 |
| | 3.2 | ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራን ያካተተ የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎትን ማስፋፋት | 55,000 | 150,000 | 105,000 | 60,000 | 20,000 | 390,000 | 19 |
| | 3.3 | ግብርናዊ-ቢዝነስ፣ የአርሶ አደሮችን ኢንተርፕራይዞች እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችን ኩታ-ገጠም በሆነ መልኩ ማሰባሰብ | 180,000 | 290,000 | 265,000 | 365,000 | 295,000 | 1,395,000 | 67 |
| ዋዓ 4:  እሴት መጨመርን ማስፋፋት | | | 165,000 | 425,000 | 335,000 | 250,000 | 185,000 | 1,360,000 | 13 |
| የመካከለኛ ጊዜ ውጤት | 4.1 | ለድህረ-ምርት አያያዝ የሚውል የገንዘብ አቅርቦት እና ኢንቨስትመንት መሻሻል | - | 180,000 | 100,000 | 80,000 | 20,000 | 380,000 | 28 |
| | 4.2 | አበረታች እና አዳዲስ ፈጠራን ያካተተ የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎትን ማስፋፋት | 165,000 | 245,000 | 235,000 | 170,000 | 165,000 | 980,000 | 72 |

# ክፍል ፯

## የድህረ-ምርት አያያዝ የማስፈፀሚያ እቅድ

**የማስፈፀሚያ እቅድ**

**ውጤታማ የሆነ የድህረ-ምርት አያያዝ የማስፈፀሚያ እቅድ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥቅል ተግባሮች መያዝ አለበት።**

ሀ፡ ስትራቴጂው ሥራላይ ውሎ የድህረ-ምርት ብክነት እንዲቀንስ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ሥራ የሚያስተባብር አስተዳደራዊ አካል ያስፈልጋል። የአስተዳደሩ አካል ለስትራቴጂው ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅረቦት ማሟላት ይኖርበታል።

ለ፡ በቂ እና ተደራሽ የሆነ ሀብት በለለበት የስትራቴጂውን ውጤት እና የሚጠበቀውን ለውጥ ማምጣት ስለማይቻል አስፈላጊውን ሀብት የማሰባሰብ ሥራ ይፈልጋል።

ሐ፡ ሥራው እንደታቀደው እየተፈፀመ እንድሆነ ለማወቅ የክትትል እና የግምገማ ሥራ ይጠይቃል።

በዚህ ክፍል የአስተዳደር አካል እና የሀብት ማሰባሰብ ተግባራት በጥልቅ የሚተነተኑ ሲሆን የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው ሥራላይ ሲውል ሊገጥሙ ሰለሚችሉ ስጋቶች እና ታሳቢዎች ግን ማጠቃለያ ብቻ ይቀርባል። ክትትል እና ግምገማ በምዕራፍ 6 ውስጥ ተካተዋል።

**የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀም እቅድ የአስተዳደር አካል**

ይህ ስትራቴጂ በሚቀረጽበት ስዓት ከባለድርሻ አካላት ከተሰጡት ምክረ-ሃሳቦች መካከል ኢትዮጵያ ውስጥ የእህል ድህረ-ምርት ብክነትን ለመረዳት (ለማወቅ)፣ ለመቀነስ እና ለመቆጣጠር የተቀናጀ አሰራርን መፍጠር አንዱ ነበር። የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀም እቅድ እምብርት የሚሆነው በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በማስገባት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በማሳተፍ ስትራቴጂውን የሚያስተዳድር እና የሚያስፈጽም ሁሉንአቀፍ የአስተዳደር አካል መፈጠር ነው። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተግባሮች ለውጤታማ የስትራቴጂ አፈፃፀም አስፈላጊ ናቸው።

ሀ፡ የፖሊሲ እና የቁጥጥር ሥራ<br>
ለ፡ የግብርና ምርምር፣ ልማት እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት<br>
ሐ፡ የንግድ እና የገበያ አገልግሎት መስጠት<br>
መ፡ የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት<br>
ሠ፡ የእሴት መጨመር እና የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ<br>
ረ፡ የገንዘብ እና የድጋፍ አገልግሎት

በእነዚህ የሥራ ቡድኖች መካከል የተቀናጀ አሰራር ለስኬታማ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀም አስፈላጊ ነው። ሥዕል 4 የእነዚህን የሥራ ቡድኖች ሚና እና ሀላፊነት በሥዕል ያሳያል። የአስተዳደሩን አካል ሥራ በሙሉ አቅም ለማሰራት የተሟላ ሀብት ያለው የድህረ-ምርት አያያዝ ዳይሬክቶሬት በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥር መኖር አለበት።




ሥዕል 4:  የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አስፈፃሚ አስተዳደር አካላት አወቃቀር

## የፖሊሲ እና የቁጥጥር ሥራ

የፖሊሲ እና የቁጥጥር ሥራ የሚያካትተው ፖሊሲ ማውጣት እና አቅጣጫ ማስቀመጥ፣ ቁጥጥር፣ የመመርመር እና የማጽደቅ ሥራዎች እና ለስትራቴጂው ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን ሀብት ማሰባሰብ ነው። እነዚህን ሥራዎች እና ሂደቶች የሚሰሩ ብዙ የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ቢሆኑም መስሪያ ቤቶችን በማስተባበር የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀሙን በዋናነት የሚመራው የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ነው። ከሌሎች ጋር በትብብር የሚሰሩ የቁጥጥር ሥራዎች ለምሳሌ ዓይነት እና ደረጃ መሟላታቸውን፣ የሚመረቱ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝር ደንቦችን ማሟላታቸውን፣ የምግብ ደህንነት ደረጃ፣ የኬሚካል አጠቃቀም እና አወጋገድ ሥርዓት ወዘተ መመርመር እና በትክክል ሥራላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ ነው። በመጨረሻም መንግስት፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች፣ ዓለም ዓቀፍ ኢንቨስተሮች እና የልማት አጋር አካላት የቴክኒክ እና የገንዘብ አገልግሎት በመስጠት ሥራውን የሚያሳልጡ ናቸው።

የፖሊሲ እና የቁጥጥር ሥራ በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥር አዲስ በሚከፈተው የድህረ-ምርት አያያዝ ዳይሬክቶሬት እንዲከናወን እና ዳይሬክቶሬቱ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ ይዋቀራል። የዳይሬክቶሬቱ ዋና ተግባር የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን በሥራላይ የሚያውሉትን ባለድርሻ አካላት በተስተካከለ እና በተሳሰረ ሁኔታ መፈፀማቸውን መከታተል እና ማስተባበር ነው።

## የግብርና ምርምር፣ ልማት እና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት

የግብርና ምርምር፣ ልማት እና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት የሚያካትተው የግብርና ምርምር እና ልማት ሥራዎችን፣ አርሶ አደሮችን ማሰልጠን፣ የትምህርት እና የእውቀት አገልግሎት እና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ናቸው። የግብርና ምርምር እና ሌሎች መሰል ደጋፊ ተቋማት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን በማስፈፀም ደረጃ የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ ነው። በግብርናው እሴት ሰንሰለት ውስጥ ብክነትን ሳይቀንሱ ምርት ለመጨመር መጣር ብቻ ውጤት አያመጣም። ይህን ክፍተት በመሙላት ምርምር ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።

የዩኒቨርሲቲዎች ሚና የሚያካትተው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደርሰውን የእህል ብክነት መጠን፣ የብክነቱን መንስኤ እና ተጓዳኝ መፍትሄዎችን በጥናት መለየት ነው። ሌላው የዩኒቨርሲቲዎች ሚና ደግሞ ስለድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ ስለአገር-በቀል እና ምርጥ የሰብል አመራረት ልምዶች፣ ስለማከማቻ እና እሴት የመጨመር ሂደቶች ማስተማር እና ስልጠና መስጠት ነው።

የግብርና ሙያ እና ቴክኒክ ማሰልጠኛዎች እና የሌሎች ማሰልጠኛዎች ተግባር እና ሃላፊነት ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀም ጉልህ ድርሻ አለው። ከምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የስልጠና ኮሌጆች የሚገኙ የምርምር ውጤቶች በአምራቾች፣ በነጋዴዎች እና በገበያ ደረጃ ወደ ተግባር መለወጥ ሁሉን-ዓቀፍ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ይፈልጋል። የልማት ሠራተኞችን እና ሌሎች መሰል ባለሙያዎችን በድህረ-ምርት አያያዝ እና ልማት ማሰልጠን ወሳኝ ነው። የአርሶ አደሮች ድርጅቶችን፣ የህብረት ሥራ ማህበራትን እና ዩኒየኖችን ማጠናከር እና ማሰልጠን ለስትራቴጂ አፈፃፀሙ ይጠቅማል።

ስለሆነም በድህረ-ምርት አያያዝ የአፈፃፀም እቅድ ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱት ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት የግብርና ምርምር፣ ልማት እና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተብሎ ተወስዷል።

- የግብርና ምርምር እና ልማት ተቋማት
- ዩኒቨርሲቲዎች እና ሌሎች ከፍተኛ ተቋማት
- የግብርና ሙያ እና ቴክኒክ ማስተማሪያ እና ማሰልጠኛ ተቋማት
- የአርሶ አደሮች ድርጅቶች፣ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒየኖች

## የንግድ እና ገበያ አገልግሎት መስጠት

የንግድ እና ገበያ አገልግሎት መስጠት የሚያካትተው የማከማቻ ሥርዓት፣ የግብርና ምርቶች ንግድ እና ገበያ ሥርዓት፣ አስተሻሸግ፣ ማጓጓዝ እና የመጋዘን ሥርዓት፣ የምርት ግብይት ሥርዓት እና የግብርና መረጃ ሥርዓት ናቸው። የአነስተኛ (የገጠር) ገበያዎች፣ የምርት ልውውጥ ማዕከላት እና የችርቻሮ ገበያዎች ሥራ ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ትግበራ ወሳኝ ናቸው። ለአምራቾች ተደራሽ የሆነ፣ ስልታዊ እና የተደራጀ የንግድ እና ገበያ ሥርዓት መኖር እና በባለሙያ በሚመሩ የማከማቻ እና የገበያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚሰጡ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ የመሳሰሉ አዳዲስ የማከማቻ እና የገበያ ስምምነቶች መኖር የድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ግብን ሊያሳኩ ይችላሉ። ስለሆነም በድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የማስፈፀሚያ እቅድ ውስጥ የንግድ እና ገበያ አገልግሎትን እንደ አንድ ጉዳይ በአጠቃላዩ የድህረ-ምርት አያያዝ አስተዳደር አወቃቀር ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

ሆኖም ግን የንግድ እና ገበያ አገልግሎትን በተመለከተ ሁሉንም የገበያ ተዋኒያኖች የሚወክል አንድ ማዕከላዊ ወይም መሪ አካል ባለመኖሩ ምክንያት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን ተፈፃሚ የሚያደርግ መሪ መስሪያ ቤት (አካል) መመረጥ አልተቻለም። የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ ቢኖርም ወደሥራ አልገባም። ይህ የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ዋና ባለድርሻ-አካላትን በሙሉ እንደሚወክል ታሳቢ ተደርጓል። አነስተኛ (የገጠር) ገበያዎች፣ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒየኖች የምርት መገበያያ ማዕከል ስለሆኑ የምክክር መድረክን ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።

ስለሆነም የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክን በማጠናከር እና በሙሉ አቅሙ እዲሰራ በማድረግ መልከብዙ የሆኑትን የማምረት፣ የማከማቸት፣ የግብይት፣ እና እሴት መጨመር ሥራዎችን የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂን ሥራላይ ከማዋል ጋር በተገናኘ እንዲወክል እና የመሪ ተዋናይነት ሚና እንዲጫወት ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ የፌደራል ህብረት ሥራ ዩኒየን የመሳሰሉ ትልልቅ ተቋማት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን እንዲፈፅሙ ሀላፊነት ይሰጣቸዋል፡፡

## የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት

የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀም ስኬትን ወይም ውድቀትን የሚወስን ንዑስ-ዘርፍ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ንዑስ-ዘርፍ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎች ማምረቻ ዋጋ ከውጭ በሚገቡ ጥሬ-እቃዎች ውድነት የተነሳ ውድ መሆን፣ ቀልጣፋ እና አስተማማኝ የማሽነሪ ጥገና የሚሰጥ እና ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ አለመኖር፣ ከውጭ የገቡ ቴክኖሎጂዎችን ለአገር ውስጥ ሁኔታ ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ አለመቻል ወዘተ የመሳሰሉ ከፍተኛ ተግዳሮቶች አሉበት፡፡ በሌላ ጎኑ ደግም የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ የሚቻለው በማምረት፣ በአጨዳ፣ በክምችት፣ በማቀነባበር ወዘተ ሂደቶች ውስጥ የቴክኖሎጂ መሻሻል ሲኖር ብቻ ነው፡፡

እንደ የንግድ እና ገበያ አገልግሎት መስጠት የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠትን የሚመራ እና የሚያስተባብር አካል የለም፡፡ ሆኖም ግን እንደ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ፣ በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥር ያለው ግብርና ሜካናይዜሽን፣ ዓለም ዓቀፍ ደጋፊ ድርጅቶች እንደ ሳሳካዋ ግሎባል 2000፣ ሃይቴክ ትሬዲንግ የመሳሰሉት የቴክኖሎጂ አገልግሎት በመስጠት ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፡፡

**የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠትን በተመለከተ ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው አፈፃፀም በሚቋቋመው የአስተዳደር አካል ውስጥ የቴክኖሎጂ አገልግሎት ንዑስ-ክፍል ከማቋቋም ይልቅ የቴክኖሎጂ አገልግሎት ሰጭዎችን የሚወክል ብቻ እንዲካተት በምክረሀሳብ ደረጃ ቀርቧል፡፡**

## እሴት መጨመር እና የግብርና ምርት ማቀነባበር

እሴት የመጨመር እና የግብርና ምርት የማቀነባበር ሥራዎች የሚከናወኑት በትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ብቻ ሳይሆን በጎጆ ኢንዱስትሪዎች ደረጃም የግብርና ምርቶችን ወደተሻለ የምርት ደረጃ ለመለወጥ የሚከናወኑ ወሳኝ ሥራዎች ናቸው፡፡ እሴት መጨመር የሚጀምረው የተሻሻሉ የዓይነት እና የአስተሻሸግ ደረጃዎችን ከማሳ ጀምሮ ተግባራዊ ሲሆኑ ነው፡፡ ጥራት ላለው ምርት ከፍተኛ ዋጋ የሚከፈል ከሆነ እሴት መጨመር በአርሶ አደሩ ገቢ ላይ አወንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ዓይነትን እና ደረጃን በግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ደረጃ ሥራላይ ማዋል የማበጠር እና ዓይነት የማውጣት ሥራን ወጪ ስለሚቀንስ ትርፋማነቱ ከፍተኛ ነው፡፡ አሁን ያሉት እሴት የሚጨምሩ እና የግብርና ምርት የሚያቀነባብሩ ኢንዱስትሪዎች የድህረ-ምርት አያያዝን በማስፋፋት ረገድ ብዙ ተሳትፎ የላቸውም፡፡ እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በድህረ-ምርት አያያዝ በሰፊው ቢሳተፉ ዘለቄታ ባለው ሁኔታ ስትራቴጂው ተግባር ላይ ይውላል፡፡

እላይ እንደተጠቀመው እንደ ንግድ እና ገበያ አገልግሎት መስጠት እና የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠት እሴት የመጨመር እና የግብርና ምርት የማቀነባበር ሥራን የሚመራ እና የሚያስተባብር አካል የለም፡፡ ሆኖም ግን የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ እሴት የሚጨምሩ እና የግብርና ምርት የሚያቀነባብሩ ተዋንያንን በስትራቴጂው ትግበራ እንዲሳተፉ የማስተባበር ሥራ በተደራቢነት ሊያከናውን ይችላል፡፡

## የገንዘብ እና የድጋፍ አገልግሎት

የገንዘብ እና የድጋፍ አገልግሎት በለለበት የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን ሥራላይ ማዋል አይቻልም። በእሴት ሰንሰለት ውስጥ በሁሉም ደረጃ የገንዘብ አቅርቦት ያስፈልጋል። ስለሆነም የገንዘብ ተቋማት የግብርና እሴት ሰንሰለትን ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ሊገነዘቡ ይገባቸዋል። ብዙ ድርጅቶች እንደ አነስተኛ አበዳሪዎች፣ ንግድ ባንኮች፣ የብድር እና ቁጠባ ህብረት ሥራ ማህበራት እና ሌሎችም የገንዘብ አቅርቦት አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው። መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የልማት አጋር-አካላት ከፕሮጀክት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ለድህረ-ምርት አያያዝ ሥራዎች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ።

የገንዘብ እና የድጋፍ አገልግሎት ሰጭዎች ባህሪ እና አደረጃጀት ተመሳሳይ ባለመሆኑ ከድህረ-ምርት አያያዝ ጋር በተገናኘ አንድ ወካይ ተቋም መምረጥ አይቻልም። ሆኖም ግን የገንዘብ እና የድጋፍ አገልግሎት ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አስፈፃሚ የአስተዳደር አካል አስፈላጊ በመሆኑ በድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ ቢወከል ሥራው እንደ ታቀደው ሊሰራ ይችላል።

### ሃብት ማሰባሰብ

በቂ ሃብት በለለበት ሁኔታ ስትራቴጂው የታለመለትን ዓላማ ሊያሳካ ስለማይችል ሀብት ማሰባሰብ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ተግባር ነው። ስለሆነም መንግስት በጀት እንዲመድብ እና ከልማት እና ከተባባሪ አጋር-አካላት የሚሰጡ ሀብቶችን በተቀናጀ ሁኔታ ማሰባሰብ ይጠበቅበታል። በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥር አዲስ እንዲቋቋም የታሰበው የድህረ-ምርት አያያዝ ዳይሬክቶሬት አንዱ ቁልፍ ተግባሩ ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ የሚሆን ሀብት ማሰባሰብ ነው። ሥራዎችን ለማስተባበር እና ለማካሄድ የሚያስፈልግ በጀት በግብርና ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን በሚያበረታታ መልኩ በኢንቨስትመንት ፕላን ምዕራፍ ውስጥ በዝርዝር ተካቷል። በጀቱን በማፈላለግ ማሰባሰብ እና በማስተዳደር ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል።

### ሥጋቶች እና ታሳቢዎች

የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ሥራላይ ሲውል ሊገጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና መፍትሄዎች በሠንጠረዥ 3 ተካተዋል።

## ሠንጠረዥ 3፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ሥራላይ ሲውል ሊገጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና መፍትሄዎች

| ሥጋት | ተፅዕኖ | እድል | መፍትሄ |
|---|---|---|---|
| ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው የፖሊቲካ ድጋፍ አለመኖር | ድህረ-ምርት አያያዝ ትኩረት ያልተሰጠው ዘርፍ እንደ ሆነ ይቀጥላል | መካከለኛ | • የግብርና እድገት ፕሮግራም 2 እና የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የወደፊት መፍትሄዎችን ያሳያሉ<br>• የፌደራል መንግስት እና የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የድህረ-ምርት አያያዝ ለምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ እና ለአነስተኛ ገቢ ምክንያት እንደሆነ ማመን እና ትኩረት መስጠት<br>• የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂውን ሥራላይ ማዋል |
| ውጤታማ የሆነ የድህረ-ምርት አያያዝ አስተዳደር ማቋቋም አለመቻል | የተበጣጠሰ (የተበታተነ እና ያልተማከለ) የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ አፈፃፀም ስለሚከሰት ስትራቴጂው የታለመለትን ግብ እና ዓለማ አይመታት | መካከለኛ | • የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የድህረ-ምርት አያያዝ አስተዳደር በሥሩ እያቋቋመ ነው<br>• የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ እንዲሰራ ማድረግ<br>• በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ በድህረ-ምርት አያያዝ ጉዳይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላትን ሥራ እና ጥረት ውጠቴማ በሆነ መልኩ ማስተባበር |
| ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው አስተዳደር እና ለማስፈፀሚያ የኢንቨስትመንት እቅድ በቂ ሀብት አለማቅረብ | የተበጣጠሰ አሰራር ከፍተኛ ወጪ ከማስከተሉ በተጨማሪ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ውጤታማ አይሆንም። ስለሆነም ከፍተኛ የሆነው የድህረ-ምርት ብክነት እንዳለ ይቀጥላል | በጣም ከፍተኛ | • ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ማስፈፀሚያ የፌደራል መንግስት በጀት መመደብ<br>• ዓይነት እና ደረጃን እና እንደ ጥራቱ ደረጃ የተለያየ የዋጋ አከፋፈል ሥርዓትን በመቀበል የድህረ-ምርት አያያዝን በማስፋፋት የግል ባለሀብቱ በእሴት መጨመር ወይም በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ዘርፍ ሀብቱን እንዲያፈስ ማበረታታት |
| ትክክለኛ እና ተደራሽ የሆነ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ ማስፋፋት አለመቻል | ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ብቻ ስለሚኖሩ የተሻሻሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ቅበላ አይኖርም። ስለሆነም ከፍተኛ የሆነው የድህረ-ምርት ብክነት እንዳለ ይቀጥላል | በጣም ከፍተኛ | • በቴክኖሎጂው ወይም በመሳሪያው አምራች ላይ የተጣለውን የግብር ጫና ለማቅለል እቃው ወይም ቴክኖሎጂው ለታሰበለት ዓላማ መሸጡ ሲረጋገጥ ግብር የሚቀነስበትን ወይም የሚመለስበትን ሥርዓት መዘርጋት<br>• የተሻሻለ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ ለሚገዙ እና ለሚጠቀሙ ልዩ የገንዘብ ማበረታቻ መስጠት |
| የግብርና መረጃ አያያዝ ሥርዓትን ጨምሮ የተደራጀ የገበያ ሥርዓት አለመኖር | በእህል ንግድ እና ገበያ ሥርዓት ውስጥ ግልጽነት አይኖርም። ሥለሆነም አርሶ አደሮች ከምርታቸው ተጠቃሚ አይሆኑም፣ መካከል ላይ ያሉ ነጋዴዎችን የሚጠቅም የተመሰቃቀለ ገበያ ይኖራል፣ አገሪቱ ውስጥ ስላለው የእህል አቅርቦት ትክክለኛ መረጃ አይኖርም። | በጣም ከፍተኛ | • አነስተኛ (የገጠር) ገበያዎችን ማሻሻል<br>• ለዓይነት፣ ለደረጃ እና እና እንደ የጥራት ደረጃው ከፍተኛ ዋጋ የመክፈል ሥርዓትን ጠንክሮ ማስፋፋት<br>• አስተሻሸግን ከመቶ ኪ.ግ ደረጃ ወደ 50 ኪ.ግ እሽግ መቀነስ<br>• የህብረት ሥራ ማህበራት ብዙ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ አባላቶቻቸው የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ሥርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማበረታታት<br>• የሚሰራ የግብርና መረጃ አያያዝ ሥርዓት መመስረት |
| ለምርጥ የድህረ-ምርት አያያዝ ተግባሮች (ተሞክሮዎች) ድጋፍ እና ስልጠና አለመኖር | በአጠቃላይ ስለድህረ-ምርት አያያዝ እና የድህረ-ምርት በምግብ ዋስትና እና በአርሶ አደሮች ገቢ ላይ ስላለው ተፅዕኖ ዝቅተኛ ግንዛቤ መኖር። ስለሆነም የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ እና ዝቅተኛ የአርሶ አደር ገቢ ብሎም ድህነት ባሉበት ይቀጥላሉ። | በጣም ከፍተኛ | • ሕዝቡን ስለድህረ-ምርት ብክነት ለማስተማር መጠነሰፊ የሆነ የሰርቶ-ማሳያ እና የማስተዋወቂያ ሥራ መስራት<br>• የግብርና ቴክኒክ እና ሙያ ትምህት እና ስልጠና ማዕከላት ስለድህረ-ምርት እንዲያስለጥኑ እና የልማት ሠራተኞች የሰርቶ-ማሳያ ፓኬጅ እንዲኖራቸው ማድረግ<br>• ዩኒቨርሲቲዎች በድህረ-ምርት አያያዝ ስልጠና እንዲሰጡ እና በመስክ የሚደርሰውን የብክነት መጠን እንዲያጠኑ ድጋፍ ማድረግ |

# ክፍል ፲

## የክትትል እና ግምገማ እቅድ

### *የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት*

### *የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ወሰን*

*የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ዓላማዎች እንደታቀዱት እየተሰሩ እንድሆነ ለማረጋገጥ ጠንከር ያለ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ያስፈልጋል። ይህ ሥርዓት ሂደቶች በትክክል እየተፈፀሙ እንደሆነ፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሆነ እና የሚያፈሱት ኢንቨስትመንት ከተቀመጠው ዒላማ ወይም ግብ አንፃር በየጊዜው እየተቃኘ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መሰራት የሚገባቸው ሥራዎች እንዲስተካከሉ በማድረግ ሥራው እንዲቀጥል ያደርጋል። የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት በተለያዩ ደረጃዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ለመምራት እና ለመደገፍ ከማስቻሉ በተጨማሪ ለሀሳብ ልውውጥ ወጥ እና አስተማማኝ መንገድ ይሰጣል። እንዲሁም በእያንዳንዱ የሥራ አፈፃፀም ደረጃ ተከታታይ፣ መደበኛ እና ጊዜውን የጠበቀ እቅድ እና መረጃ ለማንጨት ዋና ዋና ተዋናዮችን ለማሳተፍ መንገድ ይከፍታል።*

*የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ሦስቱ ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።*

*ሀ፡ የኢንቨስትመንት እና የሥራ አፈፃፀም እቅድ በትክክል ሥራላይ መዋሉን መከታተል* ይህ ክትትል የሥራዎችን አፈፃፀም እና የውጤት አመላካቾችን በመጠቀም ሂደቱ ወደ ታቀዱት ውጤቶች እያመራ እንደሆን ለመከታተል ያስችላል። የሥራ አፈፃፀም ክትትል የሥራው ሂደት በታቀደው ጊዜ ውስጥ ውጤት ለመስጠት ምን ያክል ከታቀደው ሥራ እና በጀት ጋር ተጣጥሞ እየተከናወነ እንደሆን ለመገምገም ይጠቅማል። ስለሆነም ሁሉም ውህቦች እና መረጃዎች ሥራውን በሚሰሩ ኤጀንሲዎች ወይም ክፍሎች (ተግባሮችን በምዕራፍ አምስት ውስጥ ይመልከቱ) ግልጽ የሆነ የሪፖርት ቅጽ በመጠቀም ይሰበስባሉ።

*ለ፡ የሚሰሩ ሥራዎችን ተፅዕኖ እና ያመጡትን ለውጥ መከታተል፡* ስትራቴጂው ሥራላይ መዋሉን መከታተል (ሀ) አሁን ያለውን የድህረ-ምርት ብክነት መጠን (ለ) መለወጥ ያለበትን ሁኔታ ወይም ሂደት እና (ሐ) የአገሪቱን የድህረ-ምርት አያያዝ አፈፃፀም ለማሻሻል አሁን እየተፈፀመ ያለውን ሥራ ማሳየት አለበት። በድህረ-ምርት ብክነት ለውጥ እንዳለ ወይም እንደሌለ ለማየት ተፅዕኖ አመላካቾችን የሚያሳይ ውህብ መሰብሰብ ያስፈልጋል።

*ሐ፡ የተገኙ ተሞክሮዎችን ማጠናቀር፡* ከድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የተገኙ ቁልፍ ተሞክሮዎችን ለማጠናቀር በክትትል እና ግምገማ የተገኙ መረጃዎችን መተንተን እና መፃፍ ያስፈልጋል። ግምገማው እና ምርመራው የሚካሄደው መደበኛ በሆነ ጊዜ በሚቀጠሩ ባለሙያዎች ነው። የተገኙ ተሞክሮዎችን ማወቅ ተዋኒያኑ (ባለድርሻ አካላት) ለሚለዋወጠው የባለድርሻ አካላቶቻቸው ፍላጎት ቀድመው ምላሽ ለመስጠት ያስችላቸዋል። ስለሆነም በሚለዋወጠው ሁኔታ ውስጥ አስፈላጊ እና ህይወት ያላቸው ሁነው ይቀጥላሉ። ከሁሉም በላይ ጠቋሚዎች እና ተሞክሮዎች ውጤቶች ወደ ድህረ-ምርት አያያዝ ግብ እየደረሱ እንደሆን ለመገምገም መሰረት ብቻ ሳይሆኑ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የእህሉ ዘርፍ ውስጥ የሚከናወኑ ፕሮግራሞችን፣ ግቦችን፣ ዓላማዎችን እና አካሄዶችን በማስተሳሰር ውጤቶች እንዲገኙ ፖሊሲዎችን ለማስተካከል እና ለመለወጥ ይጠቅማሉ።

## የቃላት ትርጓሜ

የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት እና ሂደት በጥቂት ቁልፍ ፅንሰ-ሃሳቦች ላይ የቆመ ነው፡፡ ፅንሰ-ሃሳቦቹ ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ተካተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 4: ዋና ዋና የክትትል እና ግምገማ ቃላቶች ትርጉም

| ቃል | ትርጉም |
|---|---|
| ክትትል | በስትራቴጂው የተካተቱት መሰራት ሚገባቸው ሥራዎች በታቀደው መሰረት ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወን የመከታተል ሂደት ክትትል ይባላል፡፡ ክትትል የማስተካከያ ርምጃ በወቅቱ ለመውሰድ ያስችላል፡፡ ሥራው በሂደት ላይ እንዳለ ስልታዊ በሆነ መንገድ መረጃ የመሰብሰብ እና የመተንተን ሥራ ያካትታል፡፡ |
| ግምገማ | በኢንቨስትመንት እቅድ እና የሥራ አፈፃፀም እቅድ የተቀመጡት ውጤቶች በአገሪቱ የድህረ-ምርት አያያዝ ላይ ለውጥ እንዳመጡ እና እንዳላመጡ መከታተል ግምገማ ይባላል፡፡ የስትራቴጂው የግምገማ መመዘኛዎች፡- አግባብነት፣ ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት፣ የለውጥ ተደራሽነት፣ ዘለቄታዊነት እና ለሌሎች ያለው ጠቀሜታ ናቸው፡፡ |
| ውጤታማነት | ውጤታማነት የሚሰሩ ሥራዎች የሚያስገኙት ውጤት ተገቢነትን ያሳያል፡፡ ይህም በግብዓት እንደ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ሠራተኛ፣ መሳሪያዎች ወዘተ ሊሆን ችላል፡፡ |
| ፍሬያማነት | ፍሬያማነት የሚሰሩ ሥራዎች ምን ያክል የስትራቴጂውን ዓላማዎች እንዳሳኩ ይለካል |
| ለውጥ | በስትራቴጂው ለመፍታት ዒላማ የሆነውን ችግር ላይ ለውጥ እየመጣ እንደሆን ወይም እንዳልሆነ ያሳያል |

## የውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ እና ጠቋሚዎች

በክፍል 2 እንደተመለከተው ከውጤት ማዕቀፍ በመነሳት ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የሚውሉ የውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ እና ጠቋሚዎች ተሰርተዋል፡፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂው ክትትል እና ግምገማ ሥርዓት የተለዩት ጠቋሚዎች፣ መነሻዎች፣ እና ዒላማዎች በአዝል 2 በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ በአዝል 2 ሠንጠረዥ ሀ የለውጥ ጠቋሚዎችን፣ ሠንጠረዥ ለ የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ ጠቋሚዎችን እና ከሠንጠረዥ ሐ እስከ ሠንጠረዥ ረ ለእያንዳንዱ የሚጠበቅ ውጤት የአጭር ጊዜ ተፅዕኖ ጠቋሚዎችን ያሳያሉ፡፡

የዚህ ምዕራፍ ቀሪ ክፍል የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት መሰረታዊ ደንቦችን በአጭሩ ይገልፃል፡፡

## የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ዓላማዎች

ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት በምዕራፍ (ክፍል) 3 የተለዩትን ውጤቶች ማሳካት ላይ ያተኩራል፡፡ ከእነዚህ ውጤቶች ጋር የተሳሰሩ የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ፕሮግራሞች እና ተያያዥ ሥራዎች በክፍል 3 እንደተቀመጡት በታቀደው መሰረት በተለያዩ ባለድርሻ አካላት በክፍል 5 እንደተገለጸው በሥራላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ
- ትክክለኛ ሥራዎች እየተሰሩ እና ውጤቶች በውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ (አዝል 2) እንደተቀመጡት እየተገኙ እንደሆነ ማረጋገጥ
- ዒላማዎች በማይሳኩበት ሁኔታ እንደ ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓት ለማገልገል

- የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ስላለበት ደረጃ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት መደበኛ በሆነ ጊዜ መረጃ መስጠት እና ለማንኛውም ምርመራ እንደ መረጃ ማገልገል

- ፕሮግራሞች እና ተያያዥ ሥራዎች የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ዓላማዎችን ለማሳካት ያላቸውን አግባብነት እና ውጤታማነት ማረጋገጥ

- የሚሰሩ ሥራዎች በተከታታይ መስተካከላቸውን እና አቅጣጫ መያዛቸውን ማረጋገጥ እና ለሥራ ማስፈፀሚያ የሚሆን ሀብት መመደብ እና ማነቀሳቀስ

- የባለድርሻ አካላትን አቅም ግንባታ ማጠናከር የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ዓላማዎችን ለማሳካት ያለውን አስፈላጊነት ማረጋገጥ ናቸው፡፡

*ግምገማ*

ውጤትን መሰረት ያደረገ ግምገማ የውጤት የስኬት ደረጃዎችን በአጭር ጊዜ ፣ በመካከለኛ ጊዜ እና በአጠቃላይ በለውጥ ደረጃ በመለየት እንዲሁም ውጤታማ የሆኑ እና ያልሆኑ አካሄዶችን በመለየት የክትትል ሂደትን ያጠናክራል፡፡ በተጨማሪም ግምገማ ለውድቀት ወይም ለስኬት መልስ እንዲሁም ከሁለቱም ክስተቶች ለመማር እድል ይሰጣል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 5 የተገለጹት የግምገማ አካሄዶች ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ግምገማ ይውላሉ፡፡

ሠንጠረዥ 5: ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ግምገማ የአካሄድ ዓይነቶች

| የግምገማ ዓይነት | ገለፃ | የሚሰራበት ወሰን | ሃላፊ |
|---|---|---|---|
| መነሻ | ይህ ጥናት ሲሆን (ለድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ገና የሚጠና ነው) ስትራቴጂው ሥራላይ ከመዋሉ በፊት የነበረውን ሁኔታ ለቀጣይ ግምገማዎች እንደ መነሻ መሰረት እንዲሆን የማረጋገጫ መረጃ ያመነጫል | ለሁሉም የድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ ተፅዕኖ ጠቋሚዎች ይሰራል | እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር (እተሀሚ)፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር እና ልማት ተቋማት |
| ዓመታዊ ግምገማ | ሁሉንም ያካተተ ሙሉ ዓመታዊ የግምገማ ሪፖርት ሲሆን ስለአፈፃፀሙ ዝርዝር መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ ሪፖርቱ በሁሉም ዘርፎች ወይም የትግበራ ቦታዎች የጋራ የሆኑ ጉዳዮችን፣ የሚሰሩ ሥራዎችን እና ሂደቶችን ዘላቂነት ማሳየት አለበት፡፡ | ለስትራቴጂው ኢንቨስትመንት እና ለሥራ አፈፃፀም እቅድ | እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር (እተሀሚ) |
| የአጋማሽ ጊዜ ግምገማ | የአጋማሽ ጊዜ ግምገማ በውስጥ ወይም በውጭ ገምጋሚ ሊከናወን ይችላል፡፡ የተገኙትን ውጤቶች በማብራራት እና በመተንተን ከውጤት ማዕቀፍ እቅድ ጋር ያነፃጽራል፡፡ ከንድፍ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች፣ በመጀመሪያ የተገኙ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተሞክሮዎች እና መስተካከል ያለባቸው ሥራዎች ላይ ያተኩራል፡፡ | ለስትራቴጂው ውጤቶች እና ተፅዕኖዎች | እተሀሚ ወይም ገለልተኛ ገምጋሚ |
| የመጨረሻ ግምገማ | ስትራቴጂው ሥራላይ ከዋለ በኋላ የሚደረገው ግምገማ በዓላማ ስኬቶች እና ለግቦች ያደረጉት አስተዋፅዖ ላይ ያተኩራል፡፡ ስኬቶችን ከመነሻ (የመነሻ ቅኝት) ጋር በማወዳደር አንድ ልዩ ተፅዕኖ መሳካት ወይም አለመሳካቱን እና ምን ያክል ለታቀደው ለውጥ አስተዋፅዖ አበርክቷል የሚሉትን ሪፖርቱ ያካትታል፡፡ ውጤታማነት፣ የተገኙ ለውጦች እና ዘላቂነት መታየት የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ | ለስትራቴጂው ኢንቨስትመንት እና ለሥራ አፈፃፀም እቅድ እና ለተፅዕኖ ጠቋሚዎች | ገለልተኛ ገምጋሚ |

*ሪፖርት ማድረግ*

የክትትል እና የግምገማ ሥርዓቱ በብዙ የግምገማ ስብሰባዎች ይደገፋል። ከዚህ በታች እንደተገለፀው ስብሰባዎች የሩብ ዓመት ግምገማ፣ የዓመታዊ ግምገማ፣ አርሶ አደሮችን መጎብኘት ወዘተ ናቸው።

ሀ፡ የሩብ ዓመት አፈፃፀም ግምገማ፡ በክፍል 5 እንደተገለፀው ስትራቴጂውን ሥራላይ በሚያውሉ ባለድርሻ አካላት የሚፈጸም ነው። ሪፖርቱ ለሚሸፍነው ጊዜ የልኬት እና የዓይነት መረጃ ትንተናዎችን ያካተተ እና በሩብ ዓመቱ የነበረውን አጠቃላይ አዝማሚያ ማንፀባረቅ አለበት። የዚህ ግምገማ ዓላማ ሂደቶችን ከውጤት ስኬት ጋር ማነፃፀር እና ለግብ ስኬቶች ያላቸውን ተፅዕኖ መተንተን ነው። ሪፖርቱ ስለ ተግዳሮቶች፣ ክፍተቶች፣ የተገኙ ተሞክሮዎች እና እነዚህ ጉዳዮች እንዴት ከእቅድ እና ከአፈፃፀም ሂደት ጋር ሊቀናጁ እንደሚችሉ መተንተን አለበት።

ለ፡ ግምገማውን የሚያከናውኑ ኤጀንሲዎች ውስጥ የሚሰሩ የቴክኒሻን ቡድኖች አርሶ አደሮችን እና ተቋማትን የሚገመግሙ (የሚጎበኙ) ከሆነ ውጤቶችን ለማሳካት የሚደረገውን አጠቃላይ ሂደት በተለይም በሥራ አፈፃፀም ጊዜ የገጠሙ ተግዳሮቶችን እና ክፍተቶችን መገምገም ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው። ምን ያክል ውጤት ተገኘ የሚለው ዋና ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ቢሆንም ውጤቶች ወደ ዒላማ የቀረቡ ናቸውን? የሚለውን ጥያቄም የቴክኒሻን ቡድኑ መገመገም አለበት።

ሐ፡ ዓመታዊ ግምገማ፡ የታቀደው ዓመታዊ እቅድ እንደታቀደው እየተፈፀመ እንደሆነ እና የሚሰሩ ሥራዎች በድህረ-ምርት ብክነት ላይ ተፅዕኖ እያመጡ እንደሆነ በዓመታዊ ግምገማ ላይ ይታያል። ግምገማው በክፍል 5 ተለይቶ እንደተቀመጠው በሁሉም ባለድርሻ አካላት ይከናወናል።

የክትትል እና ግምገማ አስተዳደር አካል

ክትትል እና ግምገማ የማከናወን ሀላፊነት በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥር አዲስ የሚቋቋመው የደህረ-ምርት አያያዝ ዳይሬክቶሬት ይሆናል።

## እዝል 1: በድህረ-ምርት አያያዝ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች እና መሰራት የሚገባቸው ተግባራት (ዋዓ = ዋና ዓላማ)

### ሠንጠረዥ ሀ

| | | | |
|---|---|---|---|
| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ | | ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተዋፅዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | |
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚ-ምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር | |
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት በማላመድ እና ሥራላይ በማዋል በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ | |
| ውጤት 1<br>(ዋዓ 1) | ዋና ዋና ሥራዎች | ዓላማዎች | መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች |
| 1. ምግብ ላይ የሚደርስውን የመጠን እና የጥራት ብክነት መቀነስ | 1.1. ውጤታማ የሆነ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ማስፋፋት | ሀ፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ አመች የሆነ የተቋም የክትትል እና የግምገማ ሥርዓትን ጨምሮ እና የአሰራር መዋቅር መመስረት እና በማጠናከር ለመንግስታዊ ድርጅቶች እና ለግሉ ዘርፍ ግልጽ ሀላፊነት እና ሚና ከተጠያቂነት ጋር መስጠት<br>ለ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ውስጥ ያሉ መልካም ተሞክሮዎችን በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ላይ ማስተማር እና ማስፋፋት<br>ሐ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን የሚያስተባብር የተለያዩ ዘርፎችን (ግብርና፣ ጤና፣ ሥነምግብ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ወዘተ) ያካተተ አስተባባሪ መመስረት<br>መ፡ በሁሉም የግብርና እሴት ሰንሰለት ደረጃዎች ለሚሰሩ ሥራዎች በቂ ገንዘብ መመደብ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ ማድረግ | 1.1.1፡ ሁሉን ዓቀፍ የሆነ በፌደራል፣ በክልል እና በወረዳ ደረጃ የድህረ-ምርት አያያዝ የምክክር-መድረክ መመስረት እና ማጎልበት<br>1.1.2፡ በእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥር በሁሉም ደረጃ የድህረ-ምርት ክፍል መክፈት እና ማጠናከር<br>1.1.3፡ የድህረ-ምርት አያያዝን ለማስፋፋት የድህረ-ምርት አያያዝ መገናኛ እና ግንዛቤ መፍጠሪያ እቅድ ማዘጋጀት<br>1.1.4፡ ዓመታዊ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች ኤግዚቢሽን መመስረት |
| | 1.2. የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን ለመደገፍ የማላመድ ምርምርን እና ልማትን ማስፋፋት | ሀ፡ የምርምር እና ልማት ተቋማት እንዲሁም ዩኒቨርሲቲዎች በድህረ-ምርት አያያዝ ዙሪያ ምርምር እንዲሰሩ እና ስልጠና እንዲሰጡ ማመቻቸት<br>ለ፡ የመንግስት እና የግል ዘርፉ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ በጋራ ምርምር እና ልማት እንዲሰሩ ማበረታታት<br>ሐ. በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ በሁሉም ደረጃ የሚከሰተውን ብክነት በመጠን እና በገንዘብ ተመን ለመለካት እንዲሁም ውሳኔዎቸን ለመወሰን የሚረዱ በጥናት የተደገፉ ማስረጃዎችን ለማመንጨት የሚካሄዱ ጥናቶችን መደገፍ | 1.2.1፡ ስለድህረ-ምርት አያያዝ የተግባር ትምህርት የሚሰጥበትን ሥርዓት መመስረት እና መቆጣጠር<br>1.2.2፡ በመስክ እና በቤተ-ሙከራ (ላቦራቶሪ) ውስጥ የሚሰሩ የድህረ-ምርት ግመታ እና ትንተና ሥራዎችን ለመደገፍ ለዩኒቨርሲቲዎች እና /ወይም የምርምር ተቋማት ገንዘብ በውድድር የመስጫ ሥርዓት መመስረት<br>1.2.3፡ በየዓመቱ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት የሚዘግብ ዓመታዊ የስታትስቲክስ መጽሔት ማተም መጀመር<br>1.2.4፡ ለድህረ-ምርት ግምገማ የሚውሉ ግልጽ አካሄዶችን እና መንገዶችን ማውጣት<br>1.2.5፡ ተደራሽ የሆኑ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን ከውጪ በማስገባት ማላመድ እና ማስፋፋት<br>1.2.6፡ የምግብ ብክነትን ለመቀነስ የድህረ-ምርት አያያዝ ዘዴዎችን እና ቴክኒኮችን ማላመድ እና ማስፋፋት<br>1.2.7፡ ምግብ ሳይበላሽ ለማቆየት የሚያስችሉ አዳዲስ የምግብ አዘገጃጀት ዘዴዎችን ማስፋፋት |

| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ | | ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተዋፅዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | |
|---|---|---|---|
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚ-ምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር | |
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት በማላመድ እና ሥራላይ በማዋል በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ | |
| ውጤት 1 (ዋን 1) | ዋና ዋና ሥራዎች | ዓላማዎች | መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች |
| | 1.3: የማምረት፣ የማጨድ እና የማከማቸት ሥራን የሚያቃልሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማመንጨት እና ማሰራጨት | ሀ፡ አግባብነት ያለው እና ተደራሽ የሆነ ቴክኖሎጂ በማንጨት አጨዳን፣ ውቂያን፣ ማድረቅን፣ ማሸግን፣ ማጓጓዝን እና የማከማቸት ሥራን በማገዝ  የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀንስ  ተቀናጅተው የሚሰሩ ምርምሮች እና ልማቶችን ማስፋፋት<br>ለ፡ የድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ እንዲሁም ለጥገና እና ሰርቪስ አገልግሎት የሚውል የገንዘብ አቅም እንዲኖር አበረታችና በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የገንዘብ አቅርቦት መፍጠር<br>ሐ. የድህረ-ምርት ብክነትን የሚያስከትሉ ማሽነሪዎችን ብቃት ለማሻሻል መሣሪያዎችን /ማሽኖችን የሚያንቀሳቅሱ እና የሚጠግኑ ባለሙያዎችን አቅም መገንባት<br>መ፡ ስለመሣሪያው አጠቃቀም የተሰጡትን ዝርዝር ደንቦች ተጠቃሚው እንዲከተል የሚያስገድድ የቁጥጥር ማዕቀፍ እና አስፈጻሚ ተቋም መመስረት<br>ሠ፡ የመሣሪያ እና የማሽነሪ ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ማቋቋም እና ማስፋፋት | 1.3.1፡ የሜካናይዜሽን ስትራቴጂን ለመተግበር የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን መለየት እና ተያያዥ የኢንቨስትመንት እቀድ ማውጣት<br>1.3.2፡ ቅድሚያ የተሰጣቸውን የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ እንዲመረቱ / እንዲገጣጠሙ እና እንዲሰራጩ ማበረታታት<br>1.3.3፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን በተግባር ለማሳየት ስርቶማሳያ ማዕከላትን መመስረት<br>1.3.4፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ ማሽኖች ጥገና፣ ማቆያ፣ ማሰልጠኛ እና ኪራይ መስጫ ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር እንዲሁም ከ RTCs ጋር በማጣጣም በወረዳ ደረጃ የአገልግሎት ማዕከላትን ማቋቋም<br>1.3.5፡ በወረዳ ደረጃ ለሚመሰረቱት የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያዎች እና ማሽነሪዎችን ማሟላት<br>1.3.6፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን ዲዛይን፣ አመራረት እና ብቃት ደረጃ መሟላቱን ለማወቅ ብሔራዊ የቁጥጥር እና የማስፈፀሚያ ሥርዓት መመስረት<br>1.3.7፡ ለማሽነሪዎች (የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ) ለመፈተሽ ብሔራዊ የመፈተሻ እና ማረጋገጫ ማዕከል ለማቋቋም የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ |
| | 1.4:  በድህረ-ምርት አያያዝ የክህሎት፣ የስልጠና እና የሰው ልማትን ማሻሻል | ሀ፡ በግብርና ሙያ እና ቴክኒክ ስልጠና ኮሌጆች እና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ  ለሚሰጡ የድህረ-ምርት የጽንሰ-ሀሳብ እና የተግባር ስልጠናዎች የሚያገለግል ድህረ-ምርትን ያካተተ ጠንካራ ሥርዓተ- ትምህርት ማዘጋጀት<br>ለ፡ ስለ ድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ስልጠና የሚሰጡ የልቀት ማዕከላትን መመስረት<br>ሐ. በድህረ-ምርት ብክነት፣ ምንጭ እና መፍትሄዎች ዙሪያ ያሉ ሳይንሳዊ እና አገር-በቀል እውቀቶችን ማሰራጨት<br>መ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ለሰለጠኑ ባለሙያዎች ማበረታቻ መስጠት እና የሥራ እድል  ማመቻቸት<br>ሠ፡ በድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት ላይ በሚሰሩ የክህሎት እና የሰው ልማት ሥራዎች  ውስጥ  ሥርዓተ-ፆታን በተለይም ለሴቶች እና ለወጣቶች ትኩረት መስጠት | 1.4.1፡ በዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ውስጥ የድህረ-ምርት ኢንጂነሪንግ ፕሮግራም ለመጀመር የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ<br>1.4.2፡ ለአርሶ አደሮች እና ለሌሎች ተጠቃሚዎች የንግድ አያያዝ ክህሎትን የሚያበለጽጉ ስልጠናዎችን ለሚሰጡ የስልጠና ማዕከላት በጀት መመደብ<br>1.4.3፡ ከግል ባላሀብቶች ጋር በመተባበር የድህረ-ምርት አያያዝ የስልጠና / የመለማመጃ ፕሮግራም መመስረት እና እንደ ሙያ እውቅና መስጠት<br>1.4.4፡ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲን በድህረ-ምርት አያያዝ ባለሙያዎች ማጠናከር<br>1.4.5፡ በድህረ-ምርት አያያዝ የአገር በቀል እውቀቶችን ጨምሮ አገልግሎት የሚሰጡ የልቀት፣ የስልጠና እና የኤክስቴንሽ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማጠናከር<br>1.4.6፡ የድህረ-ምርት አያያዝን ጨምሮ ደረጃ እንዲያወጣ እና እንዲፈትሽ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ቢሮን ማጠናከር<br>1.4.7፡ የልማት ሠራተኞች ስለድህረ-ምርት አያያዝ ያላቸውን እውቀት ለማበልጸግ ለግብርና ሙያ እና ቴክኒክ ማሰልጠኛ ትምህርት ቤቶች የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ<br>1.4.8፡ በልማት ሠራተኞች የፓኬጅ መመሪያ ውስጥ የድህረ-ምርት አያያዝ ፓኬጅን መጨመር<br>1.4.9፡ ሴቶች እና ወጣቶች ላይ ያተኮረ ስለድህረ-ምርት አያያዝ መሰረታዊ እውቀትን የሚያስጨብጥ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም መጀመር |

| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ | ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተዋፅዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | | |
|---|---|---|---|
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚ-ምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር | | |
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓት በማላመድ እና ሥራላይ በማዋል በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ | | |
| ውጤት 1 (ዋን 1) | ዋና ዋና ሥራዎች | ዓላማዎች | መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች |
| | | | 1.4.10፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎች ላይ የጥገና እና አያያዝ አገልግሎት በመስጠት ሴቶች እና ወጣቶች እንዲሳተፉ ማስቻል<br>1.4.11፡ መልካም የግብርና አሰራርን (የተሻሻለ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኒክን ጨምሮ) ለመጠቀም የብሀሪ ለውጥን ማስፋፋት |
| | 1.5 ፡ ዘላቂነት ያለው የአካባቢ አያያዝን ማስፋፋት | ሀ፡ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓትን መዘርጋት እና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ የግብርና አመራረት ዘዴዎችን በመጠቀም የእጽዋት ሽፋን እንዲጨምር ማድረግ፡፡ የአፈር መከላትን መቀነስ፣ በእጽዋት የተወሰዱ ወይም በአፈር መሸርሸር የተወገዱ ማዕድናትን መተካት፣ የውሀ ፍጥነትን እና የሚባክነው ይዘት መጠን ለመቀነስ እርከን ፣ የአፈር ክትር ወዘተ መስራት<br>ለ፡ ከድህረ-ምርት ተግባራት ጋር በተያያዘ የጠፉ ደንን እንደገና እንዲለማ ማድረግ እና ደንን ለኢኮኖሚያዊ እና ለሥርዐተ-ምህዳር (ኢኮሲስተም) ጥቅም እንዲውል እንደገና መትከል እና መጠበቅ<br>ሐ፡ የተቀናጀ ተባይ መከላከልን በመተግበር የፀረ-ተባይ እና የሌሎች ኬሚካሎችን አጠቃቀምን መከታተል እና መቆጣጠር፣ የፀረ-ተባይ ሽያጭን፣ አጠቃቀምን እና አወጋገድን በህጋዊ መንገድ ማስከበር | 1.5.1፡ ስለአግሮ-ኬሚካል (ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር) አጠቃቀም፣ አሻሻጥ፣ አያያዝ እና አወጋገድ መመሪያ ማውጣት<br>1.5.2፡ ስለአግሮ-ኬሚካል (ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር) አሻሻጥ፣ አያያዝ እና አወጋገድ የወጣውን መመሪያ ለሚያስፈጽሙ አካላት አስፈላጊ ነገሮችን ማሟላት እና ማጠናከር<br>1.5.3፡ ስለአግሮ-ኬሚካል (ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ጭምር) አጠቃቀም፣ አሻሻጥ፣ አያያዝ እና አወጋገድ የስልጠና ፕሮግራም መጀመር<br>1.5.4፡ ስልጠና፣ እውቅና እና ሌሎች አገልግሎቶች የሚሰጡ የተመሰከረላቸው የኬሚካል አያያዝ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ መደገፍ<br>1.5.5፡ ፀረ-ተባይን ያለአግባብ መጠቀም ከድህረ-ምርት አያያዝ ጋር በተገናኘ ጨምሮ ስላለው ያልተፈለገ ጉዳት ግንዛቤ መፍጠር |

# ሠንጠረዥ ለ

| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ | | ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተወጽዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | |
|---|---|---|---|
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርስውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር | |
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን በማላመድ እና በመተግበር በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ | |
| ውጤት 2 (ዋዓ 2) | ዋና ዋና ሥራዎች | ዓላማዎች | መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች |
| 2. የግብርና ግብዓቶች እና ምርቶች ገበያ ቅልጥፍናን ማሻሻል | 2.1፡ ዘለቂታ ያለው እና ተደራሽ የሆነ የድህረ-ምርት ሥርዓት ማስፋፋት | ሀ፡ ለእያንዳንዱ የአቅርቦት ሰንሰለት ደረጃ ተስማሚ እና ተደራሽ የሆነ ማከማቻ በቤት (በአባወራ)፣ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን እና በክልል ደረጃ ማቋቋም<br>ለ፡ ውጤታማ እና ተደራሽ የሆኑ የማከማቻ ቴክኖሎጂዎችን ለምሳሌ የብረት ጎተራ እና የተሻሻሉ አገር-በቀል ማከማቻዎችን ማምረት እና በሰፊው የማሰራጨት ሥራን ማሳለጥ እና ማስፋፋት<br>ሐ፡ በማከማቻ መሰረተ-ልማት አቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ የመንግስት እና የግል ዘርፉን ማስተሳሰር | 2.1.1፡ የተሻሻሉ የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን ማስፋፋት<br>2.1.2፡ በሁሉም ሥርዓት ተቀባይነት እና ታማኝነት ያለው የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ሥርዓትን ማስፋፋት<br>2.1.3፡ የተሻሻሉ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ መደገፍ<br>2.1.4፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ ለሚያመርቱ አምራቾች የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ የግብር እፎይታ እና የመሳሰሉትን ድጋፎች ማድረግ<br>2.1.5፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን እንዲያሰራጩ የግብርና ግብዓት ነጋዴዎችን ማስፋፋት |
| | 2.2: ውጤታማ የማከማቻ አያያዝ ሥርዓትን ሥራላይ ማዋል | ሀ፡ ከምግብ ደህንነት ጋር የተያያዙ እንደ የማከማቻ ቦታ ስፋት፣ የእህል ንጽህና እና ጥራትን ለመሳሰሉት ጉዳዮች ደረጃ ማውጣት እና ተግባራዊ ማድረግ<br>ለ፡ የማጠኛ ፀረ-ተባዮችን አጠቃቃም እና አወጋገድ ጨምሮ ተገቢ የሆነ የማከማቻ ተባዮች መቆጣጠሪያ መንገዶችን ማስተዋወቅ እና ማስፋፋት<br>ሐ፡ ለመጋዘኖች ደረጃ መስጠት እና ደረጃ ላሟሉ እውቅና የመስጠትን ሥርዓት ማስፋፋት | 2.2.1፡ የመጋዘን ደረጃ አጽዳቂ እና ቁጥጥር ሥርዓትን መዘርጋት<br>2.2.2፡ የመጋዘን አጽዳቂ እና ቁጥጥር ኤጀንሲ ማቋቋም<br>2.2.3፡ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን መጋዘኖች በተለይም በአነስተኛ (የገጠር) የገበያ ቦታዎች ግንባታን መደገፍ<br>2.2.4፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን ያገናዘበ የእህል አያያዝ፣ የመጋዘን አስተዳደር እና መጋዘን ውስጥ ለሚሰሩ ሥራዎች መመሪያ ማውጣት<br>2.2.5፡ ለማከማቻ ተባዮች ቁጥጥር የተቀናጀ ተባይ መከላከል ሥርዓትን ማጠናከር<br>2.2.6፡ የመጋዘን ሠራተኞችን በእህል አያያዘ እና አስተዳደር ማሰልጠን<br>2.2.7፡ ማከማቻ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካሎችን የምዝገባ፣ የአያያዝ፣ የአስተዳደር እና የቁጥጥር ሥርዓትን ማዘመን |
| | 2.3: የትራንስፖርት ሥርዓትን እና የግብይት ትስስርን ማሻሻል | ሀ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ምርታቸውን ከማሳ ወደ ቤታቸው ወይም ከቤታቸው ወደ ገበያ ለማጓጓዝ የሚያስችሉ አነስተኛ እና ጉልበት ቆጣቢ የማጓጓዣ መሳሪያዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚገጣጥሙ ድርጅቶች በየአካባቢው እንዲፈጠሩ እና እንዲጎለብቱ ማመቻቸት<br>ለ፡ የመጋቢ እና የዋና ዋና መንገዶችን ትስስር ማሻሻል እና ማልማት<br>ሐ፡ ሸቀጦችን ከወረዳ ወደ ዞን፣ ከዞን ወደ ክልል ለማጓጓዝ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎችን ግዥ መደገፍ<br>መ፡ የትምህርት ደረጃን ለማሻሻል፣ እውነተኛ እና የዕለት መረጃ ለማግኘት፣ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ለመጠቀም እና ሌሎች የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂ ሊሰጣቸው የሚችለውን ጥቅሞችን የገጠሩ ሕዝብ እንዲያገኝ የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂን ማስፋፋት<br>ሠ፡ እንደ የምርት መፈተሻ ማዕከል የመሳሰሉ አገልግሎት መስጪያ ድርጅቶችን በገጠሩ አካባቢ መመስረት<br>ረ፡ በገበያ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ተበረታትተው የግል ድርጅት ለማቋቋም የሚፈልጉ አርሶ አደሮችን እና በገጠሩ አካባቢ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን የሚያመርቱ ድርጅቶችን ከገንዘብ ብድር እና ቁጠባ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር | 2.3.1፡ አነስተኛ መጠን ያላቸውን የግብርና እና በእርሻ ደረጃ የማጓጓዣ መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ መደገፍ<br>2.3.2፡ አማራጭ የተሻሻለ የእርሻ ትራንስፖርት ሥርዓት ማስፋፋት<br>2.3.3፡ መጋቢ መንገዶችን ለማሻሻል እና ለመጠገን ድጋፍ ማድረግ<br>2.3.4፡ ሞባይልን በመሳሰሉ መሳሪያዎች መረጃ ማስተላለፍን ለማሳለጥ አግባብ ያለው የመረጃ እና ግንኙነት ቴክኖሎጂን መንደፍን እና ሥራላይ ማዋልን ማበረታታት |

<table>
<tr><td colspan="2">የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ</td><td colspan="2">ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተወጽዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ</td><td colspan="2">የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርስውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር</td></tr>
<tr><td colspan="2">የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ</td><td colspan="2">አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን በማላመድ እና በመተግበር በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ</td></tr>
<tr><th>ውጤት 2<br>(ዋዓ 2)</th><th>ዋና ዋና ሥራዎች</th><th>ዓላማዎች</th><th>መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች</th></tr>
<tr><td></td><td>2.4: ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል</td><td>ሀ፡ ዓለም ዓቀፍ የእህል ዓይነት እና ደረጃን እንደ መነሻ በመጠቀም ለሰብል ምርቶች ዓይነት እና ደረጃ ማውጣት<br>ለ፡ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓቱን የሚደግፉ የጥራት መፈተሻ ቤተ-ሙከራዎችን (ላቦራቶሪዎችን) ማቋቋም<br>ሐ. የተሻሻሉ የድህረ-ምርት አያያዝ ሥራዎች ይበልጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ዋጋ እንደ ምርቱ የጥራት ደረጃ እንዲከፈል የሚያደርግ ሥርዓት መመስረት<br>መ፡ የወጡትን የዓይነት እና ደረጃ ደንቦች ለሚያስፈጽሙ አካላት የአቅም ግንባታ ማድረግ</td><td>2.4.1፡ የእህል ዓይነትን እና ደረጃን ማሻሻል<br>2.4.2፡ የዓይነት፣ የደረጃ እና የጥራት ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር<br>2.4.3፡ የዓይነት፣ የደረጃ እና የጥራት መፈተሻ እና ማሰልጠኛ ማዕከል ማቋቋም<br>2.4.4፡ የተመሰከረለትን ዓይነት፣ ደረጃ እና ጥራት ለሚቆጣጠሩ ተቋሞች ድጋፍ ማድረግ<br>2.4.5፡ የላቦራቶሪ ቴክኒሻኖችን በዓይነት፣ በደረጃ እና በጥራት ፍተሻ ላይ ማሰልጠን</td></tr>
<tr><td></td><td>2.5: የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል</td><td>ሀ፡ ለምግብ ደህንነት ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ሃላፊነት መስጠት እና አቅም መገንባት<br>ለ፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎችን በማጓጓዣዎች፣ በመጋዘኖች፣ በማከማቻዎች እና በገበያዎች ተፈፃሚ ማድረግ</td><td>2.5.1፡ የምግብ ደህንነት ደረጃዎች ሥራላይ እንዲያውል፣ ክትልል እና ተፈጻሚ እንዲያደርግ የምግብ እና ደህንነት ጥበቃን እንደገና ማቋቋም<br>2.5.2፡ የምግብ ደህንነት መርማሪዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማሟላት<br>2.5.3፡ የምግብ ደህንነት እና ከምግብ ደህንነት ጋር የተያያዙ የመጋዘን እና የትራንስፖርት ደረጃዎችን መገምገም እና ማሻሻል<br>2.5.4፡ የምግብ ደህንነት መርማሪዎችን በምግብ ደህነት ማሰልጠን</td></tr>
<tr><td></td><td>2.6: የግብርና ገበያ የመረጃ ሥርዓትን ማሳደግ</td><td>ሀ፡ የድህረ-ምርት ብክነት የምክክር-መድረክ ውጤታማ ሥራ እንዲሰራ ማስቻል<br>ለ፡ የግብርና መረጃ አያያዝ ሥርዓት መመስረት<br>ሐ፡ መረጃ የማግኘት መብትን የግብርና ገበያ መረጃ ለማግኘት ተግባራዊ ማድረግ</td><td>2.6.1፡ የግብርና ገበያ መረጃ ሥርዓት መመስረት<br>2.6.2፡ የምርት ግብይትን እና ልውውጥን ማሳደግ</td></tr>
<tr><td></td><td>2.7: የአስተሻሸግ እና የአያያዝ ሥርዓት ማውጣት እና ሥራላይ ማዋል</td><td>ሀ፡ ማሸጊያው ከምን ቁስ መሰራት እንዳለበት፣ የማሸጊያው የቁምት እና የወርድ ስፋት ስንት መሆን እንዳለበት፣ የአሰራሩን ዓይነት (የማጠን ሥራን እና ለአየር ጠባይ ተጋላጭነትን እሳቤ ውስጥ ያስገባ አሰራር)፣ ከተሞላ በኂላ አሰፋፉን ወይም አስተሳሰሩን፣ መለያ አፃፃፍ እና ሌሎች የማሸጊያ ዝርዝር ደንቦችን ማውጣት<br><br>ለ፡ የማይገባ ማሸጊያ መጠቀምን ብሎም የድህረ-ምርት ብክነትን ለማስቀረት እንዲቻል የተለያየ ዲዛይን እና አወቃቀር ያላቸውን ማሸጊያዎች በተገቢ ሁኔታ አርሶ አደሮች እንዲጠቀሙ ማበረታታት<br>ሐ፡ ለአያያዝ አመች የሆነውን፣ ፍሰትን እና ብክነትን የሚቀንሰውን እዲሁም ተባይን እና ዘረ-አይጦችን ለመከላከል የሚያመቸውን አነስተኛ እና በ 50 ኪ.ግ. መጠን ያለውን ማሸጊያ በመጠቀም መልካም የመጋዘን አያያዝ ሥርዓትን ማስፋፋት</td><td>2.7.1፡ የማሸጊያውን ዓይነት፣ ጥቅም እና ጥራት የመሳሰሉትን መስፈርቶች ከዓለም ዓቀፍ ደረጃዎች ጋር በማጣጣም የአስተሻሸግ ደረጃ ማውጣት<br>2.7.2፡ አየርአልባ ከረጢትን (ጆንያዎችን) መጠቀምን ማስፋፋት<br>2.7.3፡ የማዳበሪያ ከረጢት እና አየርአልባ ከረጢትን በአገር ውስጥ እንዲመረቱ ወይም እንዲሰሩ ማበረታታት</td></tr>
</table>

# ሠንጠረዥ ሐ

| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ | | ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተወጽዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | |
|---|---|---|---|
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርስውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር | |
| የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ | | አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን በማላመድና በመተግበር በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ | |
| ውጤት 3<br>(ዋዓ 3) | ዋና ዋና ሥራዎች | ዓላማዎች | መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች |
| 3: ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ (የፋይናንስ) አቅርቦት እና የኢንቨስትመንት ተደራሽነትን ማሻሻል | 3.1: ለድህረ-ምርት አያያዝ የገንዘብ አቅርቦት ተደራሽነትን እና ኢንቨስትመንትን ማሻሻል | ሀ፡ ጥሬ-እቃዎችን ከውጪ አስገብተው የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለሚያመርቱ አምራቾች እና/ወይም የዕደ ጥበብ ሙያተኞች ከግብር ጋር በተገናኘ ድጋፍ ማድረግ<br>ለ፡ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዩኒየኖች የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂዎችን እንዲገዙና ለአርሶ አደሮች አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት | 3.1.1፡ በከፊል አገር ውስጥ ለተገጣጠሙ ወይም ሙሉ ለሙሉ ለተመረቱ ቴክኖሎጂዎች / ማሽነሪዎች የግብር ቅናሽ ማድረግ<br>3.1.2፡ ለሥራ ፈጣሪዎች የንግድ ስልጠና እና የአገልግሎት ድጋፍ ፕሮግራም መጀመር<br>3.1.3፡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂ የኪራይ አገልግሎት ሰጭዎችን መደገፍ<br>3.1.4፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ አገልግሎት እንደብድር ማስያዣ የሚያገለግል የብድር ዋስትና አገልግሎት ከገንዘብ ተቋማት እና ከመድህን ድርጅቶች ጋር በመተባበር መመሥረት |
| | 3.2: ማበረታቻዎች እና አዳዲስ ፈጠራዎችን ያካተተ የገንዘብ አገልግሎት | ሀ፡ የህብረት ሥራ ማህበራት እና ዮኒየኖች ለአርሶ አደሮች ብድር ማቅረብ እንዲችሉ አቅማቀቸውን መገንባት<br>ለ፡ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያን የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማግኘት እንዲችሉ አዳዲስ የገንዘብ አግልግሎቶችን መስጠት<br>ሐ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ከሚፈጽሙት የድህረ-ምርት ብክነትን መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች ግዥ ጋር በተገናኘ በዝቅተኛ ወለድ ብድር ከአበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ማግኘት እንዲችሉ ለአነስተኛ አበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ስልታዊ ድጎማ ማድረግ | 3.2.1፡ ለብድር አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጡ የአቅም ግንባታ (የሰው እና የቁሳቁስ) ስራዎችን ማጠናከር<br>3.2.2፡ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ደረሰኝ ሥርዓትን ማስፋፋት<br>3.2.3፡ የቡድን የብድር ዋስትና ሥርዓትን ማጠናከር<br>3.2.4፡ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር በአካባቢ ደረጃ አነስተኛ የገንዘብ አበዳሪ ተቋማትን ማስፋፋት<br>3.2.5፡ ለድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኖሎጂ ለሚውል ብድር በቅናቀሽ ወለድ ማበደር<br>3.2.6፡ የወደፊት ርክክብ ውል እና የኮንትራት እርሻ ሥርዓትን ማስፋፋት |
| | 3.3: ግብርናዊ ቢዝነስ፣ የአርሶ አደሮችን ኢንተርፕራይዞች እና የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችን በኩታ-ገጠም ማደራጀት | ሀ፡ ሰፊ የሥራ መጠን (ትልቅ የሥራ ድርጅት) በመፍጠር እርስ በእርስ መጠቃቀም እንዲችሉ እና በቀላሉ የገንዘብ ብድር አገልግሎት በማግኘት የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስ እንዲችሉ በግብርና የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ባሉ ተዋንያን መካከል ሽርክና መፍጠር<br>ለ፡ ለአርሶ አደሮች ስልጠና፣ የገበያ መረጃ፣ የብድር እና ቁጠባ አገልግሎት፣ የመደራደር ክህሎትን እና ሌሎች ከድህረ-ምርት ብክነት ቅነሳ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በብቃት መስጠት እንዲችሉ የአርሶ አደሮችን ድርጅቶች እና ህብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር | 3.3.1፡ ለኩታ-ገጠም ሥራ ገንዘብ ለማግኘት የመነሻ-ሀሳብ (ፕሮፖዛል) መቅረጽ<br>3.3.2፡ ድህረ-ምርትን ጨምሮ በሁሉም የግብርና እሴት ስንሰለቶች የንግድ ኩታ-ገጠም ጽንሰ-ሀሳብን ማስፋፋት<br>3.3.3፡ የአርሶ አደሮች ማህበራት ለአባላቶቻቸው አገልግሎት እንዲሰጡ የንግድ ስልጠና በመስጠት መደገፍ |

## ሠንጠረዥ መ

<table>
<tr><td colspan="2">የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ</td><td colspan="2">ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተወጽዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ</td><td colspan="2">የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ ደህንነት እና የአልሚምግብ ይዘትን በመጠበቅ በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርስውን የድህረ-ምርት ብክነት በመቀነስ የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር</td></tr>
<tr><td colspan="2">የመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖ</td><td colspan="2">አግባብነት ያለውን የድህረ-ምርት አያያዝ ሥርዓትን በማላመድና በመተግበር በግብርና እሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚደርሰውን የምግብ ብክነት መቀነስ</td></tr>
<tr><th>ውጤት 4<br>(ዋዓ 4)</th><th>ዋና ዋና ሥራዎች</th><th>ዓላማዎች</th><th>መሰራት የሚገባቸው ጉዳዮች</th></tr>
<tr><td rowspan="2">4: እሴት መጨመርን ማስፋፋት</td><td>4.1: የግብርና ግብዓት አቅራቢዎችን ማስፋፋት</td><td>ሀ፡ አነስተኛ አርሶ አደሮች ከሚፈጽሙት የድህረ-ምርት ብክነትን መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎች ግዥ ጋር በተገናኘ በዝቅተኛ ወለድ ብድር ከአበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ማግኘት እንዲችሉ ለአነስተኛ አበዳሪ ድርጅቶች እና ማህበራት ስልታዊ ድጎማ ማድረግ</td><td>4.1.1፡ በገጠር ለሚከናወኑ እሴት መጨመር ሥራዎች የገንዘብ አቅርቦትን መደገፍ<br>4.1.2፡ በገጠር አካባቢ የሚሰሩ አነስተኛ የብድር ተቋማትን መደገፍ<br>4.1.3፡ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ፓርኮች የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ</td></tr>
<tr><td>4.2: የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማሰፋፋት</td><td>ሀ፡ ለግብርና ድርጅቶች የቴክኖሎጂ እና የገንዘብ እንዲሁም የሰው ክህሎትን በማዳበር ድጋፍ ለማድረግ በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎች እና በግብርና ድርጅቶች መካከል ሽርክናን ማጠናከር<br>ለ፡ እሴት የሚጨምሩ የህብረት ሥራ ማህበራትን እና ዩኒየኖችን ማስፋፋት<br>ሐ፡ እሴትን በመጨመር የምርት ጥራትን መለየት ለሰንሰለቱ ተዋንያን በተለይም ለአርሶ አደሮች ስለሚሰጠው ጥቅም ግንዛቤ መፍጠር እና ማስፋፋት<br>መ፡ እህል በተመረተበት አካባቢ እንዲቀነባበር በማድረግ በማጓጓዝ እንዲሁም ያልተቀነባበረ ምርት በማከማቸት የሚደርሰውን የድህረ-ምርት ብክነት ለመቀነስ በገጠሩ አካባቢ አነስተኛ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያዎችን ማቋቋም እና እሴት መጨመርን ማስፋፋት</td><td>4.2.1፡ ሴቶችን እና ወጣቶችን መሰረት ያደረገ የእሴት መጨመር እና የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ሥራዎችን መደገፍ<br>4.2.2. የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ የምክክር-መድረክ መፍጠር<br>4.2.3. በግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ዙሪያ ስልጠና ለሚሰጡ አገልግሎት ሰጭዎች ድጋፍ ማድረግ፤<br>4.2.4. ደረጃ እና ዓይነትን መሠረት ያደረገ አካባቢያዊ ንግድን ማጎልበት<br>4.2.5. እሴት መጨመርን ምግብ ማቀነባበርን ጨምሮ በቀበሌ ደረጃ ማስፋፋት</td></tr>
</table>

# እዝል 2፡ የድህረ-ምርት አያያዝ የውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ እና ጠቋሚዎች

## ሠንጠረዥ ሀ፡ በለውጥ ደረጃ አመላካች፣ መነሻዎች እና ግቦች

| ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ - የውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ፡ ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተወጽዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | | | | |
| የለውጥ ቅርብ አመላካች | መነሻ | ግብ | የማረጋገጫ ምንጭ | ሃላፊነት የሚወስደው ተቋም/ ፈፃሚ አጋር-አካል |
| የግብርና ምርት ዓመታዊ እድገት | በዓመት 6.4% (2008) (የዓለም ባንክ) | በዓመት 7% (የሁለተኛው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግምት 8%) | - ብሔራዊ ቅኝት፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት | የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ፣ የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ፣<br>የተባበሩት መንግስታት ልዩ ኤጀንሲዎች፣<br>የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ኢግምኢ) |
| ከጠቅላላው አገራዊ ምርት የግብርና ምርት ድርሻ | 36.7% (2008) (የዓለም ባንክ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 2.5% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት | |
| ከጠቅላላው ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች ያለ ህዝብ (በቀን ከ 1.90 ዶላር በታች ገቢ (2003)) | 33.5% (2002) (የዓለም ባንክ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 2.5% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት | |
| አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚቀበል ሕዝብ | ከጠቅላላው ሕዝብ 5.4% (2010) (የዓለም ምግብ ፕሮግራም) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 2.5% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት | |
| በምግብ ራስን መቻል | በ 2006 ዓም ወደ አገር ውስጥ የገባውን 13.5% የሚሆነውን የአገር ውስጥ ምርት | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 10.0% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት | |
| የመቀጨጭ ክስተት / ቁምት በዕድሜ (ከ 5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት (%)) | 40.4% (2006) (የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 5% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት | |
| ከክብደት በታች (ቁመት በዕድሜ/ ክብደት በዕድሜ) (ከ 5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት (%)) | 25.2% (2006) (የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 5% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት | |
| የሕፃናት ሞት (ከ 5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት (%)) | 8.7% (2006) (የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 5% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ / የዓለም ባንክ/ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት | |
| የአልሚ ምግብ እጥረት ክስተት (%) (3-ዓመት አማካይ) | 33.1% (2006) (የዓለም ምግብ እና | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 10.0% መቀነስ | - ብሔራዊ ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት፣/ የዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች ግምት | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ) | | - ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ግምት | |

## ሠንጠረዥ ለ፡ ለመካከለኛ ጊዜ ተፅዕኖዎች ደረጃ አመላካች፣ መነሻዎች እና ግቦች

| ብሔራዊ የእህል ድህረ-ምርት አያያዝ ስትራቴጂ - የውጤት ማዕቀፍ ሠንጠረዥ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የመጨረሻ ተፅዕኖ/ ለውጥ፡ ለምግብ ዋስትና መሻሻል አስተወጽዖ ማድረግ እና አገሪቱ በመሠረታዊ ምግብ አቅርቦት ራሷን በማስቻል እና የህዝቧን ገቢ በመጨመር ድህነትን መቀነስ | | | | |
| ክፍል 1: የምግብ አቅርቦት | | | | |
| የለውጥ ቅርብ አመላካች | መነሻ | ግብ | የማረጋገጫ ምንጭ | ሃላፊነት የሚወስደው ተቋም/ ፈፃሚ አጋር-አካል |
| የሰብል ምርት | ሚሊዮን ቶን በሰብል (በዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ መሰረት)<br>• ጤፍ 5.02<br>• በቆሎ 7.23 (2006)<br>• ስንዴ 4.23 (2006)<br>• ማሽላ 4.34 (2006)<br>• ቦሎቄ 0.51 (2006) (የቦሎቄ ብቻ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 10.0% መጨመር | - የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ | የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ |
| የሰብል ምርታማነት (ምርት በሜትሪክ ቶን በለማ ሄክታር) | ኪ.ግ በሄክታር (የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ መሰረት)<br>• ጤፍ 1.74<br>• በቆሎ 3.42 (2006)<br>• ስንዴ 2.54 (2006)<br>• ማሽላ 2.37 (2006)<br>• ቦሎቄ 1.59 (2006) — (በአጠቃላይ ጥራጥሬዎችን መሰረት በማድረግ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 10.0% መጨመር | የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ)<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ | የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር (እተሀሚ)፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ |
| የምርት ብክነት ግምት (%) | ከጠቅላላው ምርት በመቶኛ (በዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ መሰረት)<br>• ጤፍ 12%<br>• በቆሎ 18% (2005)<br>• ስንዴ 12% (2005)<br>• ማሽላ 5 % (2005)<br>• ቦሎቄ 13% (በአጠቃላይ ጥራጥሬዎችን መሰረት በማድረግ) | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 50% መቀነስ | የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ቅኝት፣<br>- የዓለም ምግብ እና እርሻ ድርጅት ስታትስቲክስ<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ | የእርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር (እተሀሚ)፣ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ |
| ክፍል 2: የምግብ ተደራሽነት | | | | |
| የምርት ዋጋ | ዓመታዊ አማካይ ( ብር በቶን አዲስ አበባ ከተማ ባለ ገበያ)<br>• ጤፍ 24000<br>• በቆሎ 6000<br>• ስንዴ 12000<br>• ማሽላ 9000<br>• ቦሎቄ16000<br>• ገብስ 9000<br>• ሽምብራ 30000<br>• ባቄላ 25000 | መነሻ ከነበረው ዋጋ በየዓመቱ በ 5% መጨመር | - የንግድ ሚኒስቴር ቅኝት<br>- ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ | የንግድ ሚኒስቴር ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • አተር 25000<br>• ምስር 38000<br>• ኑግ 45000<br>• ሰሊጥ 1800<br>• ኦቾሎኒ (ለውዝ) 1800 | | | |
